# በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ
# ሪፐብሊክ
# የፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት

# በኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን የጉምሩክ ሥነ-ሥርዓት አፈፃፀምን በተመለከተ የተከናወነ የክዋኔ ኦዲት ሪፖርት

መጋቢት 2009 ዓ.ም

አዲስ አበባ

## ማውጫ

ገጽ

የዋና ዋና ግኝቶች ማጠቃለያ ..... 1

**ክፍል አንድ** ..... 4

መግቢያ ..... 4

የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን አመሰራረት ..... 5

የባለስልጣኑ ዓላማዎች ..... 6

የባለስልጣኑ ሥልጣንና ተግባር ..... 6

የባለስልጣኑ ድርጅታዊ መዋቅር እና የሰው ኃይል አደረጃጀት ..... 8

የባለስልጣኑ የፋይናንስ ምንጭ ..... 9

የጉምሩክ ስነ-ሥርዓት አሠራር ፍሰት ስዕላዊ መግለጫ፤ ..... 9

የኦዲቱ አላማ ..... 10

የኦዲቱ የትኩረት አቅጣጫዎች (Audit Issues) ..... 10

የኦዲቱ መመዘኛ መስፈርቶች ..... 11

የኦዲቱ ወሰን እና ዘዴ ..... 11

**ክፍል ሁለት** ..... 12

**የኦዲት ግኝቶች** ..... 12

ጭነቶች የትራንዚት ፈቃድ የተሰጣቸው መስፈርቱን አሟልተው ስለመሆኑ እና እንቅስቃሴ ከመጀመራቸው በፊት የትራንዚት ስነ ስርዓት መፈጸሙን ማረጋገጥ በተመለከተ፣ ..... 12

ትራንዚት ላይ ያሉ ጭነቶች በጉምሩክ ማሸጊያ መታሸጋቸውን እና በታሸጉበት ሁኔታ መድረሳቸውን ማረጋገጥ በተመለከተ፣ ..... 14

የትራንዚት ሂደታቸውን ያጠናቀቁ ጭነቶች በተነሱበት ሁኔታ እና የጊዜ ገደብ መድረሳቸውን እና በጊዜ ገደቡ የደረሱና ያልደረሱትን የትራንዚት እቃዎች በሲስተም የማጣራትና የማስታረቅ ስራ ስለመሰራቱ፣ ..... 16

የጉምሩክ ትራንዚት ስነ-ሥርዓት በዘመናዊ የመረጃ ቴክኖሎጂ እና በስጋት ስራ አመራር አሰራር ስርዓት መሰረት እየተከናወነ መሆኑን በተመለከተ፣ ..... 18

ትራንዚት የጀመሩ ጭነቶች መረጃ ወደ መረጃ ቴክኖሎጂ ቋት መተላለፋቸውን በተመለከተ ፣ ........................ 21

ወደ አገር የሚገቡ እና ከአገር የሚወጡ ዕቃዎችና ማጓጓዣዎች ላይ ስለሚደረግ ፍተሻ እና የጉምሩክ ስነ ስርዓት መፈጸሙን ማረጋገጥ በተመለከተ፣ ........................................................................ 22

በባለስልጣኑ የተዘረጋው የጉምሩክ ዕቃ አወጣጥና የመጋዘን አሠራር ስርዓት ቀልጣፋ እና ውጤታማ መሆኑን መገምገም በተመለከተ፤ ........................................................................ 26

የጉምሩክ ዕቃ አወጣጥ ሥነ-ሥርዓት በብቃት እና በቅልጥፍና የሚከናወን መሆኑን ማረጋገጥ በተመለከተ፣ ..... 26

የጉምሩክ መጋዘን ሊያሟላ ስለሚገባው መስፈርት እና የመጋዘን ባለቤቶች ግዴታ በተመለከተ፣ ...................... 28

የጉምሩክ መጋዘን የዕቃዎች አቀማመጥ፣የምዝገባና ሪፖርት ስርዓት እንዲሁም የመጋዘን ኪራይ አሰራር በተመለከተ፣ ........................................................................ 32

በጉምሩክ መጋዘን የዕቃዎች በመጋዘን የቆይታ ጊዜ በጉምሩክ አዋጅ ቁጥር 859/2006 በተቀመጠው መሰረት ተግባራዊ ስለመደረጉ፣ ........................................................................ 34

ባለስልጣኑ ወቅታዊና የክህሎት ክፍተትን መሰረት ያደረገ ስልጠና መሰጠቱን እና የተሟላ የሰው ኃይል መቀጠሩን በተመለከተ፣ ........................................................................ 36

በባለስልጣኑ ዘመናዊና ቀልጣፋ የሆነ የመረጃ አያያዝና ልውውጥ ስርዓት መኖሩን በተመለከተ፣ ..................... 38

በባለስልጣኑ የአንድ መስኮት አገልግሎት ስርዓት የተዘረጋ እና ተግባራዊ የተደረገ መሆኑን በተመለከተ፣ ....... 40

በባለስልጣኑ ስለሚደረጉ የክትትልና ድጋፍ ስራዎች በተመለከተ፣ ........................................................ 41

በባለስልጣኑ ከባለድርሻ አካላት ጋር ስለሚደረጉ የጋራ የውይይት መድረኮች በተመለከተ፣ .............................. 43

**ክፍል ሦስት** ........................................................................ 45

**መደምደሚያ** ........................................................................ 45

**ክፍል አራት** ........................................................................ 48

**የማሻሻያ ሃሣቦች** ........................................................................ 48

አባሪ 1 ያለዘርፍ አስመጪነት ዕቃዎችን ያስመጡ ዝርዝር........................................................ 51

አባሪ 2 ........................................................................ 52

የኦዲቱ የትኩረት አቅጣጫዎችና የመመዘኛ መስፈርቶች........................................................ 52

አባሪ 3 የጉምሩክ ስነ -ሥርዓት የስራ ፍሰት ስዕላዊ መግለጫ ........................................................ 55

## የዋና ዋና ግኝቶች ማጠቃለያ

## /Executive Summery/

ኦዲቱ የተከናወነው የመንግሥት መ/ቤቶችን የክዋኔ ኦዲት ለማድረግ ለፌደራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት በአዋጅ ቁጥር 982/2008 በተሰጠው ሥልጣን መሠረት ሲሆን የክዋኔ ኦዲቱ አላማ የጉምሩክ ሥነ-ሥርዓት አፈጻጸምን በተመለከተ ስራውን ለማስፈጸም የወጡ ሕጎችና ደንቦች ላይ በመመስረት ባለስልጣኑ ያወጣቸውን መመሪያዎችና የገባቸውን አለምአቀፍና አገር አቀፍ ስምምነቶች በተቀላጠፈና ውጤታማ በሆነ መንገድ ተግባራዊ ለማድረግ የሚያስችል የአሰራር ሥርዓት መዘርጋቱን እና የተዘረጋው የአሰራር ሥርዓት ተፈፃሚ መደረጉን ማረጋገጥ ሲሆን በዚሁ መሰረት በኦዲቱ የተገኙ ዋና ዋና ግኝቶች የሚከተሉት ናቸው፡፡

- ነዳጅ ጭነው ወደ አገር ውስጥ ለሚገቡ ተሽከርካሪዎች ዲክላራሲዮን እና የመንገድ ወረቀት (T1) አይዘጋጅም፣ የአሰራር ስርዓት አልተዘረጋም፣የወጪ ትራንዚት እቃ ትክክለኛነት ሲጫን በአካል ተገኝቶ በማረጋገጥ በሲል ማሸግ እና ሲል ቁጥሩን በአውቶሜሽን ሲስተም በመመዝገብ ትራንዚቱ እንዲጀምር የሚያደርግ አሰራር ተግባራዊ አልተደረገም፡፡
- በሀገር ውስጥ ተመርተው ወይንም እሴት ተጨምሮባቸው ለውጭ ገበያ የሚላኩ ምርቶች የሚታሸጉበት ደረጃውን የጠበቀ የጉምሩክ ማሸጊያ /ሲል/ የሌለ በመሆኑ ህገ ወጥነትን ለመቆጣጠር በማይቻልበት መንገድ በሽቦ ብቻ እየታሰረ ወደ ውጭ እየተላከ እንደሚገኝ ለማወቅ ተችሏል፡፡
- በመልቲሞዳል ስርዓት ተጓጉዘው ወደ አገር የገቡ ጭነቶች ቃሊቲ ገቢዎች እና ጉምሩክ ቅ/ጽ/ቤት መድረስ የነበረባቸው ከ2006-2008 ዓ.ም 1,365 ኮንቴይነሮች እና ሞጆ ገቢዎች እና ጉምሩክ ቅ/ጽ/ቤት ከተጀመረበት ጀምሮ መግባት የነበረባቸው ጭነቶች 2,647 ኮንቴይነሮች በድምሩ 4,021 በቅርንጫፍ ጽ/ቤቶቹ መድረሳቸው በሲስተም ቫሊዴት አለመደረጉ፣በተጨማሪም እ.ኤ.አ ከ2013 እስከ 2016 በሚሌ ጉምሩክ ቅ/ጽ/ቤት፣አዳማ ጉምሩክ ቅ/ጽ/ቤት፣ሞያሌ ጉምሩክ ቅ/ጽ/ቤት፣ጅማ ገቢዎችና ጉምሩክ ቅ/ጽ/ቤት እና መቀሌ ገቢዎችና ጉምሩክ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት በድምሩ 2,131 የመልቲ ሞዳል ጭነቶች በቅርንጫፍ ጽ/ቤቶቹ መድረሳቸው በሲስተም ቫሊዴት አለመደረጉ ፣
- ባለስልጣኑ የኤሌክትሮኒክስ የጭነት መቆጣጠሪያ ስርዓት (Electronics Cargo Tracking and Monitoring System) ከጥር 2003 ዓ.ም ጀምሮ በአምስት አመታት ጊዜ ውስጥ በትንሹ 10,000 ተሽከርካሪዎችን ወደ ስርአቱ በማስገባት ወደ ሙሉ ትግበራ

እንደሚገባ በውል ስምምነቱ ቢገለጽም እስከ 2008 በጀት አመት መጨረሻ 312 (3%) ተሽከርካሪዎች ብቻ የካርጎ ትራኪንግ መሳሪያ የተገጠመላቸው መሆኑ እና የተዘረጋው የካርጎ ትራኪንግ ሲስተም ከኢትዮጵያ መግቢያ በር ጋላፊ ጀምሮ ሲሆን በውሉ መሰረት ከጅቡቲ ወደብ እስከ ጋላፊ ባለው ስፍራ ስርአቱ ያልተዘረጋ መሆኑ፣

- በባለስልጣኑ በስምንት የጉምሩክ መቆጣጠሪያ ጣቢያዎች በዘመናዊ የፍተሻ መሳሪያ (Scanning Machine) የታገዘ አገልግሎት ለመስጠት ታቅዶ በ2003 ዓ.ም ወደ ስራ የተገባ ቢሆንም ከስምንቱ መቆጣጠሪያ ጣቢያዎች ውስጥ በጋላፊ ጉምሩክ ቅ/ጽ/ቤት ብቻ አገልግሎቱ እየተሰጠ ሲሆን በቀሪዎቹ ሰባት ጣቢያዎች አገልግሎቱ ያልተጀመረ መሆኑን ለማወቅ ተችሏል፡፡
- በአዲስ አበባ ኤርፖርት ጉምሩክ ቅ/ጽ/ቤት በ190 የማስጫኛ ሰነድ የመጡ ብር 101,932,491 ግምታዊ የቀረጥና ታክስ ዋጋ ያላቸው ጭነቶች አስፈላጊው የጉምሩክ ስነ ስርዓት ሳይፈጸምባቸው አየር በአየር ከኢትዮጵያ አየር መንገድ መጋዘን የወጡ መሆኑ፣
- በባለስልጣኑ የጉምሩክ አዋጅ 859/2006 አንቀጽ 6(4) መሰረት መ/ቤቱ የገቢ፣የወጪ እና የተላላፊ እቃዎችን በሚመለከት የሚኖር የስጋት ደረጃን የሚወስን መመሪያ እንደሚያወጣ ቢገልጽም መመሪያው ያልወጣ መሆኑን ለማወቅ ተችሏል፡፡
- በ2008 በጀት ዓመት በቀይ የሥጋት ደረጃ የተስተናገዱ ዲክላራሲዮኖች 35 በመቶ ሲሆን 20 በመቶ ለማድረስ ታቅዶ አለመሳካቱ፣በ2007 በጀት ዓመት በቀይ የሥጋት ደረጃ የተስተናገዱ ዲክላራሲዮኖች 40.02 በመቶ ሲሆን 31 በመቶ ለማድረስ ታቅዶ ያልተሳካ መሆኑ፣
- በአዋጅ ቁጥር 859/2006 የተቀመጡ ግዴታዎች እና ስለጉምሩክ መጋዘን አስተዳደር የወጣ የአፈፃፀም መመሪያ ቁጥር 40/2002 ላይ የተቀመጡ መስፈርቶችን ሳያሟሉ የሚሰሩ የጉምሩክ መጋዘኖች የሚገኙ መሆኑ፣
- በባለስልጣኑ የጉምሩክ ጊዜያዊ የዕቃ ማከማቻ መጋዘኖች ዕቃዎች እንደአይነታቸውና እንደባህሪያቸው ተለይተው ለደህንነታቸው ተስማሚ በሆነና ለጉምሩክ ቁጥጥር አመቺ በሆነ ሁኔታ ያልተቀመጡ መሆናቸው፣በጉምሩክ አዋጅ ቁጥር 859/2006 አንቀጽ 59 ንዑስ አንቀጽ 2 መሰረት የጉምሩክ መጋዘን ኪራይ ማስከፈያ ተመን ደንብ ያልወጣ መሆኑ፣
- በጉምሩክ መጋዘን የዕቃዎች በመጋዘን የቆይታ ጊዜ በጉምሩክ አዋጅ ቁጥር 859/2006 በተቀመጠው መሰረት ተግባራዊ ያልተደረገ መሆኑ፣ እስከ ሰኔ 30/ 2008 ዓ.ም በሞጆ

ደረቅ ወደብ ከሶስት ወር እስከ አንድ አመት 967 እና ከአንድ አመት በላይ የሆናቸው 213 ኮንቴይነሮች በድምሩ 1,180፤ በአዲስ አበባ ቃሊቲ ደረቅ ወደብ ከሁለት ወር በላይ የቆዩ 54 ኮንቴነሮች ፣መጋዘን ቁጥር አንድ 29፣መጋዘን ቁጥር ሁለት 28 ፣ መጋዘን ቁጥር አምስት 21፣ መጋዘን ቁጥር ስድስት 19፣ መጋዘን ቁጥር ሰባት 16፣መጋዘን ቁጥር አስራ ሁለት 18 የተለያዩ እቃዎች እና በክፍት መጋዘን 3 ኮንቴነሮች ከሁለት ወር በላይ በመጋዘን የቆዩ መገኘታቸው፣

- በአዳማ ገቢዎችና ጉምሩክ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት ገቢ የተደረጉ እና የቆይታ ጊዜያቸውን ያሳለፉ የተለያዩ እቃዎች ለማሳያነት ያክል 11 ኮንቴነር ፣ በቁጥር 489 ልዩ ልዩ የመኪና ጎማዎች፣ባለ 25 ኪ.ግ 2,616 ከረጢት ሩዝ፣ 783 ካርቶን ኮስሞቲክስ እና 385 ካርቶን እስክርቢቶ ወደ ውርስ መጋዘን ሳይተላለፉ ጊዜያዊ እቃ ማከማቻ መጋዘን ውስጥ ተከማችተው የሚገኙ መሆኑ፣
- የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን በማቋቋሚያ አዋጅ 587/2000 ከተሰጡት ስልጣንና ተግባራት መካካል የሠራተኞችን አቅም ለመገንባት የሚያስችለውን ማዕከል እንዲደራጅ ያደርጋል፣የስልጠናና የሙያ ማሻሻያ ስርዓቶችን ይዘረጋል ቢልም የሰራተኞችን አቅም ለመገንባት የሚያስችል ማዕከል አልተደራጀም። በናሙና በታዩ የጉምሩክ ቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች የሚፈለገው የሰው ኃይል ያልተሟላ መሆኑ።
- በጋላፊ ጉምሩክ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት የስካኒንግ ማሽን ከአሲኩዳ ሲስተም ጋር ያልተገናኘ መሆኑ፣ በአዲስ አባባ ኤርፖርት ፣ቃሊቲ፣ሞጆ እና አዳማ ገቢዎችና ጉምሩክ ቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች የመጋዘን አስተዳደር እና ቁጥጥር በዘመናዊ የመረጃ ቴክኖሎጂ አያያዝ ያልተደገፈ መሆኑ፣
- ባለስልጣኑ የኤሌክትሮኒክስ አንድ መስኮት አገልግሎት ለመስጠት እንዲያስችለው በታህሳስ ወር 2006 ዓ.ም ከInvestment Climate Facility for Africa (ICF) ጋር የፕሮጀክት ስምምነት በመፈራረም በአስራ ስምንት ወራት ለማጠናቀቅ በይፋ ስራው ተጀምሮ ፕሮጀክቱ ሳይጠናቀቅ ወደ ፕሮግራም ተቀይሮ በሂደት ላይ ቢሆንም ትግበራው የተጓተተ መሆኑ።

## ክፍል አንድ

### መግቢያ

1. በኢትዮጵያ እድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ ሰነድ መሰረት የትራንስፎርሜሽን ዕቅዱን ለማከናወን የሚያስፈልገው ወጪ በተለይ የመንግስት መደበኛ ወጪ በሙሉ ከቀጥተኛና ቀጥተኛ ካልሆኑ ታክሶች በሚሰበሰብ ገቢ እንደሚሸፈን ታሳቢ ያደርጋል፡፡መንግስት የቀረጸው የእድገትና የትራንስፎርሜሽን እቅድ ከግብ ለማድረስ የሀገሪቱ ኢንቨስትመንትና ኢንዱስትሪ ልማት በዓለም አቀፍ ደረጃ ተወዳዳሪና ውጤታማ እንዲሆን ዘመናዊ፣ ቀልጣፋና በመረጃ የተደገፈ የጉምሩክ አሠራር መዘርጋት ያስፈልጋል፡፡ይህንን ለማሳካት የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን ቀረጥና ታክስን በፈቃደኝነት የመክፈል ባህልን በማዳበር ለሃገር ልማት የሚውል ገቢ በብቃት እንዲሰበሰብ ፣ ልማታዊ ባለሀብቶችን መደገፍ የሚያስችል የተለያዩ የአሰራርና የአደረጃጀት ማሻሻያዎች በማድረግ ላይ መሆኑ ይታወቃል፡፡

2. ከእነዚህ አደረጃጃቶች መካከል አንዱ የጉምሩክ አሰራርና ፕሮግራም ልማት ዳይሬክቶሬት ነው፡፡ ለዳይሬክቶሬቱ ከተሰጡት ተልዕኮዎች በዋናነት የጉምሩክ የቁጥጥር ስርዓት እና የተሳለጠ የጉምሩክ አገልግሎት እንዲጣጣም ለማድረግ የተለያዩ ዘመናዊ የጉምሩክ አሰራሮችን መቅረፅና እነዚህ አሰራሮች በሁሉም የጉምሩክ ባለሙያዎችና ባለድርሻ አካላት እንዲሰርፁ እና ቀጣይነት እንዲኖረው በማድረግ የጉምሩክ አገልግሎት አሰጣጡ ፈጣን ፣ ለኪራይ ሰብሳቢነት ተጋላጭ ያልሆነ ፣ ወጪ ቆጣቢ ፣ ግልፀኝነት እና በንግድ ማህበረሰቡ ዘንድ ተቀባይነት ያለው የጉምሩክ አሰራር እንዲዘረጋ ማድረግ ነው፡፡

3. በዚህ መሰረት ባለስልጣኑ ከዘመናዊ የጉምሩክ አሠራር ጋር ተያያዥነት ያላቸው መርሆዎችን እና የአገሮች ምርጥ ተሞክሮ መሠረት በማድረግ በአንድ በኩል የአገሪቷን የኢንዱስትሪ ልማት እድገት በማገዝ የውጭ ንግድ የሚቀላጠፍበት በሌላ በኩል የአገር ውስጥ ንግዱ በፍትሃዊነት የሚወዳደርበት ሁናቴ ለመፍጠር የሚያስችል የዓለም አቀፍ ደረጃን የጠበቀ የጉምሩክ አሠራር ሥርዓት ተግባራዊ ለማድረግ እንዲቻል ጥናት ተጠንቶ በጥናቱ መሰረት የጉምሩክ አሰራር ስርዓት ተቀርጾ ተግባራዊ እየተደረገ ይገኛል፡፡

**የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን አመሰራረት**

4. የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን በ1989 ዓ.ም. በአዋጅ ቁጥር 60/1989 መሰረት የፌዴራል መንግስት መሥሪያ ቤት ሆኖ የኢትዮጵያ ጉምሩክ ባለሥልጣን በመባል እንደገና የተቋቋመ ሲሆን፣ ተጠሪነቱም ለገቢዎች ቦርድ እንዲሆን ተደነገገ፡፡ ከዚያም በአዋጅ ቁጥር 368/1995 መሰረት የኢትዮጵያ ጉምሩክ ባለስልጣን እና የፌዴራል አገር ውስጥ ገቢ ባለሥልጣን ሆኖ ተጠሪነቱ ለገቢዎች ሚኒስቴር ሆነ፡፡ በመቀጠልም በአዋጅ ቁጥር 587/2000 መሰረት የገቢዎች ሚኒስቴር፣ የኢትዮጵያ ጉምሩክ ባለስልጣን እና የፌዴራል አገር ውስጥ ገቢ ባለሥልጣን "የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን" ተብሎ እንዲቋቋምና ባለስልጣን መ/ቤቱ ተጠሪነቱ ለጠቅላይ ሚኒስትሩ እንዲሆን ተደንግጓል፡፡ በዚሁ አዋጅ ላይ ብቁ ባለሙያዎችን ያቀፈ የባለስልጣኑ አማካሪ ቦርድ እንደሚቋቋም ፣ የቦርዱ ሊቀመንበር ዋና ዳይሬክተሩ እንደሚሆኑ ፣ የአባላቱ አሰያየም ችሎታና ብቃትን መሠረት በማድረግ በዋና ዳይሬክተሩ መሆኑን ፣ የቦርዱ ዋና ፀሀፊም በዋና ዳይሬክተሩ እንደሚመደብና ቦርዱም በዕለት ተዕለት ተግባሮች ላይ ሳይገባ ባለሥልጣኑን በፖሊሲና ስትራቴጂ ነክ ጉዳዮች ላይ እንደሚያማክር ተገልጿል፡፡

5. በመጨረሻም አለም አቀፍ የንግድ እንቅስቃሴ ከደረሰበት የእድገት ደረጃ ጋር የሚጣጣምና በአገራችን እያደገ የመጣውን የማኑፋክቸሪንግ ኢንዱስትሪ ልማት የሚደግፍ እንዲሆን ህጋዊ ንግድና ኢንቨስትመንትን የሚያበረታታ ዘመናዊ የጉምሩክ ህግ ማእቀፍ ስራ ላይ ማዋል በማስፈለጉ፤

6. አገሪቱ አባል የሆነችባቸው አለማቀፋዊ፣ አህጉራዊና አካባቢያዊ የንግድ ስምምነቶች ወቅታዊ የጉምሩክ ህግና የአሰራር ስርዓት እንዲኖር የሚያስገድዱ በመሆናቸው፣

7. ኮንትሮባንድና ሌሎች የንግድ ማጭበርበር ወንጀሎች በህጋዊ የንግድ እንቅስቃሴ፤ በህዝብ ደህንነት፤ በመንግስት ገቢና በሌሎችም ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ እድገቶች ላይ የሚያስከትሉትንና ከጊዜ ወደጊዜ እየጨመረ የመጣውን አሉታዊ ተጽእኖ ለመከላከል የተጠናከረ የህግ ማስከበሪያ ስርዓት መዘርጋት በማስፈለጉ በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ህገ መንግስት አንቀጽ 55/1 መሰረት "የጉምሩክ አዋጅ ቁጥር 859/2006" ታውጇል፡፡

**የባለስልጣኑ ዓላማዎች**

8. በአዋጅ ቁጥር 587/2000 መሰረት የባለሥልጣኑ አላማዎች የሚከተሉት ናቸው፣

- ዘመናዊ የገቢ አወሳሰንና አሰባሰብ ሥርዓት በመዘርጋት ለተገልጋዮች ፍትሐዊ ፣ ቀልጣፋና ጥራት ያለው አገልግሎት መስጠት፣
- ታክስ ከፋዩ ግዴታውን በፈቃደኝነት እንዲወጣ ማስቻል፣
- ኮንትሮባንድን፣ የታክስ ማጭበርበርና ስወራን በመከላከልና በመቆጣጠር የታክስና የጉምሩክ ሕግጋትን ማስከበር፣
- ኢኮኖሚው የሚያመነጨውን የታክስ ገቢ በብቃትና በወቅቱ መሰብሰብ፣
- የፌዴራልና የክልል ታክስ አስተዳደር ሥርዓቶች የተጣጣሙ እንዲሆኑ ለማድረግ ለክልሎች አስፈላጊውን ድጋፍ ማድረግ።

**የባለስልጣኑ ሥልጣንና ተግባር**

9. ባለስልጣኑ በአዋጅ ቁጥር 587/2000 የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ተሰጥቶታል፦

- ዘመናዊ የገቢ አወሳሰንና አሰባሰብ ሥርዓት በመዘርጋት ተግባራዊ ያደርጋል፣
- በመስኩ ግልጽነትንና ተጠያቂነትን መሠረት በማድረግ ፍትሐዊ፣ ቀልጣፋና ጥራት ያለው አገልግሎት ይሰጣል፤ ኢንቨስትመንትን ለማበረታታት ለባለሀብቶች የተሰጡ የታክስና የቀረጥ ነፃ መብቶች በአግባቡ እንዲፈፀሙ ያደርጋል፤ ለታሰበው ዓላማ መዋላቸውን ይከታተላል፣
- ታክስ ከፋዮች በፍቃደኝነት ታክስ የመክፈል ባሕልን እንዲያዳብሩ የግንዘቤ ማስጨበጫ ፕሮግራሞችን ተግባራዊ ያደርጋል፣
- የታክስ ማስከፈያ ዋጋ ይተምናል፤ ተከፋይ የሚሆነውን የታክስ መጠን ይወስናል፤ ይሰበስባል፣
- የጉምሩክና የታክስ ሕጎችን ፣ ደንቦችንና መመሪያዎችን አፈፃፀም ለማሻሻል የበለጠ አጽንኦት በመስጠትና ሌሎች ገቢዎች በአግባቡ እንዲሰበሰቡ ለማድረግ የጥናትና የምርምር ሥራዎችን ያካሂዳል ፣ በጥናትና ምርምሩ ውጤት መሠረት ፖሊሲዎችንና ህጎችን ያመነጫል ፣ ሲፈቀድም በሥራ ላይ ያውላል፣
- ለገቢና ወጪ ዕቃዎች ቁጥጥርና ለታክስ አወሳሰን የሚያስፈልጉ መረጃዎችን ይሰበስባል ፣ ይተነትናል ፣ በመስኩ ስለሚፈጸሙ ወንጀሎች የተሟላ የስታትስቲክስ መረጃ ያጠናቅራል፤ እንደ አስፈላጊነቱም ለሌሎች አካላት ያሰራጫል፣

- የጉምሩክና የታክስ ሕጎችን በመጣስ የሚፈጸሙ ወንጀሎችን ይመረምራል፤ ይከሳል ይከራከራል፤ ይህንኑ ለማከናወን የራሱን ዐቃቤያነ ሕግና መርማሪዎች ቡድን ያደራጃል አፈፃፀማቸውን ይቆጣጠራል፣
- የሰራተኞችን አቅም ለመገንባት የሚያስችለውን ማእከል እንዲደራጅ ያደርጋል፣ የስልጠናና የሙያ ማሻሻያ ስርዓቶችን ይዘረጋል፣
- በጉምሩክ ወደቦች ፣ በወሰን አካባቢዎች እንዲሁም በሌሎች የጉሙሩክ መቆጣጠሪያ ጣቢያዎችና ማቋረጫ መስመሮች በኩል የሚገቡና የሚወጡ እቃዎችንና ማጓጓዣዎችን ይፈትሻል፣ የጉሙሩክ ስነ-ስርዓት ተፈጽሞባቸው መግባታቸውንና መውጣታቸውን ያረጋግጣል፣
- ህጋዊ ባልሆነ መንገድ ወደ አገር የሚገቡትን ወይም ከአገር የሚወጡትን እቃዎች እንቅስቃሴ የመቆጣጠርና ኮንትሮባንድን የመከላከል ስራ በፌዴራል ፖሊስ አማካኝነት እንዲካሄድ የመረጃ ልውውጥ ያደርጋል፣ ተገቢውን ድጋፍ ይሰጣል፣ ህጉ በሚፈቅደው መሰረት ተገቢው እርምጃ እንዲወሰድ ያደርጋል፣
- የጉምሩክና የታክስ ሕጎችን ለማስፈጸም የሚያስፈልጉ በማናቸውም ሰው እጅ የሚገኙ ሠነዶችን ይመረምራል፤ ይይዛል፤ ዘመናዊ የዕቃዎችና የሠነዶች ምርመራ አገልግሎት ላብራቶሪ ያደራጃል፤ በጥቅም ላይ ያውላል፣
- ወደ አገር የሚገቡ ወይም ወደ ውጪ አገር የሚላኩ እቃዎች የሚከማቹበትን ስፍራ ይወስናል፣ መጋዘን ያቋቁማል፣ የመጋዘን ፍቃድ ይሰጣል፣ የቀረጥ ነጻ እቃዎች መሽጫ መደብሮችን ይቆጣጠራል፣ ስለእቃዎች አያያዝና ጥበቃ ቁጥጥር ያደርጋል፣ የሰጠውን የመጋዘን ፍቃድ ያግዳል፣ ይሰርዛል፣ የአገልግሎት ክፍያ ይሰበስባል፣
- በተወሰኑ ጉዳዮች ላይ የጉምሩክና የታክስ ወንጀሎችን የመመርመር፣ የመክሰስና ኮንትሮባንድን የመቆጣጠር እንዲሁም ታክስ የመወሰንና የመሰብሰብ ሥልጣኑን በሙሉ ወይም በከፊል ለክልል የፍትህ አካላትና ገቢ ሰብሳቢ አካላት በውክልና ሊሰጥ ይችላል፣ ለአፈፃፀሙ ተገቢውን ድጋፍና ክትትል ያደርጋል፣
- የብሄራዊ ሎተሪ አስተዳደር ስራዎችን በበላይነት ይመራል፣ ይቆጣጠራል፣
- ለክልል ገቢ ሰብሳቢ አካላት ተገቢውን የአቅም ግንባታ ድጋፍ በመስጠት የፌዴራልና የክልል ታክስ አስተዳደር ስርዓቶች የሚጣጣሙበትን ሁኔታ ይፈጥራል፣
- የታክስና የጉምሩክ አስተዳዳርን በሚመለከት ውሎችንና ዓለም አቀፍ ስምምነቶችን ያደርጋል፣

- በሥራ ላይ ባሉ ሌሎች ህጎች ለፌዴራል አገር ውስጥ ገቢ ባለስልጣንና ለጉምሩክ ባለሥልጣን ተሰጥተው የነበሩ ሥልጣንና ተግባራት በሥራ ላይ ያውላል፣
- የንብረት ባለቤት ለመሆን፤ ውል ለመዋዋልና በስሙ ለመክሰስና ለመከሰስ ይችላል፣
- ዓላማውን ተግባራዊ ለማድረግ የሚያስፈልጉ ሌሎች ተዛማጅ ተግባሮችን ያከናውናል፡፡

**የባለስልጣኑ ድርጅታዊ መዋቅር እና የሰው ኃይል አደረጃጀት**

10.ባለስልጣን መ/ቤቱ ተጠሪነቱ ለጠቅላይ ሚኒስትር ሆኖ ፣ በአንድ ዋና ዳይሬክተር፣ በስሩ በሚገኙ አምስት ምክትል ዋና ዳይሬክተሮች ፣ እንዲሁም በ34 ዳይሬክቶሬቶች እና በ31 ቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች ተዋቅሯል:: ካሉት አምስት ምክትል ዋና ዳይሬክተሮች ውስጥ የጉምሩክ ጉዳዮች ኘሮግራም ልማትና ድጋፍ ሥራዎች ዘርፍ ም/ዋ ዳይሬክተር በስሩ አራት ዳይሬክቶሬቶች (የጉምሩክ ጉዳይ ቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች ድጋፍና ክትትል ዳይሬክቶሬት ፣ የጉምሩክ ሥነ-ሥርዓት ኘሮግራም ልማትና ድጋፍ ዳይሬክቶሬት ፣ የዋጋ ትመናና ታሪፍ ምደባ ኘሮግራም ልማትና ድጋፍ ዳይሬክቶሬት እና የድህረ-ዕቃ አወጣጥ ኦዲት ፕሮግራም ልማትና ድጋፍ ዳይሬክቶሬት) አሉት፡፡ ከእነዚህ ዳይሬክቶሬቶች ውስጥ በቀጥታ ከኦዲት አካባቢው ጋር ተያያዥነት ያለው የጉምሩክ ስነ-ስርዓት ፕሮግራም ልማትና ድጋፍ ዳይሬክቶሬት ሲሆን ይህ ዳይሬክቶሬት በስሩ አራት የቡድን አስተባባሪዎች ሲኖሩ ሁለቱ የቡድን አስተባባሪዎች (የጉምሩክ ዕቃ አወጣጥና የመጋዘን አሠራር ፕሮግራም ልማት እና የትራንዚት ሥራ አመራር አሠራርና ፕሮግራም ልማት) ከኦዲት አካባቢው ጋር በቀጥታ ግንኙነት ያላቸው ሆኖ ተገኝቷል፡፡ባለስልጣን መ/ቤቱ 21,461 በመዋቅር የተፈቀደ የሰው ኃይል ያለው ሲሆን ከተፈቀደለት የሰው ኃይል ውስጥ በሰኔ 30/2008 ዓ.ም ወንድ 5,842 ሴት 5,884 በድምሩ 11,732 (54.75%) በስራ ላይ ያለ የሰው ኃይል መሆኑን ለማወቅ ተችሏል፡፡

**የባለስልጣኑ የፋይናንስ ምንጭ**

11.ባለስልጣን መ/ቤቱ ሥራውን የሚያንቀሳቅሰው ለደመወዝ፣ ለሥራ ማስኬጃ እና ለካፒታል በጀት ከመንግስት በሚመደብለት በጀት እንዲሁም ከተለያዩ ለጋሽ አካላት ከሚገኘው እርዳታ ነው፡፡ ባለሥልጣን መ/ቤቱ ገቢውን የሚሰበስበው ከውጭ ንግድ ቀረጥና ታክስ (ከወጪ እና ገቢ ንግድ ዕቃዎች)፣ ከሀገር ውስጥ ገቢ ግብር፣ ከብሔራዊ ሎተሪ አስተዳደር የተጣራ ትርፍ እና ከኮንትሮባንድ ዕቃዎች ሽያጭ ነው፡፡ በዚሁ መሰረት ከ2006-2008 በጀት አመታት የተመደበለት በጀት፣ በስራ ላይ ያዋለው ሂሳብና በነዚህ በጀት ዓመታት የተያዘው የገቢ ዕቅድ እና የተሰበሰበው ገቢ ከታች ባለው ሰንጠረዥ የተገለጸ ሲሆን፣ ከኮንትሮባንድ ዕቃ ሽያጭ የሚገኘውን ገቢ በተመለከተ በዕቅድ የማይያዝና አፈጻጸሙም የማይታይ በመሆኑ በሰንጠረዡ ውስጥ አልተካተተም፡፡

| በጀት ዓመት | በጀት አጠቃቀም | | | በበጀት ዓመቱ የተሰበሰበሰ ገቢ | | |
|---|---|---|---|---|---|---|
| | የተፈቀደ በጀት | ሥራ ላይ የዋለ | ሥራ ላይ የዋለው በመቶኛ | የገቢ ዕቅድ በሚሊዮን | የተሰበሰበ ገቢ በሚሊዮን | በመቶኛ |
| 2006 | 913,143,930.43 | 847,730,640.00 | 92.84 | 116,802.44 | 106,798.28 | 91.43 |
| 2007 | 1,293,980,000.00 | 1,239,940,000.00 | 95.85 | 134,201.47 | 128,320.44 | 95.62 |
| 2008 | 1,779,897,750.00 | 1,585,120,640.00 | 89.06 | 146,254.94 | 144,347.25 | 98.74 |

**የጉምሩክ ስነ-ሥርዓት አሠራር ፍሰት ስዕላዊ መግለጫ፤**

12.የጉምሩክ ስነ ሥርዓት (የትራንዚት ፤የዕቃ አወጣጥ እና መጋዘን)አሠራርና አፈጻጸም የአሠራር ሂደት (Process Description) በአባሪ 3 ተያይዟል፡፡

**የኦዲቱ አላማ**

13. የክዋኔ ኦዲቱ አላማ የጉምሩክ ሥነ-ሥርዓት አፈጻጸምን በተመለከተ ስራውን ለማስፈጸም የወጡ ሕጎችና ደንቦች ላይ በመመስረት ባለስልጣኑ ያወጣቸውን መመሪያዎችና የገባቸውን አለምአቀፍና አገር አቀፍ ስምምነቶች በተቀላጠፈና ውጤታማ በሆነ መንገድ ተግባራዊ ለማድረግ የሚያስችል የአሰራር ሥርዓት መዘርጋቱን እና የተዘረጋው የአሰራር ሥርዓት ተፈፃሚ መደረጉን ማረጋገጥ ሲሆን በዚህ ጉዳይ ላይ የአሠራር ግድፈቶች ካሉ መንስኤያቸውን በመለየት የማሻሻያ ሀሣብ ማቅረብ ነው፡፡

**የኦዲቱ የትኩረት አቅጣጫዎች (Audit Issues)**

14. ከላይ የተገለጸውን የኦዲት አላማ ለማከናወን የሚያስችሉ ሦስት የኦዲት ትኩረት አቅጣጫዎች /Audit Issues/ እና ሁለት ንዑስ የኦዲት ትኩረት አቅጣጫዎች /Audit Sub Issues/ ተቀምጠዋል፡፡ እነሱም ፡-

1. በባለስልጣኑ የተዘረጋው የጉምሩክ የትራንዚት ሥነ-ስርዓት በሁሉም የጉምሩክ መቆጣጠሪያ ጣቢያዎች ተግባራዊ መደረጉን ማረጋገጥ፤
2. በባለስልጣኑ የተዘረጋው የጉምሩክ ዕቃ አወጣጥና የመጋዘን አሠራር ስርዓት ቀልጣፋ እና ውጤታማ መሆኑን መገምገም፤
    - 2.1. የጉምሩክ ዕቃ አወጣጥ ሥነ-ሥርዓት በብቃት እና በቅልጥፍና የሚከናወን መሆኑን ማረጋገጥ፤
    - 2.2. የጉምሩክ መጋዘን ሥነ-ሥርዓት አፈጻጸም ውጤታማ እና ቀልጣፋ መሆኑን ማረጋገጥ፤
3. ባለስልጣኑ ብቁና የተሟላ የሰው ኃይል ፣ በዘመናዊ ቴክኖሎጂ የታገዘ የመረጃ አጠቃቀም ፣ አያያዝ እና ልውውጥ ያለው መሆኑን እንዲሁም ከባለድርሻ አካላት ጋር በቅንጅት የሚሰራበት የአሰራር ሥርዓት የዘረጋ እና ተግባራዊ ያደረገ መሆኑን መገምገም የሚሉ ናቸው፡፡

**የኦዲቱ መመዘኛ መስፈርቶች**

15. የኦዲት ቡድኑ ከላይ የተገለጹትን ሦስት የኦዲት የትኩረት አቅጣጫዎች እና ሁለት ንዑስ የትኩረት አቅጣጫዎችን ኦዲት ለማድረግ እንዲያስችል 30 የኦዲት መመዘኛ መስፈርቶች ተዘጋጅተው በባለስልጣኑ አስተያየት ተሰጥቶባቸዋል፡፡የኦዲት መመዘኛ መስፈርቶች በአባሪ 2 ተያይዟል፡፡

**የኦዲቱ ወሰን እና ዘዴ**

16. ኦዲቱ የተከናወነው የመንግሥት መ/ቤቶችን የክዋኔ ኦዲት ለማድረግ ለመሥሪያ ቤታችን በአዋጅ ቁጥር 982/2008 በተሰጠው ሥልጣን የኢትዮጵያ የክዋኔ ኦዲት ደረጃዎች (Ethiopian Performance Audit Standards) መሠረት ሲሆን በኦዲቱ የሚሸፈነው ጊዜ ከ2006-2008 በጀት ዓመት በኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን የጉምሩክ ሥነ-ሥርዓት አፈጻጸምን በተመለከተ በተሰሩ ስራዎች ላይ ነው፡፡ ኦዲቱ በዋናነት የተከናወነው በባለስልጣኑ ዋና መ/ቤት ሲሆን በናሙና በተመረጡ ቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች (በአዲስ አበባ ቃሊቲ ጉምሩክ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት፣በአዲስ አበባ ኤርፖርት ጉምሩክ ቅ/ጽ/ቤት ፣ በሞጆ ጉምሩክ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት፣በአዳማ ጉምሩክ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት እና በጋላፊ ጉምሩክ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት) ፣ባለድርሻ አካላት ጋር ከኢትዮጵያ ባህር ትራንስፖርት ሎጅስቲክስ አገልግሎት ድርጅት፣ከግል የጉምሩክ አስተላላፊዎች እና የግል ቦንድድ መጋዘን ከተፈቀደላቸው ድርጅቶች በመገኘት ከኦዲት አካባቢው ጋር ተያያዥነት ያላቸውን ማስረጃዎች በመከለስና ጉዳዩ ለሚመለከታቸው የሥራ ኃላፊዎች ቃለ-መጠይቅ በማቅረብ እና በአካል ምልከታ ማስረጃ የመሰብሰብ ስራ ተከናውኗል፡፡

## ክፍል ሁለት

## የኦዲት ግኝቶች

**ሀ. በባለስልጣኑ የተዘረጋው የጉምሩክ የትራንዚት ሥነ-ስርዓት በሁሉም የጉምሩክ መቆጣጠሪያ ጣቢያዎች ተግባራዊ መደረጉን በተመለከተ፣**

**ጭነቶች የትራንዚት ፈቃድ የተሰጣቸው መስፈርቱን አሟልተው ስለመሆኑ እና እንቅስቃሴ ከመጀመራቸው በፊት የትራንዚት ስነ ስርዓት መፈጸሙን ማረጋገጥ በተመለከተ፣**

17. ባለስልጣን መ/ቤቱ በዓለም አቀፍ ደረጃ ለሚታወቁ የጉምሩክ ትራንዚት ዓይነቶች ፍቃድ ከመስጠቱ በፊት በመመሪያው የተቀመጡትን መስፈርቶች ያሟሉ ስለመሆናቸው ፣በትራንዚት የተመዘገበ ዕቃ እንቅስቃሴውን ከመጀመሩ በፊት የጉምሩክ ትራንዚት ስነ ሥርዓት መፈጸሙን እና የጉምሩክ ትራንዚት መነሻ ቦታዎች ወይም ጣቢያዎች የእቃውን ትክክለኛነት ሲጫን በአካል ተገኝቶ በማረጋገጥ በሲል ማሸግና ሲል ቁጥሩን በአውቶሜሽን ሲስተም በመመዝገብ የትራንዚት ፈቃድ አዘጋጅቶ በመስጠት ትራንዚቱ እንዲጀምር ሊያደርጉ ይገባል፡፡

18. የገቢ ዕቃዎች ትራንዚት ላይ በቃሊቲ ጉምሩክ የዘርፍ አስመጪነት ፍቃድ ሳይኖራቸው የባንክ ፈቃድ አግኝተው ቀረጥ እና ታክስ ከፍለው እቃ ወደ ሀገር ለማስገባት የሚጠየቅበት ሁኔታ መኖሩ እንዲሁም ከሚመለከታቸው አካላት (ንግድ ሚኒስቴር እና ብሄራዊ ባንክ) ጋር ውይይት ተደርጎ እልባት እንዲኖረው አለመደረጉ እና የዘርፍ አስመጭነት በአገልግሎት አሰጣጡ ላይ አሉታዊ ተጽእኖ እያስከተለ መሆኑ ያለዘርፍ አስመጭነት እቃዎችን ያስመጡ 34 አስመጭዎች ዝርዝር በአባሪ 1 ተያይዟል፡፡ በተጨማሪም ነዳጅ ጭነው ወደ አገር ውስጥ ለሚገቡ ተሽከርካሪዎች ዲክላራሲዮን እና የመንገድ ወረቀት (T1) የማይዘጋጅ መሆኑና የአሰራር ስርዓት እንደሌለው በኦዲት ወቅት ከተከለሱ ማስረጃዎች ለማወቅ ተችሏል፡፡

19. በሌላ መልኩ የወጪ ዕቃዎች የትራንዚት አሰራር ላይ ለወጪ እቃዎች ከሚጠየቁ ቅድመ ሁኔታዎች መካከል የወጪ ትራንዚት ዲክላራሲዮን( Ex 8) ስራ ላይ አለመዋሉን በኦዲቱ ወቅት ለማወቅ ተችሏል፡፡

20. በኦዲት ወቅት በናሙና ከታዩ ቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች መካከል አዲስ አበባ ቃሊቲ እና አዳማ ገቢዎችና ጉምሩክ ቅ/ጽ/ቤቶች የወጪ ትራንዚት እቃ ትክክለኛነት ሲጫን በአካል ተገኝቶ በማረጋገጥ በሲል ማሸግ እና ሲል ቁጥሩን በአውቶሜሽን ሲስተም በመመዝገብ ትራንዚቱ

እንዲጀምር የሚያደርግ አሰራር ተግባራዊ እንዳልተደረገ በቃለ-መጠይቅ እና በአካል ምልከታ ለማወቅ ተችሏል፡፡

21. ነዳጅ ለጫኑ ተሽከርካሪዎች የመንገድ ወረቀት T1 አለመዘጋጀቱን አስመልክቶ የባለስልጣኑ የሚመለከታቸው ኃላፊዎች በሰጡት ምላሽ የኢትዮጵያ ነዳጅ ድርጅት የሚያዘጋጀው ፎርም የጉምሩክ የመንገድ ወረቀት የሚይዘውን መረጃ ስለሚይዝ በዚህ ፎርም ተገልጋዮች እንደሚጠቀሙ ገልጸው ፣ የገቢ ዕቃዎች ትራንዚት ዲክላራሲዮን እና የመንገድ ወረቀት ይዘጋጅ ቢባል ግን አገሪቱ የምታወጣው ተጨማሪ ወጪ ከፍተኛ በመሆኑ ዲክላራሲዮን እና የመንገድ ወረቀት መዘጋጀት እንደሌለበት ከበላይ አካል በተላለፈ የውሳኔ ሃሳብ መሰረት ተግባራዊ አላደረግነውም የሚል ምላሽ ሰጥተዋል፡፡

22. ባለስልጣን መስሪያ ቤቱ ለቀረበለት የኦዲቱ ነባራዊ ሁኔታ መግለጫ በሰጠው መልስ በመልቲሞዳል ስርዓት በአስመጪዎች የዘርፍ አስመጪነት ፍቃድ ሳይኖራቸው ያስመጧቸው ዕቃዎች አገር ውስጥ ባሉ ደረቅ ወደቦች እና ጅቡቲ ወደብ ላይ የሚገኙ ስላሉ ከዘርፍ አስመጭነት ጋር ያለው ችግር አሁንም ያልተፈታ መሆኑ፤ነዳጅን በተመለከተ የነዳጅ አሰራር ስርዐት የጉምሩክ ሰራተኛ ተመድቦ እንዲቆጣጠር ተደርጎ በየወሩ ከጅቡቲ ጉምሩክ ሪፖርት እየደረሰ እንደሚገኝ እና ይህ አሰራር ክፍተት ያለበት ቢሆንም እንደሌሎች እቃዎች ዲክላራሲዮን እንዲዘጋጅ ማድረግ በጅቡቲ ዲክላራሲዮን ለማዘጋጀት እና እያንዳንዱን ጭነት ለማሸግ በጅቡቲ መንግስት የሚጠየቅ ክፍያ በመኖሩ እና ይህ ዘርፍ ከወጪ እና ከአገልግሎት አንጻር በህብረተሰቡ ላይ የሚያመጣውን ጫና ለመቀነስ በማሰብ የተደረገ መሆኑን እና በቀጣይ በጥናት ተደግፎ አገልግሎት አሰጣጡን እና ወጪን ያገናዘበ አሰራር እየተሰራ መሆኑን ፣የወጪ ትራንዚት ዲክላራሲዮን Ex 8 የሚጠየቀውን ቅድመ ሁኔታ በተመለከተ የወጪ እቃ ትራንዚት አለምአቀፍ አሰራር ቢሆንም አሁን ያለው ሲስተም (አሲኩዳ) ውስንነት ያለው በመሆኑ ለወደፊቱ ይህን የሚቀይር ሲስተም በመልማት ላይ መሆኑ ተገልጿል፡፡

23. ሆኖም ግን የትራንዚት ዲክላራሲዮን እና የመንገድ ወረቀት ነዳጅ ለጫኑ ተሽከርካሪዎች ተግባራዊ እንዳይደረግ የተላለፈበት የውሳኔ ሃሳብ ሰነድ እንዲቀርብ ተጠይቆ ሊቀርብ አልቻለም፣በተጨማሪም በ2008 በጀት ዓመት ከዋናው መ/ቤት እና ከሚመለከታቸው ቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች ከመጡ የጉምሩክ ስነ ሥርዓት የስራ ሂደት መሪዎችና የትራንዚት ቡድን አስተባባሪዎች ጋር በተደረገ ውይይት በትራንዚት ዙሪያ ከተለዩ ችግሮች መካከል በጋላፊ ጉምሩክ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት ነዳጅን በተመለከተ የአሰራር ስርዓት ባይኖረውም

መረጃዎችን በአግባቡ መዝግቦና አደራጅቶ አለመያዝ፣LPG( Liquefied Petroleum Gas ) በተመለከተ ሁሉም አስመጭዎች በጅቡቲ የኢትዮጵያ ጉምሩክ ማስተባበሪያ ጽ/ቤት የመንገድ ወረቀት አሰርቶ እንዲወጣ የሚል ቢተላለፍም የመንገድ ወረቀት ሳይዙ ሲመጡ ማሳለፍ እና በዋናው መ/ቤት ደረጃ የነዳጅ አሰራር ስርዓት ለመዘርጋት ተጀምሮ አለመጠናቀቁ በመግቢያ በሮች ላይ ከፍተኛ ችግር እየፈጠረ መሆኑ በመገለጹ በባለስልጣኑ ኃላፊዎች የተሰጠው ምላሽ አጥጋቢ ሆኖ አልተገኘም፡፡

24. የትራንዚት ዕቃዎች በመመሪያ እና በአሰራር ላይ የተቀመጡ መስፈርቶችን ሳያሟሉ ወደ አገር እንዲገቡ እና እንዲወጡ ማድረግ የትራንዚት ቁጥጥሩን ደካማ የሚያደርግ ከመሆኑም በላይ መንግስት ከገቢና ወጪ ዕቃዎች ላይ መሰብሰብ የሚገባውን ቀረጥና ታክስ ሊያሳጣ የሚችል ከመሆኑም በተጨማሪ አሰራሩ ለህገወጥ ዕቃዎች ዝውውር በር ስለሚከፍት ተገቢ ሆኖ አልተገኘም፡፡

**ትራንዚት ላይ ያሉ ጭነቶች በጉምሩክ ማሸጊያ መታሸጋቸውን እና በታሸጉበት ሁኔታ መድረሳቸውን ማረጋገጥ በተመለከተ፣**

25. ባለስልጣን መ/ቤቱ ታሽገውና ሳይታሸጉ የሚጓጓዙ የትራንዚት እቃዎችን በጉምሩክ ትራንዚት ሥነ-ሥርዓት አፈፃፀም መመሪያ ላይ በተቀመጠው መስፈርት መሰረት በመለየት መታሸግ የሚገባቸው እቃዎች በጉምሩክ ማሸጊያ መታሸጋቸውን እና በታሸጉበት ሁኔታ መድረሳቸውን ሊያረጋግጥ ይገባል፡፡

26. ባለስልጣኑ የሚጠቀምባቸው የጉምሩክ ማሸጊያዎች ወይም ልዩ ምልክቶች ማሟላት ከሚገባቸው መስፈርቶች መካከል ጠንካራ አስተማማኝና ለረጅም ጊዜ የሚቆይ፣ በቀላሉ ለመቆለፍና ለማሸግ የሚቻል፣ በቀላሉ ለማንበብና ለመለየት የሚቻል፣ ካልተሰበረ ወይም ካልተነሳ በስተቀር እቃ ለማውጣትም ሆነ ለማስገባት የማያስችል፣ ከአንድ ጊዜ በላይ አገልግሎት የማይሰጥ (ኤሌክትሮኒክ ሲል ካልሆነ በስተቀር)፣ አስመስሎ ለመስራት የማይቻል፣ የጉምሩክ ማሸጊያ ወይም ልዩ ምልክት መሆኑን ለማመላከት በእንግሊዝኛ ''CUSTOMS'' የሚል ጽሑፍ የተጻፈበት፣ እሽጋ የሚያደርገዉ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት ኮድና ተከታታይ ቁጥር ያለው፣ ለማሸግ ወይም ለመቆለፍ አመች የሆነ እና አደጋን መቋቋም ከሚችል ማቴሪያል የተሰራ ሊሆን እንደሚገባው ተገልጿል፡፡

27. በኦዲት ወቅት ከተከለሱ ማስረጃዎች በሀገር ውስጥ ተመርተው ወይንም እሴት ተጨምሮባቸው ለውጭ ገበያ የሚላኩ ምርቶችን በሚመለከት የጉምሩክ ስነ ስርዓት ለመፈጸም የማሸጊያ ሲል መጠቀም የግድ አስፈላጊ ቅድመ ሁኔታ እንደሆነ፣ሆኖም ምርቶቹ

የሚታሸጉበት ደረጃውን የጠበቀ ማሸጊያ /ሲል/ ግዥ ለመፈጸም በ2007 በጀት አመት ግልጽ ጨረታ በማውጣት ግዥ ለመፈጸም ተሞክሮ ባለመሳካቱ ያለው የማሸጊያ ሲል በማለቁ ህገ ወጥነትን ለመቆጣጠር በማይቻልበት መንገድ በሽቦ ብቻ እየታሰረ ወደ ውጭ እየተላከ እንደሚገኝ ለማወቅ ተችሏል፡፡

28.በኦዲት ወቅት በናሙና ተመርጠው ከታዩ ቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች መካከል በአዲስ አበባ ቃሊቲ ጉምሩክ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት በኮንቴይነር ለሚጓጓዙ ጭነቶች በሽራ ታሽገው ለሚጓጓዙ ጭነቶች ተብሎ የተዘጋጀውን ሽቦ እና ጠጠር እንደሚጠቀሙ ነገር ግን ሽቦ እና ጠጠር ለኮንቴይነር እንደማይሆን በተጨማሪም ለውጭ ገበያ የሚላኩ ዕቃዎች የሚታሸጉበት ደረጃውን የጠበቀ ማሸጊያ አለመኖሩን ጠቅሰው ከ2006 ዓመተ ምህረት ጀምሮ ጥያቄ ቢቀርብም ግዥው የሚፈጸመው በአለም አቀፍ ግዥ ሂደት በመሆኑ ጊዜ የሚጠይቅ መሆኑን በቃል እንደተገለጸላቸው፤ ደረጃውን የጠበቀ ማሸጊያ እስኪገዛ ጥቅም ላይ የዋለው መጨፍለቂያ በተደጋጋሚ ለብልሽት የሚዳረግ በመሆኑ በአገልግሎት አሰጣጡ ላይ ከፍተኛ ጫና ከመፍጠሩም ባሻገር የቅርንጫፍ ጽ/ቤቱን መለያ በግልጽ ስለማያወጣ ለፎርጅድ እጅጉን የተጋለጠ መሆኑን ገልጸው ትኩረት እና ቅድሚያ ተሰጥቶ ደረጃውን የጠበቀ ማሸጊያ እንዲገዛላቸው ለዋናው መ/ቤት የጠየቁ መሆኑን በኦዲት ወቅት ከተከለሱ ማስረጃዎች እና በአካል ምልከታ ለማወቅ ተችሏል፡፡፡

29.በሞጆ ጉምሩክ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት ተጓጉዘው የሚደርሱ ጭነቶች የኮንቴነሮች የሲል ልዩነት በተደጋጋሚ የሚከሰት መሆኑን፣የሲል አስተሻሸግ ልዩነት እና በአንድ ተሽከርካሪ ሁለት ኮንቴነሮች ተጭነው በሚመጡበት ሰአት የጉምሩክ ሲል ቁጥራቸው እየተዟዟረ የሚታሸግ መሆኑን በዚህም ምክንያት በአገልግሎት አሰጣጥ ላይ አሉታዊ ተጽእኖ እያስከተለ እንደሚገኝ እና የጉምሩክ ሲል ከመነሻ ጣቢያው በአግባቡ ስለመታሸጉ ክትትል እንዲደረግ ቢጠየቅም ችግሩ የቀጠለ መሆኑን በኦዲት ወቅት ከተከለሱ ማስረጃዎች ለማወቅ ተችሏል፡፡

30. በአዲስ አበባ ቃሊቲ ጉምሩክ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት በተለያየ ጊዜያት ወደ አገር የገቡ የዩኒ ሞዳልና የመልቲ ሞዳል ተሽከርካሪዎች የጫኑት ኮንቴነር ከመግቢያ በር ጀምሮ እስከ አቃቂ መቆጣጠሪያ ጣቢያ የሲል ቁጥር ልዩነት ወይም የሲል መቆረጥ መኖሩ ምንም ሪማርክ ሳይጻፍበት ቅርንጫፍ ጽ/ቤቱ እየደረሰ መሆኑ፣በአዲስ አበባ ዙሪያ የውጭ ፍተሻ ፈቃድ ያገኙ ድርጅቶች ጭነት በመጋዘናቸው በሚደርስበት ሰዓት ስራው በትራንዚት ኢንስፔክሽን ስለማይሰራ ጥንቃቄ እንዲደረግ መገለጹን እና የሲል ቁጥር ልዩነት መኖሩን በኦዲት ወቅት ከተከለሱ ማስረጃዎች ለማወቅ ተችሏል፡፡

31.ባለስልጣን መስሪያ ቤቱ ለቀረበለት የኦዲቱ ነባራዊ ሁኔታ መግለጫ በሰጠው መልስ በሽራ ለሚጓጓዙ ጭነቶች ተብሎ የተዘጋጀውን ሽቦ እና ጠጠር በኮንቴይነር በሚወጡ ወጪ እቃዎች መጠቀም በተመለከተ ደረጃውን የጠበቀ ማሸጊያ ግዥ በመንግስት ግዥና ንብረት ማስወገድ አገልግሎት እስኪገዛ ድረስ ጭነቶች ሳይታሸጉ ከሚወጡ በሚል እየተሰራበት ያለ መሆኑ ተገልጿል፡፡

32.የትራንዚት ዕቃዎች የማሸጊያ ሲል ቁጥር ልዩነት መከሰት ስራዎች በስጋት ስራ አመራር መርህ መሰረት እንዳይሰሩ እና ለትራንዚት ሂደቱ መጓተት አሉታዊ አስተዋጽኦ እንደሚያበረክት እንዲሁም በትራንዚት ላይ ያሉ ዕቃዎች ደረጃውን በጠበቀ የጉምሩክ ማሸጊያ የማይታሸጉ ከሆነ ህገ ወጥነትን ለመቆጣጠር እና ለመከላከል የሚደረጉትን ስራዎች አስቸጋሪ እንዲሆኑ ያደርጋል፡፡

**የትራንዚት ሂደታቸውን ያጠናቀቁ ጭነቶች በተነሱበት ሁኔታ እና የጊዜ ገደብ መድረሳቸውን እና በጊዜ ገደቡ የደረሱና ያልደረሱትን የትራንዚት እቃዎች በሲስተም የማጣራትና የማስታረቅ ስራ ስለመሰራቱ፣**

33.የትራንዚት እቃዎች በተነሱበት ሁኔታ እና በተቀመጠው የጊዜ ገደብ መሰረት የደረሱ ስለመሆኑ ሊያረጋግጥ እና በጊዜ ገደቡ የደረሱና ያልደረሱትን እቃዎች በሲስተም የማጣራትና የማስታረቅ (Reconciliation) ስራ በመስራት በጊዜ ያልደረሱትን ወደ ህግ ማስከበር በማስተላለፍ ክትትል እንዲደረግባቸ ሊያደረግ ይገባል፡፡

34.በኦዲቱ ወቅት በናሙና ተመርጠው ከታዩ ቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች መካከል በመልቲሞዳል ስርአት ተጓጉዘው ቃሊቲ ገቢዎች እና ጉምሩክ ቅ/ጽ/ቤት መድረስ የነበረባቸው ጭነቶች ከ2006-2008 ዓ.ም 1,365 ኮንቴይነሮች እና ሞጆ ገቢዎች እና ጉምሩክ ቅ/ጽ/ቤት ከተጀመረበት ጀምሮ መግባት የነበረባቸው ጭነቶች 2,647 ኮንቴይነሮች በቅርንጫፍ ጽ/ቤቶቹ መድረሳቸው በሲስተም ቫሊዴት አለመደረጉ በቃለ-መጠይቅ እና ከቀረቡ ማስረጃዎች ለማወቅ ተችሏል፡፡

35.በተጨማሪም እ.ኤ.አ ከ2013 እስከ 2016 በሚሌ ጉምሩክ ቅ/ጽ/ቤት 1,576፣አዳማ ጉምሩክ ቅ/ጽ/ቤት 279፣ሞያሌ ጉምሩክ ቅ/ጽ/ቤት 9፣ጅማ ገቢዎችና ጉምሩክ ቅ/ጽ/ቤት 28 እና መቀሌ ገቢዎችና ጉምሩክ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት 239 የመልቲ ሞዳል ጭነቶች በቅርንጫፍ ጽ/ቤቶቹ መድረሳቸው በሲስተም ቫሊዴት አለመደረጉ በኦዲት ወቅት ከተከለሱ መረጃዎች ለማወቅ ተችሏል፡፡

36.በመልቲ ሞዳል ትራንስፖርት ስርአት ተጓጉዘው ወደ ተፈቀደ መጋዘን (bonded warehouse) የሚራገፉ ጭነቶች የማጓጓዣ ሰነድ ሲዘጋጅላቸው መድረሻቸው መጋዘኑን በሚቆጣጠረው ቅ/ጽ/ቤት አድራሻ ስም መዘጋጀትና መላክ ሲገባቸው በሞጆ ጉምሩክ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት ስም ተመዝግበው መላካቸው ፣ በዚህም ምክንያት ጭነቶች ወደ ሀገር ስለመግባታቸው ማረጋገጥ ባለመቻሉ እና በአሲኩዳ ሲስተም የትራንዚት ጭነት ሰነዶች ያልተዘጉ በመሆናቸው መፍትሄ እንዲቀመጥለት ለዋናው መ/ቤት በደብዳቤ የተጠየቀ ቢሆንም ችግሩ እንደቀጠለ መሆኑን፣ ኮንቴይነሮቹ የት እንደተራገፉ ከአጓጓዥ ድርጅቱ የኢትዮጵያ ባህር ትራንስፖርት ሎጀስቲክስ አገልግሎት ድርጅት መረጃውን ለማግኘት ግልጽ የሆነ አቅጣጫ ያልተቀመጠ መሆኑን እና በባለስልጣኑ ስር ባሉ ቅ/ጽ/ቤቶች በደብዳቤ ለተጠየቁ ምላሾች ጊዜ ወሳጅ በመሆናቸው የትራንዚት ጭነት ሰነዶችን በሲስተም ለመዝጋት የተቸገሩ መሆኑን ከሞጆ ገቢዎችና ጉምሩክ ቅ/ጽ/ቤት የጉምሩክ ጉዳዮች የስራ ሂደት ለባለስልጣን መ/ቤቱ የጉምሩክ ፕሮግራም ልማት ድጋፍ ስራዎች ዘርፍ ከተጻፈ ደብዳቤ ለማወቅ ተችሏል፡፡

37.ጉዳዩ የሚመለከታቸው የገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን መ/ቤት ኃላፊዎች ሲመልሱ የችግሩ መንስኤ የሆኑት ቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች ፈቃድ ከሰጧቸው የቦንድድ መጋዘኖች መረጃ ተከታትሎ የማስታረቅ ስራ ባለመስራታቸው የመረጃ ክፍተት መፍጠሩ፤ ቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች በስህተት ቅርንጫፍ ጽ/ቤታቸው የደረሱ እቃዎችን ወደ ትክክለኛው መዳረሻ ጣቢያ ሳይልኩ በራሳቸው ቅርንጫፍ ጽ/ቤት ማስተናገዳቸው መሆኑን ገልጸው ችግሩን ለመፍታት በሁሉም ቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች ያሉ የትራንዚት ቡድን አስተባባሪዎችን ጠርተው እንዳወያዮ እና በጋራ የውይይት መድረክ አሰራራቸው መሰረት ተወያይተው ችግሮቹን ለይተው ለማስተካከል ወደ ተግባር እንደገቡ ገልጸዋል፡፡

38. በሌላ በኩል የመልቲ ሞዳል ስርዓት ኦፕሬተር የሆነው የኢትዮጵያ ባህር ትራንስፖርት ሎጅስቲክስ አገልግሎት ድርጅት የመልቲሞዳል ኦፕሬሽን መምርያ ዳይሬክተር፣ ከመልቲሞዳል ስርዓት ጋር ተያይዞ ከሚነሱ ችግሮች መካከል የጭነቶች መዳረሻ ቦታ ስህተት፤የሲል ቁጥር ልዮነት፤ለአስመጪዎች/ወኪሎች እቃው ወደብ እና ተርሚናል መድረሱን በወቅቱ አለማሳወቅ እና እቃዎች የት ቅርንጫፍ ጽ/ቤት እንደተራገፉ በደብዳቤ እንዲያረጋግጡ ሲጠየቅ ወቅታዊ ምላሽ አለመስጠት እንደሚጠቀሱ ተገልጾ በኦዲት ቡድኑ ለቀረበላቸው ጥያቄ ሲመልሱ ችግሮች እንዳሉ በድርጅቱ እንደሚታወቅ ገልጸው በችግሮቹ ዙርያ በተደጋጋሚ ከባለስልጣን መ/ቤቱ ጋር እንደተወያዮ ገልጸው ከባለስልጣኑ የሚላኩ

መረጃዎች ምላሽ እንደሚሰጣቸው ነገር ግን በተለያየ ምክንያት (ቢል ኦፍ ሎዲንግ እና ሻንሲ ቁጥር) ባለመገለጹ ምላሽ ያልተሰጣቸው መረጃዎች እንደሚኖሩ ገልጸው ችግሩን ለመፍታት የሪኮንሲሊዮሽን ስራዎች እየተሰሩ መሆናቸውን ገልጸዋል፡፡

39.ባለስልጣን መስሪያ ቤቱ ለቀረበለት የኦዲቱ ነባራዊ ሁኔታ መግለጫ በሰጠው ምላሽ በመልቲሞዳል ስርአት ተጓጉዘው ቃሊቲ ገቢዎችና ጉምሩክ ቅ/ጽ/ቤት መድረስ ከነበረባቸው ጭነቶች ውስጥ ከ2006-2008 ዓ.ም ብዛት 1,365 ኮንቴይነሮች ለኢትዮጵያ ባህር ትራንስፖርት ሎጀስቲክስ አገልግሎት ድርጅት(ኢ.ባ.ት.ሎ.አ.ድ) ሪፖርት የተደረጉ ቢሆንም የኢ.ባ.ት.ሎ.አ.ድ የመልቲሞዳል ኦፕሬሽን መምሪያ ዳይሬክተር 1,078 ኮንቴይነሮች የተራገፉበት ቦታ ዝርዝር በማሳወቅ በቀሪዎቹ ላይ መረጃ የማጥራት ስራ እየተሰራ መሆኑ ግምት ውስጥ ሊገባ ይገባል፡፡ በተጨማሪም 2,647 ኮንቴይነር በሲስተም መድረሻ ሞጆ ጉምሩክ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት ቢልም በወቅቱ ከመልቲሞዳል መጀመር ጋር በተያያዘ እቃዎቹ በተለያየ ቅ/ጽ/ቤቶች እንደተራገፊ ታሳቢ የሚደረግ በመሆኑ ከመረጃ ቴክኖሎጂ ዳይሬክቶሬት የክሊራንስ ዲክላራሲዮን መረጃ እንዲቀርብ በማድረግ በማጥራት ሂደት ላይ በአሁን ወቅት ካለው የቁጥጥር ስርዐት እና ከትግበራ ሂደት ጋር በተያያዘ ያልታረቁ ኮንቴይነሮች ቁጥር በከፍተኛ ሁኔታ እየቀነሰ መሆኑን ገልጸዋል፡፡

40.የመልቲ ሞዳል ጭነቶች ቀረጥና ታክስ የሚሰበሰበው እቃዎች አገር ውስጥ ከገቡ በኂላ በመሆኑ ጭነቶች የት እንደተራገፉ በወቅቱ ማረጋገጥ ካልተቻለ በመንግስት መሰብሰብ የሚገባው ቀረጥና ታክስ እንዳይሰበሰብ ፣ የኮንትሮባንድ አሰራር እንዲስፋፋ እንዲሁም ጭነቶች የትራንዚት ሂደታቸውን ሳያጠናቅቁ ዕቃዎች እንዲለቀቁ የሚያደርግ አሰራር ስለሚፈጥር የትራንዚት ስርዓቱን ያላጠናቀቁ ዕቃዎች ላይ አስፈላጊው እርምጃ እንዳይወሰድ ሊያደርግ ይችላል፡፡

**የጉምሩክ ትራንዚት ስነ-ሥርዓት በዘመናዊ የመረጃ ቴክኖሎጂ እና በስጋት ስራ አመራር አሰራር ስርዓት መሰረት እየተከናወነ መሆኑን በተመለከተ፣**

41.በባለስልጣኑ የጉምሩክ ትራንዚት ስነ-ሥርዓት በዘመናዊ የመረጃ ቴክኖሎጂ እና በስጋት ስራ አመራር አሰራር ስርዓት መሰረት ሊከናወን ይገባል፡፡

42.ባለስልጣኑ የኤሌክትሮኒክስ የጭነት መቆጣጠሪያ መሳሪያዎችን ወጪና ገቢ ዕቃዎች በሚያጓጉዙ ተሽከርካሪዎች ስለመጠቀም የወጣ መመሪያ ቁጥር 73/2004 አንቀጽ 4/1 ማንኛውም ተጠቃሚ ተሽከርካሪውን ለወጪና ገቢ ዕቃዎች ማጓጓዝ ተግባር በሚያውልበት ወቅት መሳሪያውን የመጠቀም ግዴታ እንዳለበት ተቀምጧል በተጨማሪም በባለስልጣኑ

ከ2005 ዓ.ም ጀምሮ የተተገበረው የጉምሩክ አሰራር ስርዓት በትራንዚት ላይ ያለ ዕቃ ቁጥጥር በዘመናዊ ቴክኖሎጂ (cargo scanning, cargo tracking, electronics seal) እና በተጠናከረ ተንቀሳቃሽ ኢንተለጀንስ ዩኒት ቁጥጥር እንደሚደረግበት ታሳቢ ተደርጎ የተቀረጸ ነው፡፡

43. በዚህ መሰረት ባለስልጣኑ የኤሌክትሮኒክስ የጭነት መቆጣጠሪያ ስርዓት (Electronics Cargo Tracking and Monitoring System) ለመዘርጋት ከሀይ.ጅ.ቴክ ካምፓኒ ጋር ጥር 7/2003 ዓ.ም በ2,500,000.00( በሁለት ሚሊየን አምስት መቶ ሺህ የአሜሪካን ዶላር) የውል ዋጋ እና ከውሉ ሁለተኛ አመት ጀምሮ እስከ አምስተኛው ዓመት በየአመቱ ለስራ ማስኬጃ ወጪዎች በሚከፈል 289,000 የአሜሪካን ዶላር ውል ተፈራርሞ በቀጣዮቹ አምስት አመታት ጊዜ ውስጥ በትንሹ 10,000 ተሽከርካሪዎችን ወደ ስርአቱ በማስገባት ወደ ሙሉ ትግበራ እንደሚገባ የውል ስምምነቱ ቢገልጽም እስከ 2008 በጀት አመት መጨረሻ 312 (3%) ተሽከርካሪዎች ብቻ የካርጎ ትራኪንግ መሳሪያ የተገጠመላቸው መሆኑ እና የተዘረጋው የካርጎ ትራኪንግ ሲስተም  ከኢትዮጵያ መግቢያ በር ጋላፊ ጀምሮ ሲሆን ከጅቡቲ ወደብ እስከ ጋላፊ ባለው ስፍራ በውሉ መሰረት ስርአቱ ያልተዘረጋ መሆኑን በኦዲት ወቅት ከተከለሱ ማስረጃዎች ለማወቅ ተችሏል፡፡

44. ባለስልጣኑ በ2007 በጀት ዓመት ስርዓቱን በሙሉ አቅም ለማስጀመር ከትራንስፖርትና መገናኛ ሚኒስቴር እና ከፌዴራል የትራንስፖርት ባለሥልጣን እና  ሌሎች ባለድርሻ አካላትን ያካተተ ዓብይ እና ሙያዊ ድጋፍ የሚሰጥ የቴክኒክ ኮሚቴ ተቋቁሞ በተሽከርካሪዎች ላይ የሚገጠሙትን የኤሌክትሮኒክ ካርጐ ትራኪንግ መሣሪያ አክሰሰሪ አቅራቢዎች ጋር በአክሰሰሪዎች ዋጋ እና በጅቡቲ ኮሪደር ከሚሠሩ ትራንስፖርተሮች ጋር ውይይት ተደርጎ ተሽከርካሪዎቻቸው ወደ ሲስተም እንዲገቡ መግባባት ላይ ተደርሶ ሆኖም ግን  ተግባራዊ አለመደረጉን በኦዲት ወቅት ከተከለሱ መረጃዎች ለማወቅ ተችሏል ፡፡

45. በኦዲቱ ወቅት በናሙና ከታዩ ቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች መካከል በሞጆ ገቢዎችና ጉምሩክ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት ስርዓቱ ያልተጀመረበት ምክንያት በቅርንጫፉ ሀላፊዎች በኩል ስለ ካርጎ ትራኪንግ ስራ በቂ ግንዛቤ አለመኖሩ ፤የሹፌሮች ግንዛቤ ማጣት፤ትራንስፖርተሮች የኤሌክትሮኒክስ ካርጎ ትራኪንግ ጠቀሜታ እና ትርፋማነት አለማወቅ፤በኤሌክትሮኒክስ ካርጎ ትራኪንግ ስራ የተመደቡ ባለሙያዎች ስራ ስላልጀመረ በሚል ምክንያት ሙሉ ለሙሉ ተደራቢ ስራ እየሰሩ ስለሆነ የኤሌክትሮኒክስ ካርጎ ትራኪንግ ክህሎት እና እውቀት ማነስ ለስራው ፍላጎት የማጣት ዝንባሌ እያሳደረባቸው መሆኑ፤ሲስተሙ የተገጠመላቸው

ተሽከርካሪዎች ቴክኒካል ችግር ሲገጥማቸው ተከታታይ አካል አለመኖሩ፤ሲስተሙን ከሚሰራው ድርጅት ጋር የተቀናጀ ስራ አለመስራት፤ሲስተሙ የተገጠመላቸው ተሽከርካሪዎች በወቅቱና በአፋጣኝ አገልግሎት እያገኙ ስላልሆነ ስራው እንዳይሰራላቸው ሽሽት ማሳየታቸው፣

46. በአዳማ ገቢዎችና ጉምሩክ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት በኤሌክትሮኒክስ ካርጎ ትራኪንግ ሲስተም ለሚያጋጥሙ ችግሮች ዋናው መ/ቤት በወቅቱ ምላሽ አለመስጠት፤የካርጎ ትራኪንግ ስራ ከሙከራ ያለፈ ባለመሆኑ በፈጻሚው ስነ-ልቦና ላይ አሉታዊ ተጽእኖ መፍጠሩ እና ጂፒኤስ የተገጠመላቸው ተሽከርካሪዎች ለሙከራ ትግበራ ሲባል ሲስተሙ የታሰረው በተሽከርካሪዎች ጋቢና ጀርባ በመሆኑ ከጉዞ ያለፈ ክትትል ማድረግ የማይቻል መሆኑን ምክንያቱም በዋናው መ/ቤት ለተወሰነ ጊዜ ወደ ስራው ለመግባት ቆርጦ አለመነሳት እንደነበረ እንዲሁም በአዲስ አበባ ቃሊቲ ጉምሩክ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት ወደ ውጪ የሚላኩ ዕቃዎችን በኤሌክትሮኒክስ ካርጎ ትራኪንግ ስርዓት ተቆልፎ (አርም ተደርጎ) እንዲያልፉ አለማድረግ ማለትም ስርዓቱ በተገጠመላቸው ተሽከርካሪዎች ላይ የሚታይ መሆኑን በኦዲቱ ወቅት ከተከለሱ ማስረጃዎች እና በቃለ መጠይቅ ለማወቅ ተችሏል፡፡

47.ስለጉዳዩ በባለስልጣኑ የኤሌክትሮኒክስ ካርጎ ዩኒት ቡድን አስተባባሪ ተጠይቀው ተሽከርካሪዎች ወደ ስርአቱ ያልገቡበት ምክንያት የኤሌክትሮኒክ ካርጎ ትራኪንግ ሲስተም ከተዘረጋ በኋላ ይህንን ሲስተም ከሌላ የፍሊት ማኔጅመንት ሲስተም ጋር እንዲተሳሰር በተወሰነው መሰረት ለማስተሳሰር ጊዜ መውሰዱ፤የቴሌ ኔትወርክ ሽፋን ቶሎ አለመሰራቱ፤ትራንስፖርት ድርጅቶች መኪኖቻቸውን ወደ ስርአቱ ለማስገባት ጊዜ መውሰዳቸው እና ማንተታቸው፤የሲስተሙ ቴክኒካል ችግሮች በፍጥነት አለመፈታት፤አቅራቢ ድርጅቶች መሳሪያውን ለማቅረብ የአቅም ችግር መኖሩ፤የሰው ሀይል በስራ መደቡ ላይ አለመቆየት (በዝውውር እና በመልቀቅ) እና የውሳኔ ሰጪ አካላት መቀያየር ስራው ወደ ሙሉ ትግበራ እንዳይገባ እንቅፋት መፍጠሩን ገልጸዋል፡፡

48.በባለስልጣኑ ከ2005 ዓ.ም ጀምሮ ተግባራዊ በተደረገው የጉምሩክ አሰራር ስርዓት በትራንዚት ላይ ያለ ዕቃ በዘመናዊ ቴክኖሎጂ ቁጥጥር እንደሚደረግበት ታሳቢ ተደርጎ የተቀረጸ ቢሆንም የኤሌክትሮኒክስ የጭነት መቆጣጠሪያ ስርዓት ትግበራ እየተጓተተ በመሆኑ ተቋሙ ከስርአቱ ትግበራ የሚያገኘውን ጥቅም በወቅቱ እና በአፋጣኝ እያገኘ አለመሆኑ፤ የትራንዚት ቁጥጥሩ የላላ፣አገልግሎት አሰጣጡም የተጓተተ እና ለህገወጥ ዕቃዎች ዝውውር የተጋለጠ እንዲሆን የሚያደርግ መሆኑን ለመረዳት ተችሏል ፡፡

**ትራንዚት የጀመሩ ጭነቶች መረጃ ወደ መረጃ ቴክኖሎጂ ቋት መተላለፋቸውን በተመለከተ ፣** ባለስልጣኑ ትራንዚት የጀመሩ ጭነቶችን መረጃ ወደ መረጃ ቴክኖሎጂ ቋት መተላለፋቸውን ሊያረጋግጥ ይገባል፡፡

49.በኦዲት ወቅት በናሙና ተመርጠው ከታዩ ቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች መካከል በጋላፊ ጉምሩክ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት በመልቲ ሞዳል ስርዓት መጥተው በሲስተም ያልተገኙ ሰነዶች ከተስተናገዱ በኂላ ተከታትሎ የመንገድ ወረቀት አለማዘጋጀት እና የተዘጋጀውን የመንገድ ወረቀት ቁጥር ለመድረሻ ጣቢያ አለማሳወቅ ፣ በማንዋል የተሰሩ የመልቲሞዳል ጭነቶች ወደ ሲስተም አለማዞር፤የመልቲሞዳል ጭነቶች ዝርዝር በየእለቱ ከጋላፊ ወደ መድረሻ ጣቢያዎች አለመላክ፤

50. በመግቢያ በር በተለያየ ምክንያት በማንዋል እየተመዘገቡ የተስተናገዱ ጭነቶች ዝርዝር መረጃ ለመረጃ ቴክኖሎጂ ስራ አመራር ዳይሬክቶሬት፤ለዋናው መ/ቤት ትራንዚት ቡድን እና ለመድረሻ ጣቢያዎች በየእለቱ በተሟላ ሁኔታ አለመድረስ፤ሲስተሙ ሲስተካከል በማንዋል የተስተናገዱ ጭነቶችን መረጃ በሲስተም ከስር ከስሩ አለመመዝገብ፤ የመረጃ ቴክኖሎጂ ዳይሬክቶሬትም ከመግቢያ የጉምሩክ ጣቢያዎች መረጃው ሲደርሰው የጅቡቲ ጉምሩክ መረጃ ባለመድረሱ በማንዋል የተስተናገዱ ከሆነ ለጅቡቲ ጉምሩክ አለማሳወቅ፤መረጃው እንዲላክ ክትትል አለማድረግ፤የመድረሻ ጣቢያዎችም ከመግቢያ በር በስማቸው በሲስተም የተመዘገቡ እና በማንዋል የተስተናገዱ ጭነቶች ሲደርሷቸው የትራንዚት መረጃዎችን ሁልግዜ በተሟላ ሁኔታ የማስታረቅ ስራ አለመስራቱ ለትራንዚት ቁጥጥሩ ችግሮች እንደምክንያት የሚጠቀሱ መሆናቸው ከተከለሱ መረጃዎች ለማወቅ ተችሏል፡፡

51.በአዲስ አበባ ኤርፖርት ጉምሩክ ቅ/ጽ/ቤት ወደሀገር ውስጥ ስለሚያስገቧቸው እቃዎች መግለጫ(manfest) የተሟላ መረጃ ከመነሻ ተቀብሎ በሲስተም አለማስገባት እና ወደ ጉምሩክ መረጃ ቋት በወቅቱ አለመላክ ችግሮች መኖራቸውን በኦዲት ወቅት ከተከለሱ መረጃዎች ለማወቅ ተችሏል፡፡

52.መረጃዎች በአግባቡ እና በተደራጀ ሁኔታ ካልተያዙ እና ካልተቀመጡ የትራንዚት ሂደቱን በተቀናጀ መልኩ የቁጥጥር ስራ እንዳይሰራ በሚፈጠረው የአፈጻጸም ክፍተት ምክንያት በገቢ አሰባሰብ ላይም ሆነ ሀገር ውስጥ እንዳይገቡ የተከለከሉ እቃዎችን ዝውውር ከመቆጣጠር አንጻር አሉታዊ ተጽእኖ የሚያሳድር እና ለስነ-ምግባር ችግርም ክፍተት የሚፈጥር በመሆኑ መረጃዎችን በወቅቱ ወደመረጃ ቋት አለማስተላለፍ ተገቢ ሆኖ አላገኘነውም፡፡

**ወደ አገር የሚገቡ እና ከአገር የሚወጡ ዕቃዎችና ማጓጓዣዎች ላይ ስለሚደረግ ፍተሻ እና የጉምሩክ ስነ ስርዓት መፈጸሙን ማረጋገጥ በተመለከተ፣**

53.ባለስልጣን መ/ቤቱ በጉምሩክ ወደቦች ፣ በወሰን አካባቢዎች ፣ በጉምሩክ መቆጣጠሪያ ጣቢያዎችና ማቋረጫ መስመሮች በኩል የሚገቡና የሚወጡ እቃዎችንና ማጓጓዣዎችን ሊፈትሽና የጉሙሩክ ስነ-ስርዓት ተፈጽሞባቸው መግባታቸውንና መውጣታቸውን ሊያረጋግጥ ይገባል፡፡

54. ወደ አገር የሚገቡና የሚወጡ ዕቃዎች ላይ የሚደረገውን ቁጥጥር ለማጠናከርና አገልግሎት አሰጣጡን ለማቀላጠፍ በዘመናዊ ቴክኖሎጂ የተደገፈ የካርጎ ስካኒንግ ፍተሻ ሥርዓት ለመዘርጋት ባለስልጣን መ/ቤቱ በስምንት የጉምሩክ መቆጣጠሪያ ጣቢያዎች (ሞያሌ፣ሞጆ፣ ሁመራ፣ ቶጎጫሌ፣ ያቤሎ ፣መተማ፣ ጋላፊ እና ጅግጅጋ) ላይ ለኤሌክትሮኒክስ ካርጎ ፍተሻ መሳሪያ (Scanning machine) ተያያዥ የቤትና የአስፋልት ግንባታ በ53 ሚሊዮን ብር በሶስት ወራት ውስጥ አጠናቆ እንዲያስረክብ ከኢትዮጵያ ብረታብረት እና ኢንጅነሪንግ ኮርፖሬሽን ጋር የካቲት 1/2003 ዓ.ም ውል ተፈራርሞ ወደ ስራ የተገባ ቢሆንም ከስምንቱ መቆጣጠሪያ ጣቢያዎች ውስጥ የያቢሎ መቆጣጠሪያ ጣቢያ ለሞያሌ ቅርብ ስለሆነ መገንባቱ አስፈላጊ አይደለም ግንባታው ወደ ቃሊቲ ይዛወር ተብሎ መቅረቱን፣ ነገር ግን ቃሊቲም ላይ ግንባታው አለመከናወኑ ፣የጋላፊ መቆጣጠሪያ ጣቢያን በተመለከተ ግንባታው ተጠናቆ ከ2005 ዓ.ም ጀምሮ የካርጎ ስካኒንግ ፍተሻ አገልግሎት ወደ ስራ ቢገባም በመንገዱ ፣በህንጻው ላይ በታዩ የግንባታ ችግሮች ምክንያት የመጨረሻ ርክክብ አለመደረጉንና በመንገዱ ላይ የታየው ችግር በገለልተኛ አካል እንዲጠና ተደርጎ የተሰራው ስራ ከዲዛይኑ ጋር የማይመሳሰል መሆኑ መረጋገጡ፣ሞያሌን በተመለከተ የቤት ግንባታው ሙሉ ለሙሉ ተጠናቆ የነበረ ቢሆንም በኢትዮ-ኬንያ (One Stop Border Post) የመንገድ ስራ ምክንያት በመፍረሱ አገልግሎት እንደማይሰጥ፣ ሞጆን በተመለከተ ስራው 64% ከተጠናቀቀ በኋላ አሁን ካለው የደረቅ ወደብ የፍተሻ ጣቢያ የራቀ እና ለፍተሻ የማያመች በመሆኑ ግንባታው ባለበት ሁኔታ ቆሞ ርክክብ መፈጸሙን ፣የመተማ እና ሁመራ ስካኒንግ ማሽን ጣቢያዎች ግንባታ ተጠናቆ ግንቦት 15/2008 ጊዜያዊ ርክክብ መደረጉን እና በጅግጅጋ እና ቶጎጫሌ ሳይቶች ቀሪ ስራዎችን ለማጠናቀቅ ሂደት ላይ መሆናቸውን በኦዲት ወቅት ከተከለሱ ማስረጃዎች እና በቃል መጠይቅ ለማወቅ ተችሏል፡፡

55.በተጨማሪም በውለታው የተካተቱ የሪጅድ ፔቭመንት መንገድ ስራ ግንባታ እና የስካኒንግ ማሽን ዙሪያ አጥር በተመለከተ የብረታ ብረት እና ኢንጅነሪንግ ኮርፖሬሽን ስራውን ባግባቡ

ሊሰራ ባለመቻሉ ባለስልጣን መ/ቤቱ ከኮርፖሬሽኑ ጋር የገባውን ውል በማቋረጥ አዲስ ጨረታ እንዲወጣ  በማድረግ ጅግጅጋ ላይ የጅግጅጋ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት የግንባታ ፕሮጀክት ስራን በመስራት ላይ ያለው ድርጅት  መንገዱንም እንዲሰራ መደረጉን እና የቶጎጫሌ ስካኒንግ ማሽን የሪጅድ ፔቭመንት መንገድ ስራ ለቤርሞግ የግል ኮንስትራክሽን ኩባንያ መሰጠቱን፣እስከ ህዳር/2009 ለመተማ እና ሁመራ ጣቢያዎች ስካኒንግ ማሽን የሪጅድ ፔቭመንት መንገድ ስራ ግንባታ መጀመሪያ በወጣው ጨረታ የተወዳደረ ተጫራች ባለመኖሩ ለሁለተኛ ጊዜ በወጣ ጨረታ የቀረቡ ተጫራቾች ግምገማ ላይ መሆኑን ለማወቅ ተችሏል፡፡

56. የኤሌክትሮኒክስ ካርጎ ስካኒንግ ማሽን ፕሮጀክት ግንባታ ተቋራጭ የሆነው የኢትዮጵያ ብረታብረት እና ኢንጅነሪንግ ኮርፖሬሽን በውል ስምምነቱ ከገባቸው ግዴታዎች መካከል ያልተከበሩ አንቀጾች፣አሰሪው መ/ቤት ስምምነቱን በጽሁፍ ሳይገልጽ ውል ተቀባዩ ፕሮጀክቱን ለንዑስ ስራ ተቋራጮች አሳልፎ መስጠቱ፣የአሰሪውን መ/ቤት ስምምነት ሳይጠይቅ የኮንትራት ጊዜውን ማራዘሙ፣ውል ተቀባዩ በገባው ግዴታ መሰረት ፕሮጀክቱን በማጠናቀቂያ ጊዜ ውስጥ አጠናቆ አለማስረከቡ፣ውል ተቀባዩ ከፍተኛ የጥራት መጓደሎችን በተገቢው ጊዜ ውስጥ አለማስተካከሉ/የጋላሬ አስፋልት/፣ ውል ተቀባዩ ለፕሮጀክቱ ተገቢውን ትኩረት ሰጥቶ ፕሮጀክቶቹን በሳይቱ በመገኘት የሚከታተል ባለሙያ አለመመደቡ፣በብድርና በልገሳ በውድ ገንዘብ ተገዝተው የገቡ የስካኒንግ ማሽኖች ለሁለት ዓመታት የህል ያለስራ በመቀመጣቸው ለብልሽት እየተዳረጉ መሆኑ፣የኢትዮጲያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን ለኢትዮጲያ ብረታብረትና ኢንጅነሪንግ ኮርፖሬሽን ቀሪ የግንባታ ስራዎችን እንዲያጠናቅቁ ማሳሰቢያ ቢጻፍም በውል ተቀባዩ በኩል አመረቂ ምላሽ ያልተሰጠ መሆኑን  በኦዲት ወቅት ከተከለሱ ማስረጃዎች ለማወቅ ተችሏል፡፡

57. ጉዳዩን አስመልክቶ የባለስልጣን መ/ቤቱ ኃላፊዎች ለቀረበላቸው ጥያቄ ሲመልሱ ለስራው መጓተት ዋነኛ መንስኤ የሆነው ውለታውን የወሰደው የብረታ ብረት እና ኢንጅነሪንግ ኮርፖሬሽን ስራውን ባግባቡ ባለመስራቱ፣ የዲዛይንና ግንባታ ስራውን ያለአማካሪ ኮርፖሬሽኑ ብቻ እንዲሰራ መደረጉ እና ስራውንም ከባለስልጣኑ እውቅና ውጪ ለሰብ ኮንትራክተሮች አሳልፎ መስጠቱ የሚጠቀሱ ችግሮች መሆናቸውን ገልጸው ችግሮቹን ለመፍታት ከብረታ ብረትና ኢንጅነሪንግ ኮርፖሬሽን ጋር በተደጋጋሚ ውይይት ቢደረግም መፍትሄ ሊገኝ እንዳልቻለ ገልጸዋል፡፡

58. በሌላ በኩል በኢትዩጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን በአዲስ አበባ ኤርፖርት ጉምሩክ ቅ/ጽ/ቤት የአየር በአየር በ190 የማስጫኛ ሰነድ ለወጡ እቃዎች የኢትዮጵያ አየር መንገድ

እቃዎችን ለማን እንዳስረከባቸው ፤መቼ እንዳስረከባቸው ዝርዝር መረጃ የተጠየቀ ቢሆንም አየር መንገዱ በ83 የማስጫኛ ሰነዶች ለመጡ እቃዎች ብቻ የእቃዎቹ ባለቤት ናቸው የተባሉትን ማረጋገጫ የሰጠ ሲሆን በ107 የማስጫኛ ሰነድ ለወጡ ዕቃዎች ማረጋገጫ ያላቀረበ መሆኑ፣ በተጨማሪም ከመጋዘን አየር በአየር ከወጡ ዕቃዎች በግምታዊ ዋጋ ብር 101,932,491 ቀረጥና ታክስ እንዲሰበሰብ መጠየቁ፣የአዲስ አበባ ኤርፖርት ጉምሩክ ቅ/ጽ/ቤት አጓጓዥ ድርጅቶች ወደ ሀገር ለሚያስገቧቸው እቃዎች የእቃ መግለጫዎችን (manifest) የሚያገኝበት አሰራር ኋላ ቀር እና አጓጓዥ ድርጅቶች ካላቸው ሲስተም ጋር የተጣጣመ እንዳልሆነ በኦዲት ወቅት ከተከለሱ ማስረጃዎች እና በቃለ መጠይቅ ለማወቅ ተችሏል፡፡

59.ጉዳዩን አስመልክቶ ለአዲስ አበባ ኤርፖርት ጉምሩክ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት የህግ ማስከበር የስራ ሂደት ተወካይ ለቀረበላቸው ጥያቄ የባለስልጣን መ/ቤቱ እና የኢትዮጵያ አየር መንገድ ሲስተም አለመጣጣም የችግሩ መንስኤ መሆኑን እና ጉዳዮ በህግ ሂደት ላይ እንዳለ ፣ በተጨማሪም የቅርንጫፍ ጽ/ቤቱ የመጋዘን አስተዳደር የስራ ሂደት አስተባባሪ በሠጡት ምላሽ የአየር ክልል ቡድን እና የማንፌስት ቡድን ለካርጎ የንግድ እቃዎች ባለመመደቡ የንግድ እቃ ከአውሮፕላን ወርዶ መጋዘን መግባት አለመግባቱን በቅርንጫፍ ጽ/ቤቱ የመከታተል እና የመቆጣጠር ስራ አለመሰራቱ መንስኤ እንደሆነ ገልጸዋል፡፡

60.በአዲስ አበባ ቃሊቲ ጉምሩክ የውጭ ፍተሻ ውጤት በወቅቱ ከቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች ባለመላኩ የትራንዚት ማንፌስት መዝጋት አለመቻሉ ይህ የሚሆንበትም ምክንያት የውጭ ፍተሻ እንዲያካሄዱ ፍቃድ የተሰጣቸው አካላት የፍተሻ ውጤት መመሪያው እንደሚያዘው በሶስት ቀን ውስጥ ውጤቱን ማድረስ ሲገባቸው አለማድረስ እና የውጭ ፍተሻው ውጤት የሚመለከታቸው የእቃ አወጣጥ ዮኒቶች ውጤቱ ምን ደረጃ ላይ እንደደረሰ አለመከታተላቸው በዚህ ምክንያት የፍተሻ ውጤት እንደሚዘገይ እና ዲክላራሲዮን እንደማይበተን፣የፍተሻ ወሰናቸው አለመታወቁ ከአዲስ አበባ ውጪም እየተሰራ መሆኑ እና በስድስት ፈታሾች መሰራቱ አገልግሎቱን እንደሚያጓትተው በኦዲት ወቅት ከተከለሱ ማስረጃዎች እና ቃለ መጠይቅ ከቀረበላቸው ሃላፊዎች ምላሽ ለመረዳት ተችሏል፡፡

61.በባለስልጣኑ ለነባራዊ ሁኔታ መግለጫ በተሰጠ ምላሽ በጉምሩክ የእቃ ፍተሻ መመርያ መሰረት በሌሎች የጉምሩክ ቅ/ጽ/ቤቶችና ጣቢያዎች ለሚፈቀዱ የአደራ ፍተሻዎች የፍተሻ ውጤት በወቅቱ ባለመላኩ ምክንያት በርካታ ሰነዶች በእንጥልጥል ላይ የሚገኙ መሆኑን አስመልክቶ የተሰጠው የኦዲት አስተያየት ትክክል ሲሆን በዋናነት ፍተሻ እንዲያከናውኑ የተጠየቁ ቅ/ጽ/ቤቶች በመመርያው በተቀመጠው አግባብ ባለመፈጸማቸው የተነሳ እና

በቅ/ጽ/ቤቶች የውጭ ፍተሻ የጠየቁ ክሊራንስ ዮኒቶች የሚያደርጉት ክትትል አናሳ በመሆኑ ሲሆን በጉዳዩ ላይ በተደረገ ውይይትና መግባባት የፍተሻ ውጤት ላልላኩ ቅ/ጽ/ቤቶች በድጋሚ በደብዳቤ እንዲጠየቁ በማድረግ እና በዋና መ/ቤት የጉምሩክ ቅ/ጽ/ቤቶች ድጋፍና ክትትል ዳይሬክቶሬት በኩል ግፊት እንዲደረግ ተደርጎ አብዛኛው የፍተሻ ውጤት የተላከላቸው በመሆኑ ሰነዶች ተዘግተዋል ቀሪ ያልመጣላቸው ላይ መረጃው ተይዞ ክትትል እየተደረገ እንደሚገኝ ተገልጿል፡፡በተጨማሪም በሞጆ ጉምሩክ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት የተንቀሳቃሽ ስካኒንግ ማሽን አገልግሎት የጀመረ  መሆኑ ተገልጿል፡፡ እንዲሁም በአ.አ ኤርፖርት ቅ/ጽ/ቤት 101,932,491 ግምታዊ ቀረጥና ታክስ ዋጋ ያላቸው እቃዎች መጋዘን ውስጥ ገብተው ነገር ግን ተገቢ የመንግስት ቀረጥና ታክስ ሳይከፈል ከአየር መንገድ መጋዘን እቃዎቹ አየር ባየር መውጣታቸውን በተመለከተ ያለጉምሩክ መልቀቂያ የወጡ እቃዎች መኖራቸው ትክክል ሆኖ ያለጉምሩክ መልቀቂያ እንዲወጡ የሚፈቅድ አሰራር ስላለ ሳይሆን የጉምሩክ መልቀቂያ ተሰጥቶአቸው የሚወጡ እቃዎች ብቻ ለይተው እንዲያስተናግዱ፣የጉምሩክ መልቀቂያ ሳያገኝ እቃ እንዳይወጣ እንዲቆጣጠሩ የተመደቡ ኢንስፔክተሮች ከህገ-ወጦች ጋር በመተባበር የጉምሩክ ስነ-ስርአት ሳይፈጸምበትና የጉምሩክ መልቀቂያ ሳይሰጣቸው እንዲወጡ በማድረጋቸው ነው፡፡ይህ ህገ-ወጥ ተግባር እንደታወቀ የዚህ ተባባሪ የነበሩ ሰዎች በህግ ለመጠየቅ በተሰራው ስራ አንድ የጉምሩክ ሰራተኛ እና ሶስት የአየር መንገድ እንዲሁም የውጭ ግብረ አበሮቻቸው በህግ ተይዘው በፍርድ ሂደት ላይ ያለ ሲሆን አንድ ተዋናይ መሆኗ የታወቀች የጉምሩክ ሰራተኛ ተሰውራ በጸረ-ሙስና በክትትል ላይ መሆኗ፤ኢንስፔክተር አስተባባሪ የነበረ ለጥያቄ ሲፈለግ የጠፋ መሆኑ እንደተቋም ሊወሰድ የሚገባው እርምጃ የተወሰደ በመሆኑ እንደክፍተት ሊወሰድ አይገባም በማለት ገልጸዋል፡፡

62. ሆኖም ግን በአዲስ አበባ ኤርፖርት ጉምሩክ ቅ/ጽ/ቤት ድርጊቱ ከተፈጸመ በኋላ የተሰሩ ስራዎች አግባብነት ያላቸው መሆኑ እንደተጠበቀ ሆኖ የአየር በአየር ኮንትሮባንድ ወንጀሉ ሲፈጸም በቅርንጫፍ ጽ/ቤቱ በአሰራር ደረጃ መሰራት እያለባቸው ያልተሰሩ ስራዎች በመኖራቸው ለምሳሌ በኢትዮጵያ አየር መንገድ መጥተው ወደ መጋዘን የሚገቡ ዕቃዎችን የሚቆጣጠሩ የጉምሩክ የአየር ክልል ሰራተኞች አለመኖራቸው፣አጓጓዥ ድርጅቶች ወደ አገር ለሚያስገቧቸው ዕቃዎች የእቃ መግለጫዎችን ባለስልጣኑ የሚያገኝበት አሰራር ኋላ ቀር እና አጓጓዥ ድርጅቶች ካላቸው ሲስተም ጋር የተጣጣመ አለመሆኑ፣በኢንስፔክተሮች ለሚለቀቁ ዕቃዎች በሀርድ ኮፒ ከሚሰጠው መልቀቂያ በተጨማሪ በሲስተም ቀረጥና ታክሱ ስለመከፈሉ

እና መልቀቂያ ስለመሰጠቱ አረጋግጦ ዕቃዎች እንዲወጡ አለማድረግ እና ሌሎችንም የቁጥጥር ክፍተቶች በመጠቀም የተፈጸመ ድርጊት በመሆኑ ድርጊቱ እንደክፍተት ሊወሰድ አይገባውም ተብሎ የተገለጸው አግባብነት የለውም፡፡

63.በባለስልጣኑ የሚሰጡ አገልግሎቶችን እና ቁጥጥሩን ለማመጣጠን ከሚያግዙ ዘመናዊ ቴክኖሎጂዎች መካካል አንዱ የሆነው የኤሌክትሮኒክስ ካርጎ ፍተሻ መሳሪያ በታቀደው መሰረት በመቆጣጠሪያ ጣቢያዎች ላይ ስራ አለመጀመራቸው በባለስልጣኑ የጉምሩክ ስነ ሥርዓት የፍተሻ ስርዓቱ እና በአጠቃላይ በአገልግሎት አሰጣጡ ላይ መጓተትን የሚያስከትል መሆኑ፣የጉምሩክ ስነ ስርዓት ሳይፈጸምባቸው አየር በአየር ከመጋዘን የወጡ ዕቃዎች መንግስት ሊያገኝ የሚገባውን ቀረጥና ታክስ ከማሳጣቱም በላይ በቅርንጫፍ ጽ/ቤቱ የሚካሄደው የቁጥጥር ስርዓት ደካማ መሆኑን የሚያሳይ በመሆኑ አሰራሩ ተገቢ ሆኖ አልተገኘም፡፡

**በባለስልጣኑ የተዘረጋው የጉምሩክ ዕቃ አወጣጥና የመጋዘን አሠራር ስርዓት ቀልጣፋ እና ውጤታማ መሆኑን መገምገም በተመለከተ፤**

**የጉምሩክ ዕቃ አወጣጥ ሥነ-ሥርዓት በብቃት እና በቅልጥፍና የሚከናወን መሆኑን ማረጋገጥ በተመለከተ፣**

64.ባለስልጣኑ የገቢ፣የወጪ እና የተላላፊ ዕቃዎችን በሚመለከት የሚኖር የስጋት ደረጃን የሚወስን መመሪያ ሊያወጣ እና የሚሰጡ የጉምሩክ አገልግሎቶች እና የሚከናወኑ የቁጥጥር ስርዓቶች በመረጃ በተደገፈ መመዘኛ የገቢ ፣ የወጪ እና የተላላፊ ዕቃዎችን የስጋት ደረጃ በመለየት የአገልግሎት አሰጣጡን እና የቁጥጥር ስርዓቱን ሚዛናዊነት ጠብቆ መከናወን ይገባዋል፡፡

65.በባለስልጣኑ የጉምሩክ አዋጅ ቁጥር 859/2006 አንቀጽ 6(4) መሰረት መ/ቤቱ የገቢ፣የወጪ እና የተላላፊ እቃዎችን በሚመለከት የሚኖር የስጋት ደረጃን የሚወስን መመሪያ እንዳላወጣ ለማወቅ ተችሏል፡፡

66.በባለስልጣን መ/ቤቱ በ2008 በጀት ዓመት በሥጋት ሥራ አመራር ሥርዓት ላይ በተደረገው ማሻሻያ ከአጠቃላይ የሥጋት ደረጃ ከተስተናገዱ 136,931 ዲክላራሲዮኖች ውስጥ የቀይ የሥጋት ደረጃ 35 በመቶ፣ የቢጫ የሥጋት ደረጃ 50.7 በመቶ፣ የአረንጓዴ የስጋት ደረጃ 13.70 በመቶ እና በሰማያዊ የስጋት ደረጃ 0.06 በመቶ ሽፋን ሲኖራቸው የቀይ የሥጋት ደረጃ 20 በመቶ ለማድረስ ታቅዶ አለመሳካቱ፣እንዲሁም በ2007 በጀት ዓመት በስጋት ሥራ አመራር ሥርዓት ላይ በተደረገው ማሻሻያ ከአጠቃላይ የሥጋት ደረጃ ከተስተናገዱ 139,330

ዲክላራሲዮኖች ውስጥ የቀይ የሥጋት ደረጃ 40.02 በመቶ ሽፋን የነበራቸው ሲሆን በበጀት ዓመቱ መጨረሻ የቀይ የሥጋት ደረጃን ወደ 31 በመቶ ለማድረስ ታቅዶ እንዳልተሳካ በኦዲት ወቅት ከተከለሱ ማስረጃዎች ለማወቅ ተችሏል፡፡

67.ጉዳዩን አስመልክቶ የባለስልጣን መ/ቤቱ ኃላፊዎች ሲመልሱ በባለስልጣኑ ለስጋት ስራ አመራር የራሱ የሆነ ፖሊሲ እና ማንዋል እንደተዘጋጀለት ገልጸው አዋጁ ላይ የተጠቀሰው አንቀጽ የስጋት ባህሪ ተለዋዋጭነትን ግንዛቤ ውስጥ ያላስገባ ስለሆነ መግባት የለበትም፣ መመርያው ቢወጣም ማንዋሉ እና ፖሊሲው ላይ ያለውን ነገር ስለሚደገም አስፈላጊ አይሆንም የሚል አስተያየት እንደተሰጠበት፣ በቀይ የስጋት ደረጃ የተስተናገዱ ዲክላራሲዮኖችን በዕቅድ የተያዘውን ግብ ለማሳካት ያልተቻለው የግብር ከፋዮ የህግ ተገዢነት በሚፈለገው ደረጃ አለመድረሱ፤ከተጓዳኝ መ/ቤቶች ጋር ያለው ቅንጅታዊ አሰራር ደካማ በመሆኑ የመረጃ ክፍተት መፍጠሩ፤በተቋም ደረጃ መረጃ የሚያስገቡ አካላት ለስጋት ትንተና የሚያስፈልጉ መረጃዎችን ሙሉ ለሙሉ አለማስገባታቸው እንደምክንያት የሚጠቀሱ መሆናቸውን ገልጸው ከዚሁ ጋር ተያይዞ የሀገሪቱም ማህበራዊ፤ኢኮኖሚያዊ እና ፖለቲካዊ ሁኔታ ግንዛቤ ውስጥ መግባት እንዳለበት ገልጸዋል፡፡በተጨማሪም የቀይ የስጋት ደረጃን ለመቀነስ የተሰሩ ስራዎችን በተመለከተ የነበሩ ሂደቶችን በመከታተል የስጋት መምረጫ መስፈርቶች ላይ ትሬሽሆልዶችን የማስተካከል ስራ መሰራቱን፣ከትራንዚተሮችና ከአስመጭዎች ጋር ለብቻ የስልጠና እና የውይይት መድረክ በማዘጋጀት የህግ ተገዥነታቸውን ደረጃ ለማሻሻል ጥረት መደረጉን እና ለስጋት ትንተና የሚገቡ መረጃዎችን ጥራት እንዲጠበቅ ጥረት እንደተደረገ በመግለጽ በቀጣይም እነዚህን ስራዎች አጠናክሮ መስራት እና በምክንያትነት የተጠቀሱ ችግሮችን እንዲፈቱ ሁሉም የበኩሉን እንዲወጣ ማድረግ ያስፈልጋል በማለት ገልጸዋል፡፡

68.በናሙና ከታዩ ቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች መካከል በአዳማ ጉምሩክ ቅ/ጽ/ቤት ከሚሌ እና ከጋላፊ ቅ/ጽ/ቤት መንገድ ወረቀት ላይ የሚጻፉ ሪማርኮች በዝቅተኛ የስጋት ደረጃ መስተናገድ የሚገባቸው ሰነዶች ተቀይረው በከፍተኛ የስጋት ደረጃ እንዲስተናገዱ መደረጉ ይህም በስራ ላይ ጫና መፍጠሩና የልዮ መብት ተጠቃሚ በሆኑት ላይ አገልግሎት አሰጣጡ እንዲጓተት ማድረጉ ምክንያቱም ሚሌ እና ጋላፊ ያሉ ሰራተኞች ስካን በሚያደርጉበት ወቅት ጥርጣሬ ካደረባቸው እዛው ከመፈተሽ ይልቅ ወደ መድረሻ ጣቢያ መላካቸው እንዲሁም ጥርጣሬ የፈጠረባቸውን ጉዳይ በኢንስፔክሽን አክት ላይ የማይሞሉ መሆኑ፣ በሞጆ ጉምሩክ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት የሚከናወን ድንገተኛ ፍተሻ ስጋትን መሰረት ያደረገ አለመሆኑ ምክንያቱም

ዕቃዎች ከመድረሳቸው በፊት የሚገኝ  መረጃ ባለመኖሩ፣ ባህር ትራንስፖርትና ሎጅስቲክስ አገልግሎት ድርጅት እና ቅ/ጽ/ቤቱ የሚጠቀሙበት ሲስተም የተገናኘ /integrated/ ባለመሆኑ መረጃ መለዋወጥ የማይቻል  መሆኑን ቃለ-መጠይቁ የቀረበላቸው የቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች የስራ ሂደት መሪዎች በሰጡት ምላሽ ለመረዳት ተችሏል፡፡

69. በነባራዊ ሁኔታ መግለጫ በተሰጠ ምላሽ በመጋዘን እና ተርሚናል አካባቢ ቅኝትና ክትትል በማድረግ ይሰራ የነበረ ሲሆን ከ2007 ዓ.ም አጋማሽ በኂላ የጉምሩክ ዘመናዊ ቴክኖሎጂ (Facevet,TPRDP) እና የስጋት መስፈርቶችን በመጠቀም ስጋትን መሰረት ያደረገ አሰራር በመተግበር ላይ ይገኛል በማለት ገልጸዋል፡፡

70. በባለስልጣኑ በቀይ የስጋት ደረጃ የሚስተናገዱ ዲክላራሲዮኖችን ለመቀነስ የተያዘውን ዕቅድ ማሳካት አለመቻሉ እቃዎችን ለመፈተሸ ተጨማሪ ወጪ ማለትም እቃዎችን ለማራገፍ እና ለመጫን እና የመጋዘን ማቆያ፣ተጨማሪ ጊዜ እና ቁሳቁስ የሚያስፈልግ መሆኑ እነዚህ ወጪዎች በዕቃዎች ዋጋ ላይ ተጨማሪ የሚደረጉ በመሆናቸው  በተጠቃሚው ህብረተሰብ ላይ ጫና ሊያሳድር ይችላል፡፡

**የጉምሩክ መጋዘን ሊያሟላ ስለሚገባው መስፈርት እና የመጋዘን ባለቤቶች ግዴታ በተመለከተ፣**

71. ባለስልጣኑ ወደአገር የሚገቡና ከአገር የሚወጡ እቃዎችን ለማከማቸት የተዘጋጁ መጋዘኖች ስለጉምሩክ መጋዘን አስተዳደር የወጣ የአፈፃፀም መመሪያ ቁጥር 40/2002 የተቀመጠላቸውን መስፈርት ያሟሉ ስለመሆናቸው እና የጉምሩክ መጋዘን እንዲያቋቁም የተፈቀደለት ሰው በአዋጅ ቁጥር 859/2006 የተቀመጡ ግዴታዎችን እየተወጣ ስለመሆኑ የክትትልና የቁጥጥር ስራ ሊሰራ ይገባል፡፡

72. በኦዲቱ ወቅት በተከለሱ ማስረጃዎች ፣በተደረገ አካላዊ ምልከታ እና በቃለ መጠይቅ ወቅት በተገኘ መረጃ  በኢትዮጵያ ባህር ትራንስፖርት ሎጅስቲክስ አገልግሎት ድርጅት በቃሊቲ ቅርንጫፍ ስር የሚተዳደሩ ክፍት እና ዝግ መጋዘኖች መልቲሞዳል መጋዘን ቁጥር 1፣6፣7፣8 እና ዩኒሞዳል  መጋዘን ቁጥር 2፣5፣12  ለመድሀኒት፣ለምግብ፣ለአደገኛ እና ለሌሎች እቃዎች አንደባህሪያቸው ለማከማቸት ወይንም ለማቆየት የሚችል የተሟላ መሳሪያ፣ጋሪ፣መሰላል፣ለጉምሩለክ ስራ አስፈላጊ የሆኑ ቢሮዎችና ተያያዥነት ያላቸው እቃዎች ያልተሟላለት መሆኑ ፣መጋዘኑ ከሌሎች የአገልግሎት መስጫ ስፍራዎች ተለይቶ አለመከለሉ፣በተለያዩ ምክንያቶች ከመጋዘን ያልወጡና የተያዙ እቃዎች የሚከማቹበት መጋዘን አለመኖሩ፣በአስፋልት የተሰራ በቂ የተሽከርካሪዎች መተላለፊያ መንገድ አለመኖሩ፣

73.በመልቲ ሞዳል ክፍት የተሽከርካሪ መጋዘን ቁጥር 11 እና ክፍት የተሽከርካሪ መጋዘን ቁጥር 9 መጋዘኑ በአስፋልት ወይንም በኮንክሪት የተሰራ ክፍት መጋዘን አለመሆኑ፣ለተሽከርካሪ ፍተሻ አመች  የሆነ የመፈተሻ ጉድጓድ/ሊፍት እና የተሟላ ጥላ ሼድ፣የጎማ የኤሌክትሪክ እና ተያያዥ የጋራዥ አገልግሎት መስጫ ፣የተሽከርካሪ መጎተቻ መሳሪያ ማሽን የሌለው መሆኑ፣ምንም አይነት የአደጋ መከላከያ መሳሪያ እና ለጉምሩክ ስራ የሚያስፈልጉ ቢሮዎች  የሌለው መሆኑ፣

74.በሞጆ ጉምሩክ ቅ/ጽ/ቤት ሜጋ መጋዘን ቁጥር 2 ባለስልጣኑ ስለጉምሩክ መጋዘን አስተዳደር የወጣ የአፈፃፀም መመሪያ ቁጥር 40/2002 ካስቀመጣቸው መስፈርቶች መካከል የውሀ መርጫ ሆዝ ፣በተለያዩ ምክንያቶች ከመጋዘን ያልወጡ እና የተያዙ እቃዎች ተለይተው የሚቀመጡበት ልዩ ስፍራ ፣ለመድሀኒት፣ለምግብ፣ለአደገኛ እና ለሌሎች እቃዎች እንደባህሪያቸው ተለይተው የሚቀመጡበት ልዩ ስፍራ አለመኖሩን እና በአግባቡ የተከለለ እና መጋዘኑ ከሌሎች የአገልግሎት መስጫ ስፍራዎች ተለይቶ የታጠረ አለመሆኑን ለማወቅ ተችሏል፡፡

75.በአዳማ ገቢዎችና ጉምሩክ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት መጋዘን ቁጥር 1 እና 4 ለመድኃኒት፣ለምግብ፣ለአደገኛ እና ለሌሎች እቃዎች እንደ ባህሪያቸው ለማከማቸት ወይንም ለማቆየት የሚያስችል የተሟላ መሳሪያ ፤ለእቃዎች፣ ለሰራተኞችና ለሌሎች ንብረቶች ደህንነት አስፈላጊ የሆኑ የአደጋ መከላከያ መሳርያዎች (የእሳት አደጋ ማጥፊያ፣ውሃ፣የውሃ መርጫ ሆዝ፣ እና የውሃ ማጠራቀሚያ)፣ለጉምሩክ ስራ አስፈላጊ የሆኑ ቢሮዎችና ተያያዥነት ያላቸው እቃዎች ፣ ለተገልጋዮች ተለይቶ የተዘጋጀ ክበብ እና በቂ መጸዳጃ ቦታ፣ በቂ የውሀ አቅርቦት የሌለው መሆኑን፣ በአግባቡ የተከለለ እና የመጋዘኑን ስፍራ ከሌሎች የአገልግሎት መስጫዎችና ቢሮዎች ተለይቶ የታጠረ አለመሆኑ፣

76.በአዳማ ገቢዎችና ጉምሩክ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት የቦንድድ መጋዘን ፈቃድ የተሰጣቸው ዲና ገዛኸኝ አስመጭና ላኪ ክፍት የተሽከርካሪ መጋዘን እና አልባር ትሬዲንግ ክፍት የተሽከርካሪ መጋዘን ስለጉምሩክ መጋዘን አስተዳዳር የወጣ የአፈጻጸም መመሪያ ካስቀመጣቸው መስፈርቶች መካከል ለተሽከርካሪ ፍተሻ አመች የሆነ የመፈተሻ ጉድጓድ/ሊፍት እና የተሟላ ጥላ/ሼድ፣የጎማ፣ የኤሌክትሪክ እና ተያያዥ የጋራዥ አገልግሎት መስጫ ፣የተሽከርካሪ መጎተቻ መሳሪያ/ማሽን፣ለእቃዎቹ፣ ለሰራተኞችና ለሌሎች ንብረቶች ደህንነት አስፈላጊ የሆኑ የአደጋ መከላከያ መሳሪያዎች (የእሳት አደጋ ማጥፊያ፣ውሃ፣የውሃ መርጫ ሆዝ፣ እና የውሃ

ማጠራቀሚያ)፣ለጉምሩክ ስራ አስፈላጊ የሆኑቢሮዎችና ተያያዥነት ያላቸው እቃዎች (ስልክ፣ኮምፒዩተር፣ወንበር፣ጠረጴዛ እና ወደ መጋዘን የሚገባና የሚወጣ እቃ የሚመዘገብበት መዝገብ፣ጄነሬተር እና መጋዘኑን ከሌሎች አገልግሎት መስጫዎችና ቢሮዎች የሚለይ አጥር እና በተለያዩ ምክንያቶች ከመጋዘን ያልወጡና የተከማቹ እቃዎች የሚከማቹበት መጋዘን የሌለው መሆኑ፤ በአዳማ የሚገኘው የአለም የምግብ ድርጅት(WFP) የመጋዘን ፈቃድ ባለቤት ቢሆንም በጉምሩክ ቁጥጥር ስር አለመሆኑ እና በጉምሩክ የቁጥጥር ስርዐት እንደማይካሄድበት ለመረዳት ተችሏል፡፡

77. በአዲስ አበባ ቃሊቲ ገቢዎችና ጉምሩክ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት የመጋዘን ፈቃድ የተሰጣቸው አብዱልቃድር ፋሪስ እና ጌታሰው አያሌው የተሽከርካሪ ቦንድድ መጋዘን በመመሪያው መሰረት ማሟላት ከሚገባቸው መስፈርቶች ውስጥ መጋዘኑ በአስፓልት ወይንም ኮንክሪት የተሰራ አለመሆኑ ፣የጎማ ፣የኤሌክትሪክ እና ተያያዥ የጋራዥ አገልግሎት መስጫ እንደሌለው፣የተሽከርካሪ መጎተቻ መሳሪያ/ማሽን የሌለው መሆኑን፣ለሰራተኞች እና ለተገልጋዮች ተለይቶ የተዘጋጀ ክበብና የተሽከርካሪ ማቆሚያ ስፍራ የሌለ መሆኑን፣በተለያዩ ምክንያቶች ከመጋዘን ያልወጡና የተያዙ እቃዎች የሚከማቹበት መጋዘን አለመኖሩ፣

78. በአዲስ አበባ ቃሊቲ ገቢዎችና ጉምሩክ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት የቦንድድ መጋዘን ፈቃድ የተሰጠው ሲ ኤንድ ኢ የግብአት ዝግ መጋዘን ማሟላት ከሚገባው መስፈርት ውስጥ ከ30 ቶን በላይ የመጫን ጉልበት ያለው መሳሪያ/ጋንትሪ ፣አንድ ወይንም ከዚያ በላይ ከ5-10 ቶን ክብደት ያለው እቃ የመጫን ጉልበት ያለው ፎርክ ሊፍት ፣እቃዎችን እንደባህሪያቸው ለማከማቸት ወይንም ለማቆየት የሚችል የተሟላ መሳሪያ ፣ለሰራተኞች እና ለተገልጋዮች ተለይቶ የተዘጋጀ ክበብ እና የተሽከርካሪ ማቆሚያ፣በተለያዩ ምክንያቶች ከመጋዘን ያልወጡና የተያዙ እቃወች የሚከማቹበት መጋዘን እና በአስፋልት የተሰራ በቂ የተሽከርካሪዎች መተላለፊያ መንገድ አለመኖሩ እና በአግባቡ የተከለለና የመጋዘን ስፍራዎች ከሌሎች አገልግሎት መስጫዎችና ቢሮዎች ተለይቶ የታጠረ አለመሆኑ፣

79. በአዲስ አበባ ቃሊቲ ገቢዎችና ጉምሩክ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት የመጋዘን ፈቃድ የተሰጠው የሺ ኃ/የተ/የግ/ማህበር የተሽከርካሪ ቦንድድ መጋዘን የተሽከርካሪ መጎተቻ መሳሪያ/ ማሽን እና በተለያዩ ምክንያቶች ከመጋዘን ያልወጡና የተያዙ እቃዎች የሚከማቹበት መጋዘን አለመኖሩ፤ ገብረሊባኖስ ስብሀቱ የተሽከርካሪ ቦንድድ መጋዘን በመመሪያው መሰረት ማሟላት ከሚገባው መስፈርት መካከል የጎማ የኤሌክትሪክና ተያያዥ የጋራዥ አገልግሎት መስጫ ፣የተሽከርካሪ መጎተቻ መሳሪያ/ማሽን ፣ለሰራተኞች እና ለተገልጋዮች የተለዩ የተሽከርካሪ ማቆሚያ ስፍራ

የሌለው መሆኑ እና በተለያዩ ምክንያቶች ከመጋዘን ያልወጡና የተያዙ እቃወች የሚከማቹበት መጋዘን አለመኖሩ፣

80. ወረታ ኢንተርናሽናል ኃ/የተ/የግ/ማህበር የተሽከርካሪ ቦንድድ መጋዘን በመመሪያው ላይ ከተቀመጡት መስፈርቶች መካከል የመፈተሻ ጥላ/ሼድ ፣የጎማ፣የኤሌክትሪክ እና ተያያዥ የጋራዥ አገልግሎት መስጫ፣ለሰራተኞችና ለተገልጋዮች ተለይቶ የተዘጋጀ ክበብና መጸዳጃ እንደሌለና በተለያዩ ምክንያቶች ከመጋዘን ያልወጡና የተያዙ እቃወች የሚከማቹበት መጋዘን የሌለው መሆኑ፣

81. ታምሬን ኢንተርናሽናል ትሬዲንግ መመሪያ ላይ ከተቀመጡት መስፈርቶች መካከል መጋዘኑ በአስፓልት ወይንም በኮንክሪት የተሰራ አለመሆኑ፣የጎማ፣የኤሌክትሪክ እና ተያያዥነት ያላቸው የጋራዥ አገልግሎት መስጫ ፣የተሽከርካሪ መጎተቻ መሳሪያ/ማሽን ፣ለሰራተኞች እና ለተገልጋዮች ተለይቶ የተዘጋጀ ክበብና በቂ መፀዳጃ ቦታ የሌለው መሆኑን እና በተለያዩ ምክንያቶች ከመጋዘን ያልወጡና የተያዙ እቃወች የሚከማቹበት መጋዘን አለመኖሩ፣

82. በ2007 በጀት ዓመት በቃሊቲ ገቢዎችና ጉምሩክ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት የሱፐርቪዥን ስራ የተከናወነባቸው የተፈቀዱ አንድ መቶ አስራ ስምንት መጋዘኖች ሲሆኑ ሰላሳ ሰባት የተፈቀዱ መጋዘኖች በአዋጅ 859/2006 አንቀጽ 132 ስር የሚያርፉ በመሆኑ በብር አምሳ ሺህ እንዲቀጡ፣ሰባት የተፈቀዱ መጋዘኖች በጉምሩክ አዋጅ 859/2006 አንቀጽ 132 ስር ከተቀመጡት ግዴታዎች ሁለት እና ከዚያ በላይ ጉድለት የተገኘባቸው በመሆኑ በብር አንድ መቶ ሺህ እንዲቀጡ፣ሃያ ሰባት የተፈቀዱ መጋዘኖች ከዚህ ቀደም የጥፋት ሪከረድ ያለባቸው ሆነው በሱፐርቪዥን ጊዜም ጉድለት የተገኘባቸው ቢሆንም በመመሪያ 46/2002 አንቀጽ 12 መሰረት ተደጋጋሚ ጥፋት በሚል የአስተዳደራዊ እርምጃ የውሳኔ ሃሳብ ለማቅረብ ያልተቻለ በመሆኑ ጉዳዩ በማኔጅመንት ታይቶ ውሳኔ እንዲሰጥበት በኮሚቴው የቀረበ መሆኑ፣

83. በተጨማሪም በቃሊቲ ገቢዎችና ጉምሩክ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት በተፈቀዱ መጋዘኖች ላይ የታዩ ጉድለቶች በመጋዘኑ ባለቤቶች ብቻ ያልተፈጸሙና በጉምሩክ በኩልም የታዩ ክፍተቶች መኖራቸው ለምሳሌ በባለስልጣኑ የመጋዘን ፈቃድ አሰጣጥ መመሪያ ላይ የተቀመጡ መስፈርቶች ሳይሟሉ ፍቃድ የሚሰጥበት ሁኔታ መኖሩ፣የተፈቀዱት መጋዘኖች በተለያየ ወቅትና በተለያዩ ቨርቹዋል ኮሚቴ ፍቃድ የተሰጣቸው ስለሆነ የመጋዘኖቹ የአፈቃቀድ ሁኔታ ወጥነት የሌለው መሆኑ፣የጉምሩክ መጋዘን ፍቃድ ከተሰጠ በኋላ የድጋፍ፣የክትትል እና የቁጥጥር ስርዓት ውስንነት መኖሩ በሱፐርቪዥን ቡድኑ የተቀመጠ መሆኑ፣

84. ስለጉዳዩ የሚመለከታቸው የባለስልጣኑ ኃላፊዎች ተጠይቀው ሲመልሱ የዳይሬክቶሬቱ ድርሻ የአሰራር ስርአት ተቀርጾ ለቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች እንዲተላለፍ ማድረግ ሲሆን ፈቃድ የመስጠቱ ስራ የቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች ሀላፊነት መሆኑን ጠቅሰው ከመመሪያው ውጭ መስፈርቱ ሳይሟላ ፍቃድ የሚሰጥ ከሆነ ተጠያቂ የሚሆኑት ፈቃድ የሰጡ ቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች መሆናቸውን ገልጸዋል፡፡

85. ለነባራዊ ሁኔታ መግለጫ በተሰጠ ምላሽ በተፈቀዱ መጋዘኖች(ቦንድድ ዌርሀውስ) የታዮ ጉድለቶችን በተመለከተ የችግሩ መነሻ በዋናነት መጋዘኖች ማሟላት ስላለባቸው ቅድመ ሁኔታዎች የተቀመጡ መስፈርቶች ከጊዜው ጋር የማይሄዱ ስለሆነ አዋጁን ተከትሎ በሚወጣው መመርያ መሰረት የሚስተካከል ነው፡፡በሌላ መልኩ መጋዘኖች ሲፈቀዱ ሁሉንም መስፈርቶች ያሟሉ መሆናቸው በቨርቹዋል ኮሚቴ ከተረጋገጠ በኂላ ሲሆን ፈቃዱን ካገኙ በኂላ በመስፈርቱ መሰረት የተቀመጡ እቃዎችን ተጠቃሚዎች በማንሳታቸው መሆኑ ባለፉት አመታት በተደረጉ የሱፐርቪዥን ስራዎች የተረጋገጠ ሲሆን በአዋጁ እና መመርያው መሰረት በአስተዳደራዊ ሁኔታ የገንዘብ ቅጣት የተጣለባቸውና ማስተካከል ያልቻሉ ሁለት ድርጅቶች ፈቃዳቸው እንዲሰረዝ ተደርጓል፡፡የተፈቀዱ መጋዘኖች ጋር የተገናኙ ችግሮች ከአፈቃቀዳቸው ጀምሮ እስከ ክትትል ድረስ ያለው ቁጥጥር ስራ ጠንካራ አለመሆን በግምገማችን የታየ ስለሆነ በአጭር ጊዜ ውስጥ የማስተካከያ እርምጃ በመውሰድ የምናሳውቅ መሆኑን እንገልጻለን በማለት ምላሽ ሰጥተዋል፡፡

86. የጉምሩክ መጋዘኖች በአዋጅ እና በመመሪያ የተቀመጡትን ግዴታዎች እና መስፈርቶች ሳያሟሉ ፈቃድ መስጠት እና በክትትል ወቅት በተደጋጋሚ ግዴታቸውን ያልተወጡ የመጋዘን ባለቤቶች ላይ እርምጃ የማይወሰድ ከሆነ ለብልሹ አሰራር እና ለህገወጥነት በር የሚከፍት ከመሆኑም በላይ መንግስት ሊያገኝ የሚገባውን ቀረጥና ታክስ ሊያሳጣ ይችላል፡፡

### የጉምሩክ መጋዘን የዕቃዎች አቀማመጥ፣የምዝገባና ሪፖርት ስርዓት እንዲሁም የመጋዘን ኪራይ አሰራር በተመለከተ፣

87. በባለስልጣኑ ወደ ጉምሩክ መጋዘን የገቡ ዕቃዎች እንደአይነታቸውና እንደባህሪያቸው ተለይተው ለደህንነታቸው ተስማሚ በሆነና ለጉምሩክ ቁጥጥር አመቺ በሆነ ሁኔታ የተቀመጡ መሆናቸው፣ ወደ ጉምሩክ መጋዘን የሚገቡና የጉምሩክ ሥነ-ስርዓት ተፈጽሞባቸው የሚለቀቁ እቃዎች ባለስልጣኑ በወሰነው የመዝገብ አያያዝ ስርዓት መመዝገባቸውና ምዝገባው ሪፖርት ስለመደረጉ እና ማንኛውም ገቢ እና ወጪ እቃ በመጋዘን ውስጥ ለቆየበት ጊዜ የመጋዘን ኪራይ ሂሳብ መከፈሉ መረጋገጥ አለበት፡፡

88.በኦዲት ወቅት በናሙና በታዩት አዲስ አበባ ቃሊቲ ጉምሩክ ቅ/ጽ/ቤት፣በሞጆ ገቢዎችና ጉምሩክ ቅ/ጽ/ቤት እና በአዳማ ገቢዎችና ጉምሩክ ቅ/ጽ/ቤት የሚገኙ ጊዜያዊ የዕቃ ማከማቻ መጋዘኖች ዕቃዎች እንደአይነታቸውና እንደባህሪያቸው ተለይተው ለደህንነታቸው ተስማሚ በሆነና ለጉምሩክ ቁጥጥር አመቺ በሆነ ሁኔታ ያልተቀመጡ መሆናቸውን በአካል ምልከታ ወቅት ለማረጋገጥ ተችሏል፡፡

89.በአዲስ አበባ ኤርፖርት ጉምሩክ ቅ/ጽ/ቤት የጊዜያዊ እቃ ማከማቻ መጋዘን ሰነዶች ባግባቡ ተደራጅተው እንደማይቀመጡ፣ስለወጡት እቃዎች በኮምፒውተርም ሆነ በተዘጋጀ መዝገብ ላይ መረጃዎችን አለመያዝና አለመመዝገብ እንዲሁም የተመዘገበውም ቢሆን የተሟላ አለመሆን ከፊረቃ ፊረቃ እንዲሁም ከፈፃሚ ፈፃሚ የሚለያይ በመሆኑ ወጥነት የሚጎድለው መሆኑ፣በቅርንጫፍ ጽ/ቤቱ 101,932,491 ግምታዊ ቀረጥና ታክስ ዋጋ ያላቸው እቃዎች መጋዘን ውስጥ ገብተው ነገር ግን ተገቢው የመንግስት ቀረጥ እና ታክስ ሳይከፈል ከአየር መንገድ መጋዘን እቃዎቹ አየር ባየር መውጣታቸውን፣በቅ/ጽ/ቤቱ እና በአየር መንገዱ ሲስተም ላይ መረጃ ያልተገኘላቸው መሆኑ ፣ከአየር መንገድ መጋዘን ወደ ጉምሩክ መጋዘን ከሚገቡ እቃወች የስጋት ደረጃቸው አረንጓዴ የሆኑትን አለመመዝገብ ፣ምን እንደገባና ምን እንደወጣ ለማወቅ አስቸጋሪ ማድረጉ ከተከለሱ ማስረጃዎች ለማወቅ ተችሏል፡፡

90.የኢትዮጵያ አየር መንገድ ለመጋዘን ኪራይ ስለጉምሩክ መጋዘን አስተዳደር የወጣ የአፈፃፀም መመሪያ ቁጥር 40/2002 ለማሻሻል የወጣ መመሪያ ቁጥር 76/2004 ከሚያዘው ታሪፍ ውጪ እያስከፈለ መሆኑ፣

91.በጉምሩክ አዋጅ ቁጥር 859/2006 አንቀጽ 59 ንዑስ አንቀጽ 2 የጉምሩክ መጋዘን ኪራይ ማስከፈያ ተመን በሚኒስትሮች ምክር ቤት በሚወጣ ደንብ ይወሰናል ቢልም ይህ ኦዲት እስከተጠናቀቀበት ጊዜ ድረስ ደንቡ ያልወጣ መሆኑን ለማወቅ ተችሏል፡፡

92.በነባራዊ ሁኔታ መግለጫ በተሰጠ መልስ ገቢ እና ወጪ እቃ በመጋዘን ውስጥ ለቆየበት ጊዜ የመጋዘን ኪራይ ሂሳብ በግኝቱ የተቀመጠው ትክክል ነው ነገር ግን በአዲሱ የጉምሩክ አዋጅ 859/2006 የመጋዘን ኪራይ ታሪፍ የማውጣት ስልጣን ለሚኒስትሮች ም/ቤት የተሰጠ ስለሆነ እና ረቂቅ ደንቡ ተዘጋጅቶ አስተያየት ተሰጥቶበት የተላከ ስለሆነ ጸድቆ ሲመጣ በደንቡ መሰረት የሚፈጸም ነው በማለት ተገልጿል፡፡

93.በባለስልጣን መ/ቤቱ እቃዎች እንደአይነታቸው እና ባህሪያቸው ተለይተው እንዲቀመጡ ካልተደረገ የመርዛማነት ባህርይ ያላቸው ዕቃዎች ለምግብ እና መጠጥ ፍጆታ ከሚውሉ እቃዎች ጋር ተቀላቅለው የሚቀመጡ ከሆነ በተጠቃሚው ህብረተሰብ ላይ የጤና እክል

ሊያስከትል የሚችል መሆኑ፣የምዝገባ እና የሪፖርት ስርአቱ ወጥ በሆነ መንገድ ባለመተግበሩ የእቃዎችን ትክክለኛ ቁጥር እንዲሁም የእቃዎችን የቆይታ ጊዜ ለማወቅ አዳጋች ሊያደርገው መቻሉ እንዲሁም በባለስልጣኑ የመጋዘን ኪራይ ደንብ እንዲወጣ ባለመደረጉ የመጋዘን ባለቤቶች ፍትሀዊ እና ወጥ ያልሆነ የመጋዘን የኪራይ ተመን አውጥተው የእቃዎች ዋጋ እንዲጨምር በማድረግ በተጠቃሚው ህብረተሰብ ላይ ጫና የሚፈጥር በመሆኑ አሰራሩ ተገቢ ሆኖ አልተገኘም፡፡

**በጉምሩክ መጋዘን የዕቃዎች በመጋዘን የቆይታ ጊዜ በጉምሩክ አዋጅ ቁጥር 859/2006 በተቀመጠው መሰረት ተግባራዊ ስለመደረጉ፣**

94. ባለስልጣኑ እቃዎች በመጋዘን ውስጥ የሚቆዩት በጉምሩክ አዋጅ በተቀመጠው የጊዜ ገደብ መሰረት መሆኑን ሊያረጋግጥ እና ወደ ጊዜያዊ የጉምሩክ ዕቃ ማከማቻ ወይም ቦንድድ መጋዘን የገባ ዕቃ በአዋጁ በተቀመጠው ጊዜ ውስጥ ካልወጣ ወደ መንግስት ጉምሩክ መጋዘን እንዲዛወር ሊያደርግ ይገባል፡፡
95. በጉምሩክ አዋጅ ቁጥር 859/2006 አንቀጽ 51 ንዑስ አንቀጽ 1 ማናቸውም በባህር ወይም በየብስ ተጓጉዞ ወደ አገር የገባ ዕቃ ጊዜያዊ የጉምሩክ ዕቃ ማከማቻ ከገባበት ቀን ጀምሮ በሁለት ወር ጊዜ ውስጥ አስፈላጊው የጉምሩክ ስነ ስርዓት ተከናውኖበት ከማከማቻው መውጣት አለበት፣ ንዑስ አንቀጽ 6 ወደ ጊዜያዊ የጉምሩክ ዕቃ ማከማቻ ወይም ቦንድድ መጋዘን የገባ ዕቃ የጉምሩክ ፎርማሊቲ ከተከናወነበት በኂላ ከሰባት የስራ ቀናት በላይ በማከማቻው ሊቆይ አይችልም በማለት ቢደነግግም፣
96. በኦዲቱ ወቅት በናሙና ከታዩ ቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች መካከል እስከ ሰኔ 30/2008 ዓ.ም በሞጆ ደረቅ ወደብ ሶስት ወር የሆናቸው 12 ኮንቴይነሮች፣ ከሶስት ወር በላይ የሆናቸው 640 ኮንቴነሮች፣ከስድስት ወር በላይ የሆናቸው 315 ኮንቴነሮች እና ከአንድ አመት በላይ የሆናቸው 213 ኮንቴይነሮች በድምሩ 1,180 እና በአዲስ አበባ ቃሊቲ ደረቅ ወደብ ከሁለት ወር በላይ የቆዩ 54 ኮንቴነሮች መኖራቸው፣
97. እንዲሁም በአዲስ አበባ ቃሊቲ ጉምሩክ ቅ/ጽ/ቤት ግቢ ውስጥ በሚገኙ መጋዘን ቁጥር አንድ 29፣መጋዘን ቁጥር ሁለት 28 ፣ መጋዘን ቁጥር አምስት 21፣ መጋዘን ቁጥር ስድስት 19፣ መጋዘን ቁጥር ሰባት 16፣መጋዘን ቁጥር አስራ ሁለት 18 የተለያዩ እቃዎች እና በክፍት የፍተሻ መጋዘን 3 ኮንቴነር ከሁለት ወር በላይ በመጋዘን የቆዩ መኖራቸው፣
98. በአዳማ ገቢዎችና ጉምሩክ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት ገቢ የተደረጉ እና የቆይታ ጊዜያቸውን ያሳለፉ የተለያዩ እቃዎች ለማሳያነት ያክል 11 ኮንቴነር፣በቁጥር 489 ልዩ ልዩ የመኪና ጎማዎች፣ባለ

25 ኪ.ግ 2,616 ክረጢት ሩዝ፣ 783 ካርቶን ኮስሞቲክስ እና 385 ካርቶን እስክርቢቶ ወደ ውርስ መጋዘን ሳይተላለፉ ጊዜያዊ እቃ ማከማቻ መጋዘን ውስጥ ተከማችተው የሚገኙ መሆኑን በኦዲት ወቅት ከተከለሱ መረጃዎች እና በአካል ምልከታ ለማረጋገጥ ተችሏል፡፡

99. በሞጆ ጉምሩክ በ2007 ዓ.ም መልቀቂያ ተሰጥቷቸው እስከ ሰባት ቀን ያልወጡ ኮንቴይነሮች ላይ እርምጃ ለመውሰድ ግልጽ አቅጣጫ ያልተቀመጠ በመሆኑ 123 አስመጪዎች በአቤቱታ መስተናገዳቸው፣በአቃቂ ቃሊቲ ጉምሩክ ቅ/ጽ/ቤት መልቀቂያ አግኝተው ከሰባት ቀናት በላይ ከመጋዘን ያልወጡ ዕቃዎች (በኢትዮጵያ ንግድ ድርጅት፣በሲኤንድኢ እና በይበል ኢንዱስትሪያል የተፈቀዱ ቦንድድ መጋዘኖች) መኖራቸው ሪፖርት መደረጉ በኦዲት ወቅት ከተከለሱ መረጃዎች ለማወቅ ተችሏል፡፡

100. በአዲስ አበባ ቃሊቲ ጉምሩክ በመልቲ ሞዳል እና በዩኒሞዳል የገቡ በርካታ ኮንቴይነሮች ሳይለቀቁ በደረቅ ወደቡ ለረጅም ጊዜ የመቆየታቸው ምክንያት ተብለው ከተገለጹት ውስጥ የሰነዶች ቶሎ አለመምጣት እና ተሟልቶ አለመቅረብ፤ ከአስመጭዎች ቀረጥና ታክስ ለመክፈል የገንዘብ እጥረት፤የቀረጥ እና የዋጋ ክርክር ሂደት መዘግየት፤መወገድ የሚገባቸው እቃዎች ደንበኞች ቀርበው አለማስወገዳቸው እንዲሁም የተተውና የተወረሱ እቃዎች መጋዘን ቡድን እቃዎችን አለማስወገዱ እና በጉምሩክ ስነ ስርዓት አዋጅ የተቀመጠ የእቃዎች የቆይታ ጊዜ ተግባራዊ አለመደረጉ፣

101. በሞጆ ደረቅ ወደብ እቃዎች በአዋጁ ከተቀመጠው የጊዜ ገደብ በላይ የሚቆዩበት ምክንያት አስመጪዎች በወቅቱ ቀርበው የሚፈለግባቸውን ቀረጥ እና ታክስ ከፍለው እቃቸውን ባለማውጣታቸው መሆኑን እንዲሁም በአዋጁ መሰረት እርምጃ ለመውሰድ አዋጁ ከ60 ቀን በላይ የሆኑት ላይ እርምጃ ይወሰዳል ስለሚል በጨረታ እስከሚሸጥ ድረስ አስመጪ ቀረጥ እና ታክሱን ከፍሎ ለመውሰድ ከመጣ መውሰድ ይችላል ስለሚል ሌላ ተጨማሪ ወጪ ከመውጣቱ በፊት ኮሚቴ ተቋቁሞ ሰፊ ቅስቀሳ በመሰራቱ አስመጪዎች ቀርበው የሚፈለግባቸውን ቀረጥ እና ታክስ ከፍለው እንዲወስዱ መደረጉ፣

102. የኢትዮጵያ ባህር ትራንስፖርት ሎጀስቲክስ አገልግሎት ድርጅት የወደብና ተርሚናል አገልግሎት ዘርፍ ምክትል ዋና ስራ አስፈጻሚ ስለጉዳዩ ተጠይቀው ሲመልሱ በኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን የፍተሻ ስርአቱ በዘመናዊ መሳርያ ሳይሆን በሰው ሀይል የሚካሄድ መሆኑ፣ ተደጋጋሚ ፍተሻ መካሄዱ እና የንግድ ስርአቱ ችግር እንደምክንያት እንደሚጠቀስ ገልጸዋል፡፡

103. በነባራዊ ሁኔታ መግለጫ በተሰጠ ምላሽ እቃ የማስወገድ ስራ የተለያዮ አካላት ድርሻ ያላቸው በመሆኑና የመንግስት የጉምሩክ/ውርስ/ መጋዘን በወቅቱ ባለመመቻቸቱ እንዲሁም እቃዎቹ የሚወገዱበት ግልጽ አቅጣጫ እስከ 2007 ዓ.ም ማብቂያ ባለመቀመጡ ምክንያት እቃዎቹ ሳይወገዱ ቆይተዋል።ሆኖም በቁጥር 3.3.0/1000/08 ቀን 01/02/08 በተሰጠው አቅጣጫ መሰረት በሽያጭ የማስወገድ ስራው ተጠናክሮ የቀጠለ መሆኑ እቃውንም ከማስወገድ በፊት ቤት ለቤትና የተለያዮ የቅስቀሳ ስራዎች በመከናወኑ በርካታ እቃዎች በወቅቱ ከወደቡ እንዲወጡ ተደርጓል።በተጨማሪም በጉምሩክ አዋጅ አንቀጽ 51/5 ላይ 7 ቀን የጉምሩክ ስነ ሥርዓት ያጠናቀቀ እቃ መቆየት አይኖርበትም ተብሎ ቢገለጽም በቀጣይ በምን አይነት መልኩ እንደሚፈጸም ግልጽ አቅጣጫ ያልተቀመጠ በመሆኑ እንዲሁም በአስመጪው ቀረጥና ታክሱ ቀድሞ በመከፈሉ በጉምሩክ የሚፈለግ ጉዳይ ባለመኖሩ መስተንግዶ አሁንም እየተሰጠ ሲሆን አዋጁ እንዲሻሻልም እየተሰራ ይገኛል በማለት ተገልጿል፡፡

104. ባለስልጣን መ/ቤቱ በአዋጁ መሰረት የእቃዎች የቆይታ ጊዜ እንዳበቃ ከመጋዘን እንዲወጡ ባለማድረጉ በመጋዘኖች ላይ የቦታ መጣበብ እንዲፈጠር፣ በአዋጁ መሰረት ወቅታዊ እርምጃ የማይወሰድ ከሆነ ሌሎች ባለድርሻ አካላትም ሆኑ አስመጪዎች አዋጁን አክብሮ ለመንቀሳቀስ ዳተኝነት ሊያሳዮ ስለሚችሉ መንግስት ማግኘት ያለበትን ቀረጥና ታክስ በወቅቱ እንዳይሰበስብ ሊያደርግ የሚችል ከመሆኑም በላይ በከፍተኛ የውጭ ምንዛሬ የሚገቡ እቃዎች በመጋዘን በቆዮ መጠን የመጠቀሚያ ጊዜያቸው እየቀነሰ ሊሄድ እና የአገልግሎት ጊዜያቸው ሊያጥር ስለሚችል አሰራሩ ተገቢ ሆኖ አልተገኘም፡፡

## 2.3. ባለስልጣኑ ብቁና የተሟላ የሰው ኃይል ፣ በዘመናዊ ቴክኖሎጂ የታገዘ የመረጃ አጠቃቀም፣ አያያዝ እና ልውውጥ ያለው መሆኑን እንዲሁም ከባለድርሻ አካላት ጋር በቅንጅት የሚሰራበት የአሰራር ሥርዓት የዘረጋ እና ተግባራዊ ያደረገ መሆኑን መገምገም፤

**ባለስልጣኑ ወቅታዊና የክህሎት ክፍተትን መሰረት ያደረገ ስልጠና መስጠቱን እና የተሟላ የሰው ኃይል መቀጠሩን በተመለከተ፣**

105. ባለስልጣኑ በጉምሩክ ስነ ሥርዓት አፈጻጸም ላይ ያለውን የማስፈጸም አቅም ለማሳደግ እንዲችል ወቅታዊና የክህሎት ክፍተትን መሰረት ያደረገ ስልጠና ያገኘና የተሟላ የሰው ኃይል ሊኖረው ይገባል፡፡

106. የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን በማቋቋሚያ አዋጅ 587/2000 ከተሰጡት ስልጣንና ተግባራት መካካል የሠራተኞችን አቅም ለመገንባት የሚያስችለውን ማዕከል እንዲደራጅ

ያደርጋል፣የስልጠናና የሙያ ማሻሻያ ስርዓቶችን ይዘረጋል ቢልም አቅም ለመገንባት የሚያስችል ማዕከል ያልተደራጀ መሆኑ፣

107. በኦዲት ወቅት በናሙና ከታዩ ቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች መካከል በሞጆ ገቢዎችና ጉምሩክ የስልጠና አሰጣጥን በተመለከተ ከስራ ክፍሎች (የስራ ሂደት ቡድን) ፍላጎት ከተሰበሰበ በኋላ ካለው በጀት ጋር በማጣጣም ስልጠና ለመስጠት ጥረት እንደሚደረግ ነገር ግን ስልጠናዎች በቂ አለመሆናቸውን ምክንያቱም ያለው የስልጠና ፍላጎት እና ስልጠና ለመስጠት የሚመደበው በጀት በጣም ሰፊ ልዮነት ያለው መሆኑ ሲሆን በዋና መ/ቤት በኩል የሚደረገው ድጋፍ እና ክትትልም የሚፈለገውን ያህል አለመሆኑ፣ የስልጠና ማእከላት አለመኖር (ስልጠናዎች የአጭር፤የመካከለኛ እና የረጅም ግዜ መሆን ቢኖርባቸውም በቅርንጫፉ የሚሰጠው ግን የስራ ላይ ስልጠና ስለሆነ በቂ አለመሆን እና የቀጣይነት ችግር ያለው መሆኑ፣

108. የክህሎት ችግር (ከዋጋ አተማመን፣ፍተሻ፣ታሪፍ አመዳደብ) መንስኤ የሆነው ከፍተኛ ልምድ ያላቸው ሰራተኞች መልቀቅ ፣የስልጠና ማዕከላት አለመኖር (ስልጠናወች የአጭር ፣የመካከለኛ እና የረጅም ግዜ መሆን ቢኖርባቸውም በቅርንጫፉ የሚሰጠው ግን የስራ ላይ ስልጠና ስለሆነ በቂ አለመሆን፣በአዲስ አበባ ቃሊቲ ጉምሩክ በቅ/ጽ/ቤቱ አቅም ስልጠና ለመስጠት የበጀት እና የማቴርያል ችግር እንዳለ እና ሰራተኞችን በስልጠና የሚፈለገውን ያክል ያለማብቃት ችግር መኖሩ፣ በጋላፊ ጉምሩክ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት የቅርንጫፉን የስልጠና ፍላጎት መሰረት ያደረገ ስልጠና በዋናው መ/ቤት እንደማይሰጣቸው፣

109. በአዲስ አበባ ኤርፖርት ጉምሩክ የጉምሩክ ዋጋ ዝርዝር መግለጫ Valuations Details Declaration(VDD)፣Traders Risk Data Profile (TRDP) ላይ መደበኛ የሆነ ስልጠና በበላይ አካል ተዘጋጅቶ አለመሰጠቱ ሲስተሙን በጥራትና በተሟላ መንገድ ለመጠቀም እንቅፋት መፍጠሩ፣ከዘመኑ ቴክኖሎጂ መለዋወጥ ጋር በተገናኘ ከፍተሻ፣ከኤክስሬይ አጠቃቀም እና ኢንስፔክሽን አንጻር በቂ ስልጠና አለመሰጠቱን፣የሰራተኞችን ክህሎት ብቃት ለማሳደግ ተከታታይና ወቅታዊ የሆኑ ስልጠናዎች አለመሰጠቱ በአገልግሎት አሰጣጡ ላይ አላስፈላጊ ምልልሶችን መፍጠሩን፣ ተከታታይ የስፔር ፓርት ስልጠና ባለመሰጠቱ ምክንያት በፍተሻ ወቅት ችግሮች እያጋጠሙ መሆኑን በኦዲት ወቅት ከተከለሱ ማስረጃዎች እና ከቀረቡ ቃለ መጠይቆች ለመረዳት ተችሏል፡፡

110. በናሙና ከታዩ ቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች መካከል በጋላፊ ጉምሩክ ፣በአቃቂ፣በሞጆ እና በአዲስ አበባ ኤርፖርት ገቢዎችና ጉምሩክ ቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች በሚፈለገው መጠን የሰው ኃይሉ የተሟላ አለመሆኑን ከተከለሱ ማስረጃዎች ለማወቅ ተችሏል፡፡

111. በነባራዊ ሁኔታ መግለጫ በተሰጠ ምላሽ ከValuation Details Declaration(VDD) ጋር በተያያዘ በተለያየ ጊዜያት በተከታታይ እስከ 2000 ለሚደርሱ ፈጻሚ ሰራተኞች ስልጠና ቢሰጣቸውም ስልጠና ያገኙ ሰራተኞች በብዛት ከስራ በመልቀቃቸው ለማሰልጠን የተደረገው ጥረት ውጤታማ አልሆነም በማለት ተገልጿል፡፡

112. በባለስልጣን መ/ቤቱ ቋሚ የስልጠና ማዕከል ባለመኖሩ የሚሰጡ ስልጠናዎች ጥራት ዘላቂ አለመሆን እና ስትራቴጂክ የስልጠና እቅድ እንዳይኖር ማድረጉ፣የተሟላ የሰው ሀይል ባለመኖሩ አንድ ሰራተኛ ከክህሎቱ እና ከተመደበበት ስራ መደብ ውጪ ሌሎች ስራዎችን በተደራቢነት እንዲሰራ ሊገደድ መቻሉ ይህ በመሆኑም የአገልግሎት እና የቁጥጥር ስርዓቱን ቀልጣፋ እና ውጤታማ እንዳይሆን በማድረግ ለተገልጋዮችም ሆነ ለሰራተኞች የቅሬታ ምንጭ ሊሆን ይችላል፡፡

**በባለስልጣኑ ዘመናዊና ቀልጣፋ የሆነ የመረጃ አያያዝና ልውውጥ ስርዓት መኖሩን በተመለከተ፣**

113. ባለስልጣኑ በዘመናዊ ኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ የታገዘ የመረጃ አጠቃቀም ፣ አያያዝ እና ልውውጥ ሊኖረውና ተግባራዊ ሊያደርግ ይገባል፡፡

114. በኦዲት ወቅት በናሙና ከታዩ ቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች መካከል በጋላፊ ጉምሩክ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት የሲስተም ችግር የሎካል ኤርያ ኮኔክሽን ባለመኖሩ ቼክ ኢን እና ቼክ አውት ላይ በማንዋል የሚሰራ በመሆኑ የመረጃ ድግግሞሽ መኖሩ፤የዮኒሞዳል ትራንስፖርት ስርዓት በሲስተም አለመታገዝ ፣የስካኒንግ ማሽን ከአሲኩዳ ሲስተም ጋር አለመገናኘት፤ በአዲስ አባባ ኤርፖርት ፣ቃሊቲ፣ሞጆ እና አዳማ ገቢዎችና ጉምሩክ ቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች የመጋዘን አስተዳደር እና ቁጥጥር በዘመናዊ ቴክኖሎጂ ያልተደገፈ መሆኑ፣

115. በአዲስ አበባ ኤርፖርት ጉምሩክ ከሌሎች ቅ/ጽ/ቤቶች በሲስተም የትራንዚት ዲክላራሲዮን ተሞልቶላቸው በቅ/ጽ/ቤቱ በኩል የሚወጡ እቃወች በቅ/ጽ/ቤቱ በኩል እቃው ከሀገር ስለመውጣቱ በሲስተም የሚረጋገጥበት ሁኔታ ባለመኖሩ እቃው ከሀገር ስለመውጣቱ በደብዳቤ መገለጹ፣

116. በአዲስ አበባ ኤርፖርት ጉምሩክ የወጪ የኤክስፖርት መረጃ የኢትዮጵያ አየር መንገድ ወደ Automated System for Customs Data(ASYCUDA) ሲስተም ቢያስተላልፍም አሲኩዳ

ግን ይህን መረጃ ተቀብሎ የአየር መንገድ እና የጉምሩክ መረጃ ለማስታረቅ በሚቻል መልኩ ለመጠቀም ያላስቻለ መሆኑ፤በተጨማሪም የወጪ እቃ አሰሰሮች እና ፈታሾች የአሰስመንት፤የፍተሻ እና እቃው ጊዜያዊ መጋዘን ስለመግባቱ እና ከአገር ስለመውጣቱ የሚያሳይ ምንም የሲስተም ግብአት የሌለ በመሆኑ የወጪ እቃ ላይ አንድ እቃ በትክክል ከአገር ስለመውጣቱ ሀርድ ኮፒ እንጂ የአሲኩዳን ሲስተም መሰረት አድርጎ ለማወቅ የማይቻል መሆኑ ይህ በመሆኑም የእቃዎች ሳይላኩ መቅረት እና Offload እንደሚያስከትል፤ችግሩን ለመፍታት ከመረጃ ቴክኖሎጂ ቡድን ጋር ለመስራት ተሞክሮ እንዳልተቻለ ፤

117. ከጅቡቲ በዩኒሞዳል ተጓጉዘው ለሚመጡ ተሽከርካሪዎች ከጅቡቲ የሚላከው የካርጎ ዲስፓች ሪፖርት በሲስተም ወይም በሶፍትዌር አለመደገፉ፤በመልቲሞዳል ተጓጉዘው ለሚመጡ ተሽከርካሪዎች ሙሉ ለሙሉ በሲስተም ወይም በአሲኩዳ ከሚሆን ይልቅ በማንዋል ጭምር እንዲሰራ በመደረጉ በወቅቱ ቫሊዴት እንዳይደረግ በአሰራር ችግር መፍጠሩ፤እቃዎች በዮኒሞዳል ተፈቅደው በመልቲሞዳል ትራንስፖርት ተጓጉዘው መምጣት፤የመልቲሞዳል ሪኮንሲሊዮሽን በሲስተም ያልተደገፈ አመቺ ያልሆነ እና ግዜ የሚፈጅ መሆኑ፤በመረጃ ቴክኖሎጂ የተደገፈ መረጃ አያያዝ ስርዐት አለመኖሩ፤የትራንዚት ኢንስፔክሽን አክት በሲስተም የተደገፈ አለመሆኑ፤

118. የኢትዮጵያ የጉምሩክ ዋጋ መረጃ ስርዓት የአምራቾችንና የአስመጭዎችን ዘርፍ ያለየ መሆኑ፤የተሟላ የዋጋ መረጃ ይዞ አለመገኘትና በአግባቡ መስራት ያለመቻሉ ወጥነት ያለው የዋጋ ውሳኔ ለመወሰን አስቸጋሪ ያደረገው መሆኑን በኦዲቱ ወቅት ከተከለሱ መረጃዎች እና ከቀረቡ ቃለ መጠይቆች ለመረዳት ተችሏል ፡፡

119. ባለስልጣን መ/ቤቱ ሁሉንም ያማከለ የመረጃ ቴክኖሎጂ ስርዓት ባለመዘርጋቱ የመረጃ ቅብብሎሹን አዝጋሚ በማድረግ ወቅታዊ ውሳኔዎች እንዲዘገዮ ከማድረጉም በላይ ስራዎች በዘመናዊ የመረጃ ቴክኖሎጂ የታገዙ ቢሆኑ ኖሮ በማንዋል የሚሰሩ የቁጥጥር ስራዎችን በማስቀረት አገልግሎት አሰጣጡንም ሆነ የቁጥጥር ስርዓቱን ሚዛናዊና ቀልጣፋ ማድረግ ይቻል ነበር፡፡

**በባለስልጣኑ የአንድ መስኮት አገልግሎት ስርዓት የተዘረጋ እና ተግባራዊ የተደረገ መሆኑን በተመለከተ፣**

120. ባለስልጣኑ የወጪ እና ገቢ እቃዎችን በሚመለከት የአንድ መስኮት አገልግሎት ለመስጠት እንዲቻል የሚመለከታቸው የመንግስት መ/ቤቶችና የፋይናንስ ተቋማት በተዘረጋው የኤሌክትሮኒክስ መረጃ ልውውጥ ስርዓት ተጠቃሚ እንዲሆኑ ሁኔታዎችን ሊያመቻች ይገባል፡፡

121. በባለስልጣን መ/ቤቱ የተቀረጹት አዳዲስ የጉምሩክ የአሠራር ሥርዓቶች የተቀላጠፈ አገልግሎት እና ውጤታማ ቁጥጥርን በተጣጣመ መልኩ ለማስፈጸም እንዲያስችሉ ሲባል ዘመናዊ የመረጃ እና ሌሎች ቴክኖሎጂዎችን መሠረት ያደረጉ እንዲሆኑ ተደርጓል፡፡

122. በዚህ መሰረት ባለስልጣኑ ስራዎቹን በዘመናዊ ቴክኖሎጂ ለመደገፍ እና የኤሌክትሮኒክስ አንድ መስኮት አገልግሎት ለመስጠት እንዲያስችለው ከInvestment Climate for Africa(ICF)፣አለም ባንክ (IFC) እና ከመንግስት በተገኘ የፕሮጀክት በጀት 7.3 ሚሊየን የአሜሪካን ዶላር በታህሳስ ወር 2006 ዓ.ም የፕሮጀክት ስምምነት በመፈረም በአስራ ስምንት ወራት ለማጠናቀቅ በይፋ ስራውን የጀመረ ቢሆንም ፕሮጀክቱ ሲጀመር በቂ ዝግጅት ባለመደረጉና የሚመለከታቸውን ባለድርሻ አካላት በዋናነት (የኢንፎርሜሽን መረብ ደህንነት ኤጀንሲ) ያላሳተፈ በመሆኑ፣ ኤጀንሲውን ለማሳተፍ ረዥም ጊዜ በመውሰዱ፣በዝግጅት ጊዜ መከናወን የነበረባቸው የሌሎች ሀገራት ተሞክሮዎች አለመከናወናቸው፣ከመንግስት የሚጠበቅ ውሳኔ በወቅቱ አለመገኘት፣የፕሮግራሙ ከፍተኛ አመራሮች ከፍተኛ የመንግስት የስራ ሀላፊዎች በመሆናቸው በተለያዩ ሀገራዊ ጉዳዮች የነበራቸው ተሳትፎ ከፍተኛ በመሆኑ ለፕሮግራሙ የሚያስፈልጉ ውሳኔዎችን በወቅቱ አለማግኘት፣የፕሮግራም ጽ/ቤቱ በተገቢው ደረጃ አለመደራጀት እና የሚያስፈልገውን የሰው ሀይል ባለመያዙ ምክንያት ወደ ትግበራ ምእራፍ መግባት እንዳልቻለ በኦዲት ወቅት ለማወቅ ተችሏል፡፡

123. በተጨማሪም በመጀመሪያ ምዕራፍ ስርዓቱን ለመጀመር የታሰበው አስር በሚሆኑ ዋናዋና ባለድርሻዎች እና በሂደት ለማስፋት ሲሆን በሂደት በተገኘ ተሞክሮ እና ከመንግስት በተሰጠ አቅጣጫ ሁሉንም ባለድርሻዎች በሙሉ የሚያካትት ፕሮግራም በአዲስ መልክ በመቅረጽ የትግበራ ጊዜው እ.ኤ.አ ወደ 2019 የተገፋ መሆኑን እና የፕሮጀክቱ በጀት 32 ሚሊዮን የአሜሪካን ዶላር የተገመተ መሆኑን ለማወቅ ተችሏል፡፡

124. በባለስልጣኑ የአንድ መስኮት አገልግሎት ፕሮጀክት በዝግጅት ምእራፍ ሊከናወኑ የሚገባቸው ስራዎች ቀድመው ታሳቢ ባለመደረጋቸው እና ፕሮጀክቱ ሲጀመር በቂ ዝግጅት ባለመደረጉ

በተፈጠረው የፕሮጀክቱ ትግበራ መጓተት ምክንያት ተቋሙ ፕሮጀክቱ ተጠናቆ ሊያገኘው የሚገባውን ቀልጣፋ፣ ወጪ ቆጣቢና ቀላል የሆነ የአሰራር ስርዓት እንዳይኖረው፤ ግልጽ፣ ወጥ እና ለክትትል አመች የሆነ የአሰራር ሂደትን በማስፈን ለሙስናና ብልሹ አሰራር የሚያጋልጡ ሂደቶችንና ልማዳዊ አሰራሮችን ከመቅረፍ አኳያ የሚኖረውን ጠቀሜታ የሚያሳጣ መሆኑን ለመረዳት ተችሏል፡፡

**በባለስልጣኑ ስለሚደረጉ የክትትልና ድጋፍ ስራዎች በተመለከተ፣**

125. ባለስልጣን መ/ቤቱ በየቅርንጫፍ ጽ/ቤቶችና መቆጣጠሪያ ጣቢያዎች ያሉ የጉምሩክ አሰራሮች ወጥነት ያላቸው ስለመሆኑ በተለያየ ጊዜ የዳሰሳ ጥናት ሊያካሂድና በጥናቱ የተገኙ በአሰራር ያጋጠሙ ግድፈቶች እንዲታረሙና ምርጥ ተሞክሮዎች በሁሉም የቅርንጫፍ መ/ቤቶች እንዲተገበሩ ሊያደርግ ይገባል፡፡ባለስልጣን መ/ቤቱ በቅርንጫፍ መ/ቤቶችና በመቆጣጠሪያ ጣቢያዎች የሚሰራው የክትትልና የድጋፍ አሰጣጥ ስራ በተያዘለት ጊዜ መሰረት ሊከናወንና በአፈፃፀም ወቅት ላጋጠሙ ችግሮች ወቅታዊ ምላሽ ሊሰጥ ይገባል፡፡

126. በኦዲት ወቅት በናሙና ከታዩ ቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች መካከል በአዲስ አበባ ኤርፖርት ቅ/ጽ/ቤት የአየር ክልል ቡድን እና የማንፌስት ቡድን ለንግድ እቃዎች ካርጎ አለመጠናቱን እንዲሁም የንግድ ዕቃዎች ካርጎ ቡድን ላይ አስራ ስድስት ሰአት እንደሚሰራ ቡድን አስተባባሪው ግን አንድ ሰው ስለሆነ ስምንት ሰአት ብቻ ስለሚሰራ ለቁጥጥር አዳጋች መሆኑ፣

127. በጋላፊ ጉምሩክ የመዋቅር ችግር መኖሩ (ቼክ ኢን፤ማንፌስት እና ትራንዚት ቁጥጥር ተለያይተው መሰራት ቢኖርባቸውም በማንፌስት ኦፊሰር መሰራቱ፤አንድ ቡድን አስተባባሪ እስከ አራት ክፍል ደርቦ መስራቱ እና ኢንስፔክሽን አክት እንደማይሞላ፣በስካኒንግ ማሽን ፍተሻ ተጨማሪ ሰነድ በሚጠየቅበት ጊዜ መድረሻ ቅ/ጽ/ቤቶች በወቅቱና በግዜው የሚፈለገውን Packing list በተለይ ከአዳማና መቀሌ ስለማይላክ ለስራ እንቅፋት ለደንበኞችም መጉላላት መፍጠሩ (የተለያየ አይተም ያላቸው እቃዎች በአንድ ኮንቴይነር ተጭነው መጥተው ወደ ስካኒንግ ማሽን ሲገቡ ስካኒንግ ማሽኑ የእቃ ልዮነት ስለሚያሳይ ይህንን የሚያስረዳ ፓኪንግ ሊስት ቅ/ጽ/ቤቶች ሲጠየቁ ቀና ምላሽ ስለማይሰጡ አሳጅቦ መላኩን እንደአማራጭ መወሰዱ፣

128. ለአዳማ ገቢዎችና ጉምሩክ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት በቀረበ መጠይቅ በተለያዮ የተቋሙ ቅ/ጽ/ቤቶች ወደ Ethiopian Customs Valuation System (ECVS) የሚገቡ ለአንድ አይነትና ተመሳሳይ እቃዎች የተለያየ ዋጋዎች ተሰጥተው የሚገኙ መሆኑ እንዲሁም የተለያየ ዋጋ

ሲኖር አማካዮን እንዲወሰድ አቅጣጫ ቢቀመጥም አማካይ የሚሰራው ማንዋሊ ስለሆነ እና የተለያዩ ዋጋዎች በተለያየ ወቅት ስለሚገቡ የተለያየ አማካይ መገኘቱ፣

129. በተለያየ ምክንያት በአንድ የጉምሩክ ቅ/ጽ/ቤት የግብር ከፋይ መለያ ቁጥር የሲስተም እገዳ የተደረገባቸው አስመጪዎች ግዴታቸውን መፈጸማቸው ሳይረጋገጥ በሌሎች ቅ/ጽ/ቤቶች እገዳው እየተነሳ መሆኑን አስመልክቶ ቃለ-መጠይቁ የቀረበላቸው የሞጆ ጉምሩክ ቅ/ጽ/ቤት የደንበኞች አገልግሎት ቡድን አስተባባሪ በሰጡት ምላሽ አስመጪዎችን ከሲስተም ማገድ ህጋዊ መሰረት ባይኖረውም ያልተከፈሉ ቀሪ ሂሳቦችን እንዲከፍሉ ለማስገደድ የተወሰደ አማራጭ መሆኑን እና አሁንም አሰራሩ የቀጠለ መሆኑን፤አስመጪዎቹ የታቀደ ገቢን ሊያሳካ የሚችል አዲስ ሰነድ ሊከፍሉ ሲመጡ ጉምሩክ ስነ-ስርአት አሳማኝ ምክንያት ሲቀርብለት ለጊዜው በበፊት ክፍያ(ቀሪ) የታገደ ለጊዜው እንዲከፈት እየመራበት እንደሚነሳ ገልጸዋል፣የአሰራር ክፍተት (የዋጋ አተማመን፤አደረጃጀት፤መመሪያው እና አሰራሩ የተለያየ ዋጋ እንዲሰጥ ክፍተት መፍጠሩን ፣ወቅታዊ የሆነ የዋጋ መረጃ አለመኖር ዋነኛ የቅሬታ ምንጭ መሆኑን፣በአዲስ አበባ ኤርፖርት ጉ/ቅ/ጽ/ቤት በመኪና እቃ መለዋወጫ ላይ ያነሱ ዋጋዎች ይገባሉ ለምሳሌ፡-fuel filter (Toyota) መለያ ቁጥር 90915-yzze 1, fuel filter 1917946,BEARING BALL PART NO 5920032 (C 65479/14), BEARING PART NUMBER 39143520(C-72572-16,OIL FILTER PART NUMBER AA 121010(C-6579/14) በመሆኑም በቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች በኩል የሚወሰኑ የዋጋ ውሳኔዎች ወጥነት የሌላቸው መሆኑን፣

130. በአዲስ አበባ ቃሊቲ ጉምሩክ በቅ/ጽ/ቤቱ እና በሞጆ ቅ/ጽ/ቤት የሚወሰኑ በርካታ የዋጋ ውሳኔዎች የተለያዮ በመሆናቸው ከተገልጋዮች ቅሬታ እየተነሳ መገኘቱ ችግሩ ግን በሞጆ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት ብቻ የሚወሰን እንዳልሆነና በሌሎች ቅርንጫፍ ጽ/ቤቶችም ተመሳሳይ ችግር እንዳለ መንስኤውም የክህሎት ችግር፤ፍርሀት(ከፍ ያለ ዋጋ በሚጣልበት ወቅት ተጠያቂ የመሆን እድሉ አናሳ ሲሆን ዝቅ ተደርጎ ዋጋ በሚወሰንበት ጊዜ ተጠያቂ እንሆናለን የሚል አመለካከት መኖሩ)፤የዋጋ አደረጃጀት ችግር (ሁሉም መረጃዎች ኢሲቪኤስ ላይ አለመገኘት እና የትራንዚተሮች Value Details Declaration (VDD) በትክክል አለመሙላት መሆናቸውን በተጨማሪም ከEthiopian Customs Valuation System (ECVS) የተለያየ አይተም በሚኖርበት ጊዜ  መረጃ ለማግኘት ግዜ መፍጀቱን ጠቅሰው ችግሩን ለመፍታት ከሞጆ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት ጋር ተወያይተው ወጥነት ያለው ዋጋ እንዲኖር ጥረት እንደተደረገ በቃለ መጠይቅ ወቅት በሰጡት ምላሽ ለማወቅ ተችሏል፡፡

131. በነባራዊ ሁኔታ መግለጫ በተሰጠ ምላሽ የእቃዎች ዋጋ አተማመን ላይ የሚታዩ የወጥነትና የአተገባበር ክፍተቶችን አስመልክቶ ለተነሳው እንደተቋም የእቃዎች ዋጋ ወቅታዊ ለማድረግ ጥረቶች እየተደረጉ ቢሆንም በአንድ ጊዜ የሁሉንም እቃዎች የዋጋ መረጃ ወቅታዊ ማድረግ ካለው የሰው ሀይል እና የመረጃ እጥረት አንጻር አስቸጋሪ መሆኑ ከግምት ውስጥ ሊገባ ይገባል የሚል ምላሽ ተሰጥቷል፡፡

132. ባለስልጣን መ/ቤቱ በየቅርንጫፍ ጽ/ቤቱ ያሉ አሰራሮችና ውሳኔዎች ወጥ እንዲሆኑ ቋሚ የሆነ የክትትል እና የቁጥጥር ስራ ካልሰራ ተቋሙ ሊያሳካ የሚፈልገውን አላማ እንዳያሳካ ከማድረጉም በላይ ለተገልጋዮች የቅሬታ ምንጭ ሊሆን ይችላል፡፡

**በባለስልጣኑ ከባለድርሻ አካላት ጋር ስለሚደረጉ የጋራ የውይይት መድረኮች በተመለከተ፣**

133. ባለስልጣኑ የጉምሩክ ስነ-ስርዓትን በተመለከተ ከባለድርሻ አካላት ጋር መደበኛ እና ተከታታይነት ያለው የመወያያ መድረክ ሊኖረው እና በመድረኩ የሚነሱ ጉዳዮችን የሚፈታበት ስርአት ሊኖረው ይገባል፡፡

134. የአዲስ አበባ ኤርፖርት ቅ/ጽ/ቤት በኤርፖርት ቅጥር ግቢ ውስጥ ከሚገኙ ተጓዳኝ መ/ቤቶች ጋር የሚኖረውን የጎንዮሽ የስራ ግንኙነት በተመለከተ የጋራ የመግባቢያ ሰነድ አለመኖሩ በአሰራር ላይ እያንዳንዱ የራሱን ድርሻ ለይቶ እንዳያውቅ ያደረገው ከመሆኑም በላይ በአሰራር ላይ ለስራው እንቅፋት የሚፈጥሩ አለመግባባቶችን እያስከተለ መሆኑ፣ከተጓዳኝ መ/ቤቶች ፣ከጉምሩክ አስተላላፊዎች፣ፖርተሮች እና እቃ አጓጓዥ ድርጅቶች ጋር በመደበኛነት የውይይት መድረክ አለመዘጋጀቱ፣የአዲስ አበባ ኤርፖርት ቅ/ጽ/ቤት ከኢትዮጵያ አየር መንገድ ጋር መረጃ በመቀያየር፣መጋዘን በማስተዳደር እና በሌሎች አጠቃላይ ተያያዥነት ባላቸው ጉዳዮች ላይ መስራት በሚገባቸው ደረጃ ተባብረው ባለመስራታቸው ምክንያትና ተቋማቱ ባላቸው የውስጥ አሰራር ክፍተት ምክንያት ለህገወጥነት ትልቅ በር መክፈቱን ለመረዳት ተችሏል፡፡

135. ሞጆ ገቢዎችና ጉምሩክ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት ከባለድርሻ አካላት ጋር የሚያደርጉት ውይይት መደበኛ እንዳልሆነ፣የደረቅ ወደብ ባለቤት የሆነው የኢትዮጵያ ባህር ትራንስፖርትና ሎጀስቲክስ አገልግሎት ድርጅት ጋር በመጋዘን አካባቢ የጉምሩክ ሚና ምን መሆን እንዳለበት እና የድርጅቱ ሚና ምን መሆን እንዳለበት በግልጽ ባለመቀመጡ ይህ ደግሞ በሁለቱ መ/ቤቶች መካከል አለመግባባት ፈጥሮ እንደነበር፣

136. ከተጓዳኝ ባለድርሻ አካላት የባሕር ትራንስፖርትና ሎጂስቲክ አገልግሎት ድርጅት (ባትሎአድ)፣ ከኢትዮጵያ አየር መንገድ፣ አስመጪዎች/ግብር ከፋዮች እና ሌሎች) ጋር ተቀናጅቶ ቀጣይነት ባለው መልኩ አለመሥራት፣

137. በአዲስ አበባ ቃሊቲ ጉምሩክ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት ከተጓዳኝ መ/ቤቶች ጋር ያለው ግንኙነት ሊፈተሽ የሚገባው ጉዳይ መሆኑ ለምሳሌ በባሕር ትራንስፖርትና ሎጂስቲክ አገልግሎት ድርጅት ችግር ጉምሩክ ተወቃሽ መሆኑ፤ከንግድ ፍቃድ አሰጣጥ ጋር የተያያዘ ችግር መኖሩ)፣ ከባለድርሻ አካላት ጋር በመወያየትና በመነጋገር በአመት ውስጥ የሚገናኙበትን የግንኙነት ጊዜ ባለማስቀመጣቸው ምክንያት ውይይቶች የተሟሉ አለመሆን፣ከባለድርሻ አካላት ጋር ተቀናጅቶ የመሰራት ውስንነቶች መኖራቸው፣በባትሎአድ እና በቃሊቲ ጉምሩክ በኩል የሚሰራው የኮማንድ ፖስት ስራ በአግባቡ ባለመስራታቸው እና የማስተካከያ እርምጃ በወቅቱ ባለመወሰዱ በመጋዘን በኩል አገልግሎቱን የሚጎዱ ተግባራትና አመለካከቶች ያልተፈቱ መሆናቸው፣በኦዲት ወቅት ከተከለሱ መረጃዎች እና በቃለ መጠይቅ ወቅት ለማወቅ ተችሏል፡፡

138. ጉዳዮን አስመልክቶ ለመ/ቤቱ በቀረበው ነባራዊ ሁኔታ መግለጫ በተሰጠ ምላሽ መቆራረጥ የሚታይበት መደበኛ የግንኙነት መድረክ ቢሆንም ችግሮችን ለመፍታት መደበኛ መድረክ ሳያስፈልግ ወዲያውኑ ከሚመለከተው ባለድርሻ አካል ጋር በመነጋገር ችግሮች የተፈጠሩበት ቦታ በመገኘት እየተፈታ ይገኛል፡፡በቀጣይም ግንኙነቱ እንዲጠናከር ያላሰለሰ ጥረት ይደረጋል፡፡በሌላ በኩል የባህር ትራንስፖርትና ሎጆስቲክስ አገልግሎት ድርጅት እና የባለስልጣን መ/ቤቱ ሀላፊነትና ሚና በግልጽ የተቀመጠ መሆኑ በውይይት ወቅትም ያጋጠሙ ችግሮችን በጋራ በመወያየት ችግሮችን ለመፍታት ጥረት ይደረጋል፡፡ከዚህ በተጨማሪ በሁለቱ አካላት መካከል መግባባት ያልተደረሰባቸው ጉዳዮች ለኦፐሬሽን ኮሚቴ እየቀረቡ አቅጣጫ እንዲሰጥበት እየተደረገ በመሰራት ላይ ይገኛል በማለት ተገልጿል፡፡

139. ባለስልጣን መ/ቤቱ ቋሚና ተከታታይ የግንኙነት ጊዜ ከሌለው በተለይ ከተጓዳኝ እና ከባለድርሻ አካላት ጋር የሚያዘጋጃቸው የውይይት መድረኮች በሌሎች ባለድርሻ አካላት መልካም ፈቃድ ላይ የተመሰረተ ስለሆነ የቀጣይነትም ሆነ በውይይቱ ወቅት ለሚሰጡ የመፍትሔ ሃሳቦች የማስፈጸም ቁርጠኝነት ማነስ ሊያስከትል ይችላል፡፡

## ክፍል ሦስት

## መደምደሚያ

140. በሪፖርቱ ክፍል ሁለት ከተዘረዘሩት ችግሮች እና የአሰራር ግድፈቶች በመነሳት በእኛ አስተያየት፤

- ነዳጅ ጭነው ወደ አገር ውስጥ ለሚገቡ ተሽከርካሪዎች ዲክላራሲዮን እና የመንገድ ወረቀት (T1) አይዘጋጅም፣ የአሰራር ስርዓት አልተዘረጋም፣የወጪ ትራንዚት እቃ ትክክለኛነት ሲጫን በአካል ተገኝቶ በማረጋገጥ በሲል ማሸግ እና ሲል ቁጥሩን በአውቶሜሽን ሲስተም በመመዝገብ ትራንዚቱ እንዲጀምር የሚያደርግ አሰራር ተግባራዊ አልተደረገም፡፡
- በሀገር ውስጥ ተመርተው ወይንም እሴት ተጨምሮባቸው ለውጭ ገበያ የሚላኩ ምርቶች የሚታሸጉበት ደረጃውን የጠበቀ ማሸጊያ /ሲል/ የሌለ በመሆኑ ህገ ወጥነትን ለመቆጣጠር በማይቻልበት መንገድ በሽቦ እና ጠጠር ብቻ እየታሰረ ወደ ውጭ እየተላከ እንደሚገኝ ለማወቅ ተችሏል፡፡
- በመልቲሞዳል ስርዓት ተጓጉዘው ወደአገር የገቡ ጭነቶች ሪኮንሲሊዮሽን በሲስተም የታገዘ ባለመሆኑ ወቅታዊነት እንደሚጎድለው እና የት እንደተራገፉ የማይታወቁ እና በሲስተም ቫሊዴት ያልተደረጉ ጭነቶች መኖራቸውን ለማወቅ ተችሏል፡፡
- ባለስልጣኑ የኤሌክትሮኒክስ የጭነት መቆጣጠሪያ ስርዓት(Electronics Cargo Tracking and Monitoring System) ከጥር 2003 ዓ.ም ጀምሮ በአምስት አመታት ጊዜ ውስጥ በትንሹ 10,000 ተሽከርካሪዎችን ወደ ስርአቱ በማስገባት ወደ ሙሉ ትግበራ እንደሚገባ በውል ስምምነቱ ቢገለጽም እስከ 2008 በጀት አመት መጨረሻ 312 (3%) ተሽከርካሪዎች ብቻ የካርጎ ትራኪንግ መሳሪያ የተገጠመላቸው መሆኑ እና የተዘረጋው የካርጎ ትራኪንግ ሲስተም ከኢትዮጵያ መግቢያ በር ጋላፊ ጀምሮ ሲሆን በውሉ መሰረት ከጅቡቲ ወደብ እስከ ጋላፊ ባለው ስፍራ ስርአቱ ያልተዘረጋ መሆኑ፣
- በመልቲ ሞዳል ስርዓት ተጓጉዘው በሲስተም ያልተገኙ ሰነዶች ከተስተናገዱ በኋላ ተከታትሎ የመንገድ ወረቀት አለማዘጋጀት እና የተዘጋጀውን የመንገድ ወረቀት ቁጥር ለመድረሻ ጣቢያ አለማሳወቅ ፣ በማንዋል የተሰሩ የመልቲሞዳል ጭነቶች ወደ ሲስተም አለማዞር፤የመልቲሞዳል ጭነቶች ዝርዝር በየእለቱ ከመግቢያ በር ወደ መድረሻ ጣቢያዎች የማይላክ መሆኑ፣

- በባለስልጣኑ በስምንት የጉምሩክ መቆጣጠሪያ ጣቢያዎች በዘመናዊ የፍተሻ መሳሪያ (Scanning Machine) የታገዘ አገልግሎት ለመስጠት ታቅዶ ወደ ስራ የተገባ ቢሆንም ከስምንቱ ውስጥ በጋላፊ ጉምሩክ ቅርንቻፍ ጽ/ቤት ብቻ አገልግሎቱ እየተሰጠ ሲሆን በቀሪዎቹ ሰባት ጣቢያዎች አገልግሎቱ አልተጀመረም፡፡
- በአዲስ አበባ ኤርፖርት ጉምሩክ ቅ/ጽ/ቤት በ190 የማስጫኛ ሰነድ የመጡ ግምታዊ የቀረጥና ታክስ ዋጋ ብር 101,932,491.10 ያላቸው ጭነቶች አስፈላጊው የጉምሩክ ስነ ስርዓት ሳይፈጸምባቸው አየር በአየር ከመጋዘን ወጪ የተደረጉ መሆኑ፣
- በባለስልጣኑ የጉምሩክ አዋጅ 859/2006 አንቀጽ 6(4) መሰረት መ/ቤቱ የገቢ፣የወጪ እና የተላላፊ እቃዎችን በሚመለከት የሚኖር የስጋት ደረጃን የሚወስን መመሪያ ያላወጣ መሆኑን ለማወቅ ተችሏል፡፡
- በ2007 እና በ2008 በጀት ዓመት የቀይ ስጋት ደረጃን ዝቅ ለማድረግ የተያዘው ዕቅድ ማሳካት ያልተቻለ መሆኑ፣
- በአዋጅ ቁጥር 859/2006 የተቀመጡ ግዴታዎች እና ስለጉምሩክ መጋዘን አስተዳደር የወጣ የአፈፃፀም መመሪያ ቁጥር 40/2002 ላይ የተቀመጡ መስፈርቶች ሳያሟሉ የሚሰሩ የጉምሩክ መጋዘኖች ያሉ መሆኑ፣
- ጊዜያዊ የጉምሩክ የዕቃ ማከማቻ መጋዘኖች ዕቃዎች እንደአይነታቸውና እንደባህሪያቸው ተለይተው ለደህንነታቸው ተስማሚ በሆነና ለጉምሩክ ቁጥጥር አመቺ በሆነ ሁኔታ ያልተቀመጡ መሆናቸው፣በባለስልጣኑ አዋጅ ቁጥር 859/2006 አንቀጽ 59 ንዑስ አንቀጽ 2 መሰረት የጉምሩክ መጋዘን ኪራይ ማስከፈያ ተመን ደንብ ያልወጣ መሆኑን ለማወቅ ተችሏል፡፡
- በጉምሩክ መጋዘን የዕቃዎች በመጋዘን የቆይታ ጊዜ በጉምሩክ አዋጅ ቁጥር 859/2006 በተቀመጠው መሰረት ተግባራዊ ያልተደረገ መሆኑ፣
- የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን በማቋቋሚያ አዋጅ 587/2000 ከተሰጡት ስልጣንና ተግባራት መካካል የሠራተኞችን አቅም ለመገንባት የሚያስችለውን ማዕከል እንዲደራጅ ያደርጋል፣የስልጠናና የሙያ ማሻሻያ ስርዓቶችን ይዘረጋል ቢልም አቅም ለመገንባት የሚያስችል ማዕከል አልተደራጀም፡፡የሚፈለገው የሰው ኃይል አልተሟላም፡፡
- የስካኒንግ ማሽን ከአሲኩዳ ሲስተም ጋር ያልተገናኘ መሆኑ፣ በአዲስ አባባ ኤርፖርት ፣ቃሊቲ፣ሞጆ እና አዳማ ገቢዎችና ጉምሩክ ቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች የመጋዘን አስተዳደር እና ቁጥጥር በዘመናዊ ቴክኖሎጂ ያልተደገፈ መሆኑን፣

- ባለስልጣኑ የኤሌክትሮኒክስ አንድ መስኮት አገልግሎት ለመስጠት እንዲያስችለው በታህሳስ 2006 ዓ.ም የፕሮጀክት ስምምነት በመፈራረም በአስራ ስምንት ወራት ለማጠናቀቅ በይፋ ስራው ተጀምሮ ፕሮጀክቱ ሳይጠናቀቅ ወደ ፕሮግራም ተቀይሮ በሂደት ላይ ቢሆንም ትግበራው የተጓተተ መሆኑ፡፡
- በባለስልጣኑ በኩል በቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች የሚሰሩ ስራዎች ወጥነት እንዲኖራቸው የሚከናወኑ የድጋፍና ክትትል ስራዎች አነስተኛ መሆናቸው፣
- ባባለስልጣኑ የጉምሩክ ቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች ከባለድርሻ አካላት ጋር የሚደረጉ ውይይቶች ወጥነትና ተከታታይነት የሚጎድላቸው መሆኑ፣

## ክፍል አራት

## የማሻሻያ ሃሣቦች

141. **በባለስልጣኑ የተዘረጋው የጉምሩክ የትራንዚት ሥነ-ስርዓት በሁሉም የጉምሩክ መቆጣጠሪያ ጣቢያዎች ተግባራዊ መደረጉን በተመለከተ፣**

- ነዳጅ ጭነው ወደ አገር ውስጥ ለሚገቡ ተሽከርካሪዎች የአሰራር ስርዓት ሊዘረጋ እና የወጪ ትራንዚት እቃ ትክክለኛነት ሲጫን በአካል ተገኝቶ በማረጋገጥ በሲል ማሸግ እና ሲል ቁጥሩን በአውቶሜሽን ሲስተም በመመዝገብ ትራንዚቱ እንዲጀምር የሚያደርግ አሰራር ተግባራዊ ሊደረግ ይገባል፡፡
- ባለስልጣኑ በሀገር ውስጥ ተመርተው ወይንም እሴት ተጨምሮባቸው ለውጭ ገበያ የሚላኩ ምርቶች የሚታሸጉበት ደረጃውን የጠበቀ የጉምሩክ ማሸጊያ ሊጠቀም ይገባል፡፡
- በመልቲሞዳል ስርዓት ተጓጉዘው ወደአገር የገቡ ጭነቶች የማስታረቅ ስራ በወቅቱ ሊሰራ እና የት እንደተራገፉ የማይታወቁ እና በሲስተም ቫሊዴት ያልተደረጉ ጭነቶች ተጣርተው ተገቢው የማስተካከያ እርምጃ ሊወሰድ ይገባል፡፡
- ባለስልጣኑ የኤሌክትሮኒክስ የጭነት መቆጣጠሪያ ስርዓት (Electronics Cargo Tracking and Monitoring System) በሁሉም ገቢና ወጪ ዕቃዎችን በሚጭኑ ተሽከርካሪዎች ላይ ከጅቡቲ ወደብ እስከ መዳረሻ ቦታች ተግባራዊ ሊያደርግ ይገባል፡፡
- በመግቢያ በር በመልቲ ሞዳል ስርዓት ተጓጉዘው በሲስተም ያልተገኙ ሰነዶች ከተስተናገዱ በኋላ ተከታትሎ የመንገድ ወረቀት ሊዘጋጅላቸው እና የተዘጋጀው የመንገድ ወረቀት ቁጥር ለመድረሻ ጣቢያ የማሳወቅ ስራ በወቅቱ ሊሰራ ይገባል፡፡
- በባለስልጣኑ በጉምሩክ መቆጣጠሪያ ጣቢያዎች የአገልግሎት አሰጣጡን እና የቁጥጥር ስርዓቱን ሊያሻሽሉ የሚችሉ ዘመናዊ የፍተሻ መሳሪያ (Scanning Machine) ሊጠቀም ይገባል፡፡
- እቃዎች አስፈላጊው የጉምሩክ ስነ ሥርዓት ሳይፈጸምባቸው እንዲወጡ ክፍተት የፈጠሩ የአሰራር ስርዓቶችን በመለየት የማስተካከያ እርምጃ እንዲወሰድ እና የተዘረጉ የአሰራር ስርዓቶች በትክክል እየተተገበሩ መሆኑን የመከታተል እና የማረጋገጥ ስራ ሊሰራ ይገባል፡፡

142. **የጉምሩክ ዕቃ አወጣጥ ሥነ-ሥርዓት በብቃት እና በቅልጥፍና የሚከናወን መሆኑን ማረጋገጥ በተመለከተ፣**

- በባለስልጣኑ የጉምሩክ አዋጅ 859/2006 አንቀጽ 6(4) መሰረት መ/ቤቱ የገቢ፣የወጪ እና የተላላፊ እቃዎችን በሚመለከት የሚኖር የስጋት ደረጃን የሚወስን በጥናት ላይ የተመሰረተ መመሪያ ሊያወጣ ይገባል፡፡
- ባለስልጣኑ የአገልግሎት አሰጣጡን እና የቁጥጥር ስርዓቱን ለማሻሻል በየበጀት ዓመቱ የቀይ ስጋት ደረጃን ዝቅ ለማድረግ የሚታቀደውን ለማሳካት ያላሰለሰ ጥረት ሊያደርግ ይገባል፡፡

143. **የጉምሩክ መጋዘን ሥነ-ሥርዓት አፈጻጸም ውጤታማ እና ቀልጣፋ መሆኑን ማረጋገጥ በተመለከተ፣**

- ባለስላጣኑ በአዋጅ ቁጥር 859/2006 የተቀመጡትን ግዴታዎች እና ስለጉምሩክ መጋዘን አስተዳደር የወጣ የአፈፃፀም መመሪያ ቁጥር 40/2002 ላይ የተቀመጡ መስፈርቶች ሳያሟሉ የሚሰሩ የጉምሩክ መጋዘኖች ላይ ክትትል በማድረግ የማስተካከያ እርምጃ ሊወስድ ይገባል፡፡
- ባለስልጣኑ በጊዜያዊ የጉምሩክ የዕቃ ማከማቻ መጋዘኖች  ዕቃዎች እንደአይነታቸውና እንደባህሪያቸው ተለይተው ለደህንነታቸው ተስማሚ በሆነና ለጉምሩክ ቁጥጥር አመቺ በሆነ ሁኔታ መቀመጣቸውን ሊያረጋግጥ፣በባለስልጣኑ አዋጅ ቁጥር 859/2006 አንቀጽ 59 ንዑስ አንቀጽ 2 መሰረት በጉምሩክ መጋዘን ኪራይ ማስከፈያ ተመን ደንብ እንዲወጣ ሊያደርግ ይገባል፡፡
- በጉምሩክ መጋዘን የዕቃዎች በመጋዘን የቆይታ ጊዜ በጉምሩክ አዋጅ ቁጥር 859/2006 በተቀመጠው መሰረት ተግባራዊ ሊደረግ ይገባል፡፡

144. **ባለስልጣኑ ብቁና የተሟላ የሰው ኃይል ፣ በዘመናዊ ቴክኖሎጂ የታገዘ የመረጃ አጠቃቀም፣ አያያዝ እና ልውውጥ ያለው መሆኑን እንዲሁም ከባለድርሻ አካላት ጋር በቅንጅት የሚሰራበት የአሰራር ሥርዓት የዘረጋ እና ተግባራዊ ያደረገ መሆኑን መገምገም፤**

- የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን በማቋቋሚያ አዋጅ 587/2000 በተሰጠው ስልጣንና ተግባር መሰረት የሠራተኞችን  አቅም ለመገንባት የሚያስችለውን ማዕከል ሊያደራጅ እና ብቁና የተሟላ የሰው ኃይል እንዲኖር ሊያደርግ ይገባል፡፡
- በባለስልጣኑ የሚሰሩ ስራዎች በዘመናዊ የመረጃ ቴክኖሎጂ የተደገፉ ሊሆኑ ይገባል፡፡

- በባለስልጣኑ የሚተገበሩ ፕሮጀክቶች ወደ ትግበራ ከመግባታቸው በፊት በተሟላ ጥናት ሊሰራ እና የወደፊቱን ታሳቢ ያደረጉ ሊሆኑ ይገባል ፡፡በተጨማሪም በባለስልጣኑ በሂደት ላይ የሚገኘው ኤሌክትሮኒክስ አንድ መስኮት አገልግሎት ፕሮጀክት በፍጥነት ተጠናቆ ወደ ትግበራ ሊገባ ይገባል፡፡
- በባለስልጣኑ በቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች የሚሰሩ ስራዎች ወጥነት እንዲኖራቸው ተከታታይነት ያለው የድጋፍና ክትትል ስራዎች ሊሰራ ይገባል፡፡
- በባለስልጣኑ ቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች ከባለድርሻ አካላት ጋር የሚደረጉ ውይይቶች ወጥነትና ተከታታይነት ያላቸው ሊሆኑ ይገባል፡፡

## አባሪ 1 ያለዘርፍ አስመጪነት ዕቃዎችን ያስመጡ ዝርዝር

| ተ.ቁ | የአስመጪው ስም | ዲክላራሲን ቁጥር | የእቃው አይነት |
|---|---|---|---|
| 1 | MICHAEL MEKONNEN YELEM | C-5584/16 | GENERATORS MASE 60 KVA |
| 2 | YARED MULUGETA | S-72/16 | DAEWOO BUS |
| 3 | K.O.JJ FOOD PROCESSING COMPLEX | C-34700/15 | ISUZU |
| 4 | GETACHEW WELDU | C-33210/15 | DIFFERENT ITEMS |
| 5 | ZULAKA MOHAMMED GORJI | C-22745/15 | CONSTRUCTION GOODS |
| 6 | FETSUM AMARE MERID | C-20963/15 | IVECO EUROSTAR & TRAILER |
| 7 | ASER CONSTRUCTION PLC | C-21130/15 | ISUZU FSR |
| 8 | TIKIKEL YIMER | C-20807/15 | FORKLIFT |
| 9 | አብዱልዋሲ. አሊሽ | C-20642/15 | ጀኔሬተር |
| 10 | THE FOUR B TRADE PLC | C-20515 | GLASS,GLU T-SHIRT,CARPET & DIFFERENT ITEMS |
| 11 | ALUMINIUM WORLD TRADING PLC | C-19768 | HONEY FILTER MACHINES |
| 12 | ABAYA MECHANICAL ENGINERING | C-19388 | CLLINDER LINER |
| 13 | ዘሪቱ በቀለ | C-18436 | ጅፕሰምዘፐሊይውድ |
| 14 | GETACHEW WOLEDU | C-18978 | WALDROBE& KITCHEN CABINET |
| 15 | ASMEROM G/MECHIL | C-18372 | OTHER PLASTICS |
| 16 | ASMEROM G/MECHIL | C-18389 | OTHER PLASTICS |
| 17 | MISBAH KELIFA | C-18548 | OTHER PLASTICS FABRICS |
| 18 | FAST FOOD MY BURGER INT | C-16700 | MERCEDES BENZ TRUCK |
| 19 | GMT/BGI | C-16597 | MALT PILSEN |
| 20 | ባማኮን ኢ/ሪግ | C-118167 | መኪና |
| 21 | DMC CONST.PLC | C-17552 | VEHICLES |
| 22 | GETACHEW WOLEDU | C-15710 | DOORS,PARAFUET WITH ACCESSORIES |
| 23 | ELFORA,ACRO PLC | C-16533 | WEIGH-BRIDGE |
| 24 | EDNAMOLL | C-13803 | CHAILED BUMBER |
| 25 | WELKITE | C-13730 | TOYOTA,ISUZU CAR |
| 26 | CHENGWEN | C-14401 | NOODLE,COUNTINYM |
| 27 | LIBIYA OIL ETHIOPIA | C-21531/15 | BITUMEN |
| 28 | GMT/BGI | C-25465/15 | IVECO TRAKER |
| 29 | GMT/BGI | C-25076/15 | IVECO TRAKER |
| 30 | GMT/BGI | C-25576 | IVECO TRAKER |
| 31 | DEEJE ZELEKE | C-1945 | PP YARN,PACKING POLY GAG |
| 32 | HARAR BERWERY | C-1355 | TABLE |
| 33 | MOHAMMED AWEL | C-5021/16 | STEEL COILS |
| 34 | KAHISAY ABRHA | C-7940/16 | STEELBAR |

## አባሪ 2

## የኦዲቱ የትኩረት አቅጣጫዎችና የመመዘኛ መስፈርቶች


| የኦዲቱ የትኩረት አቅጣጫዎች | የኦዲት መስፈርቶች |
|---|---|
| 1. በባለስልጣኑ የተዘረጋው የጉምሩክ የትራንዚት ሥነ-ስርዓት በሁሉም የጉምሩክ መቆጣጠሪያ ጣቢያዎች ተግባራዊ መደረጉን ማረጋገጥ፤ | 1. ባለስልጣን መ/ቤቱ በዓለም አቀፍ ደረጃ ለሚታወቁ የጉምሩክ ትራንዚት ዓይነቶች ፍቃድ ከመስጠቱ በፊት በመመሪያው የተቀመጡትን መስፈርቶች ያሚሉ ስለመሆናቸው ሊያረጋግጥ ይገባል። |
| | 2. ማንኛውም በትራንዚት የተመዘገበ ዕቃ እንቅስቃሴውን ከመጀመሩ በፊት የጉምሩክ ትራንዚት ስነ ሥርዓት ሊፈጸምበት ይገባል። |
| | 3. ባለስልጣን መ/ቤቱ ታሽገውና ሳይታሸጉ የሚጓጓዙ የትራንዚት እቃዎችን በጉምሩክ ትራንዚት ሥነ-ሥርዓት አፈፃፀም መመሪያ ላይ በተቀመጠው መስፈርት መሰረት በመለየት መታሸግ የሚገባቸው እቃዎች በጉምሩክ ማሸጊያ መታሸጋቸውን ሊያረጋግጥ ይገባል። |
| | 4. ባለስልጣኑ ትራንዚት የጀመሩ ጭነቶችን መረጃ ወደ መረጃ ቴክኖሎጂ ቋት መተላለፋቸውን ሊያረጋግጥ ይገባል። |
| | 5. ባለስልጣን መ/ቤቱ ታሽገው የሚጓጓዙ የትራንዚት እቃዎች በታሸጉበት ሁኔታ ስለመድረሳቸው ሊያረጋግጥ ይገባል። |
| | 6. የባለስልጣኑ የጉምሩክ ትራንዚት መነሻ ቦታዎች ወይም ጣቢያዎች የእቃውን ትክክለኛነት ሲጫን በአካል ተገኝቶ በማረጋገጥ በሲል ማሸግና ሲል ቁጥሩን በአውቶሜሽን ሲስተም በመመዝገብ የትራንዚት ፈቃድ አዘጋጅቶ በመስጠት ትራንዚቱ እንዲጀምር ሊያደርጉ ይገባል። |
| | 7. ባለስልጣኑ ወደሀገር የሚገቡ፣ የሚወጡ እና የተላላፊ የትራንዚት እቃዎች በተፈቀደላቸው መስመር መጓጓዛቸውን ሊያረጋግጥ ይገባል። |
| | 8. ባለሥልጣኑ የትራንዚት እቃዎች በተነሱበት ሁኔታ እና በተቀመጠው የጊዜ ገደብ መሰረት የደረሱ ስለመሆኑ ሊያረጋግጥ ይገባል። |
| | 9. ባለስልጣኑ በጊዜ ገደቡ የደረሱና ያልደረሱትን የትራንዚት እቃዎች በሲስተም የማጣራትና የማስታረቅ (Reconciliation) ስራ በመስራት በጊዜ ያልደረሱትን ወደ ህግ ማስከበር በማስተላለፍ ክትትል እንዲደረግባቸውና ያስያዙት ዋስትና ገቢ እንዲሆን ሊያደረግ ይገባል። |
| | 10. የጉምሩክ ትራንዚት ስነ-ሥርዓት በዘመናዊ የመረጃ ቴክኖሎጂ እና በስጋት ስራ አመራር አሰራር ስርዓት መሰረት ሊከናወን ይገባል። |
| | 11. ባለስልጣን መ/ቤቱ በጉምሩክ ወደቦች ፣ በወሰን አካባቢዎች ፣ በጉምሩክ መቆጣጠሪያ ጣቢያዎችና ማቋረጫ መስመሮች በኩል የሚገቡና የሚወጡ እቃዎችንና ማጓጓዣዎችን ሊፈትሽና የጉሙሩክ ስነ-ስርዓት ተፈጽሞባቸው መግባታቸውንና መውጣታቸውን ሊያረጋግጥ ይገባል። |

| የኦዲቱ የትኩረት አቅጣጫዎች | የኦዲት መስፈርቶች |
|---|---|
| 2. **በባለስልጣኑ የተዘረጋው የጉምሩክ ዕቃ አወጣጥና የመጋዘን አሠራር ስርዓት ቀልጣፋ እና ውጤታማ መሆኑን መገምገም፤** | |
| 1. **የጉምሩክ ዕቃ አወጣጥ ሥነ-ሥርዓት በብቃት እና በቅልጥፍና የሚከናወን መሆኑን ማረጋገጥ፤** | 2.1.1. ባለስልጣኑ የገቢ ፣ የወጪ እና የተላላፊ ዕቃዎችን በሚመለከት የሚኖር የስጋት ደረጃን የሚወስን መመሪያ ሊያወጣ ይገባል፡፡ |
| | 2.1.2. በባለስልጣኑ የሚሰጥ የጉምሩክ አገልግሎት እና የሚከናወን የቁጥጥር ስርዓት በመረጃ በተደገፈ መመዘኛ የገቢ ፣ የወጪ እና የተላላፊ ዕቃዎችን የስጋት ደረጃ በመለየት የአገልግሎት አሰጣጥን እና የቁጥጥር ስርዓቱን ሚዛናዊነት ጠብቆ መከናወን ይገባዋል፡፡ |
| | 2.1.3. ቀለል ያለ የጉምሩክ ስነ-ስርዓት የሚፈቀድላቸው ሰዎች ባለስልጣኑ ያስቀመጠውን መስፈርት ያሟሉ ስለመሆናቸው ሊረጋገጥ ይገባል፡፡ |
| | 2.1.4. ማናቸውም ዲክላራሲዮን ሊቀርብበት የሚገባ ገቢ፣ ወጪ እና ተላላፊ ዕቃ የእቃ ዲክላራሲዮን ሊቀርብበት፣ትክክለኛነቱ ወዲያውኑ ሊረጋገጥ እና ተቀባይነት ማግኘቱና አለማግኘቱ ለአቅራቢው በጽሁፍ ሊገለጽለት ይገባል፡፡ |
| | 2.1.5. ባለስልጣኑ ዲክላራሲዮን ለመሰረዝ የሚያስችሉ በመመሪያው የተቀመጡ ምክንያቶችን በአንድ ላይ ወይም በተናጠል ሲያገኝ ሊሰረዝ ይገባል፡፡ |
| 2. **የጉምሩክ መጋዘን ሥነ-ሥርዓት አፈጻጸም ውጤታማ እና ቀልጣፋ መሆኑን ማረጋገጥ፤** | 2.2.1. ባለስልጣኑ ወደአገር የሚገቡና ከአገር የሚወጡ እቃዎችን ለማከማቸት የተዘጋጁ መጋዘኖች በመመሪያው የተቀመጠላቸውን መስፈርት ያሟሉ ስለመሆናቸው ክትትልና ቁጥጥር ሊያደርግ ይገባል፡፡ |
| | 2.2.2. ባለስልጣኑ የጉምሩክ መጋዘን እንዲያቋቁም የተፈቀደለት ሰው በአዋጁ የተቀመጠውን ግዴታ እየተወጣ ስለመሆኑ የክትትልና የቁጥጥር ስራ ሊሰራ ይገባል፡፡ |
| | 2.2.3. በየጉምሩክ መጋዘኖች ወደ ጉምሩክ መጋዘን የገቡ ዕቃዎች እንደአይነታቸውና እንደባህሪያቸው ተለይተው ለደህንነታቸው ተስማሚ በሆነና ለጉምሩክ ቁጥጥር አመቺ በሆነ ሁኔታ የተቀመጡ መሆናቸው ሊረጋገጥ ይገባል፡፡ |
| | 2.2.4. ወደ ጉምሩክ መጋዘን የሚገቡና የጉምሩክ ሥነ-ስርዓት ተፈጽሞባቸው የሚለቀቁ እቃዎች ባለስልጣኑ በወሰነው የመዝገብ አያያዝ ስርዓት መመዝገባቸውና ምዝገባው ሪፖርት ስለመደረጉ መረጋገጥ አለበት፡፡ |
| | 2.2.5. ማንኛውም ገቢ እና ወጪ እቃ በመጋዘን ውስጥ ለቆየበት ጊዜ የመጋዘን ኪራይ ሂሳብ መከፈሉ መረጋገጥ አለበት፡፡ |
| | 2.2.6. ባለስልጣኑ እቃዎች በመጋዘን ውስጥ የሚቆዩት በጉምሩክ አዋጅ በተቀመጠው የጊዜ ገደብ መሰረት መሆኑን ማረጋገጥ አለበት፡፡ |
| | 2.2.7. ባለስልጣኑ ወደ ጊዜያዊ የጉምሩክ ዕቃ ማከማቻ ወይም በንድድ መጋዘን የገባ ዕቃ በአዋጁ በተቀመጠው ጊዜ ውስጥ ካልወጣ ወደ መንግስት ጉምሩክ መጋዘን እንዲዛወር ሊያደርግ ይገባል፡፡ |


| የኦዲቱ የትኩረት አቅጣጫዎች | የኦዲት መስፈርቶች |
|---|---|
| | 2.2.8. የጊዜያዊ የጉምሩክ ዕቃ ማከማቻ ወይም የቦንድድ ጉምሩክ መጋዘን ኃላፊ በዕቃ ዲክላራሲዮኑ ፣ በጭነት ማኒፌስት ወይም በትራንዚት ሰነድ ከተገለጸው መጠን በላይ ዕቃ ያገኘ እንደሆነ በትርፍ የተገኘውን ዕቃ ዲክላራሲዮኑ ለቀረበለት የባለስልጣኑ ቅርንጫፍ ወዲያውኑ ሪፖርት ሊያደርግና በትርፉ እቃ ላይ የሚፈለገው ቀረጥና ታክስ ወዲያውኑ መከፈሉ ሊረጋገጥ ይገባል፡፡ |
| 3. ባለስልጣኑ ብቁና የተሟላ የሰው ኃይል ፣ በዘመናዊ ቴክኖሎጂ የታገዘ የመረጃ አጠቃቀም ፣ አያያዝ እና ልውውጥ ያለው መሆኑን እንዲሁም ከባለድርሻ አካላት ጋር በቅንጅት የሚሰራበት የአሰራር ሥርዓት የዘረጋ እና ተግባራዊ ያደረገ መሆኑን መገምገም፤ | 1. ባለስልጣኑ በጉምሩክ ስነስርዓት አፈጻጸም ላይ ያለውን የማስፈጸም አቅም ለማሳደግ እንዲችል ወቅታዊና የክህሎት ክፍተትን መሰረት ያደረገ ስልጠና ያገኘና የተሟላ የሰው ኃይል ሊኖረው ይገባል፡፡ |
| | 2. ባለስልጣኑ በዘመናዊ ኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ የታገዘ የመረጃ አጠቃቀም ፣ አያያዝ እና ልውውጥ ሊኖረውና ተግባራዊ ሊያደርግ ይገባል፡፡ |
| | 3. ባለስልጣኑ የወጪ እና ገቢ እቃዎችን በሚመለከት የአንድ መስኮት አገልግሎት ለመስጠት እንዲቻል የሚመለከታቸው የመንግስት መ/ቤቶችና የፋይናንስ ተቋማት በተዘረጋው የኤሌክትሮኒክስ መረጃ ልውውጥ ስርዓት ተጠቃሚ እንዲሆኑ ሁኔታዎችን ሊያመቻች ይገባል፡፡ |
| | 4. ባለስልጣን መ/ቤቱ በየቅርንጫፍ ጽ/ቤቶችና መቆጣጠሪያ ጣቢያዎች ያሉ የጉምሩክ አሰራሮች ወጥነት ያላቸው ስለመሆኑ በተለያየ ጊዜ የዳሰሳ ጥናት ሊያካሂድና በጥናቱ የተገኙ በአሰራር ያጋጠሙ ግድፈቶች እንዲታረሙና ምርጥ ተሞክሮዎች በሁሉም የቅርንጫፍ መ/ቤቶች እንዲተገበሩ ሊያደርግ ይገባል፡፡ |
| | 5. ባለስልጣን መ/ቤቱ በቅርንጫፍ መ/ቤቶችና በመቆጣጠሪያ ጣቢያዎች የሚሰራው የክትትልና የድጋፍ አሰጣጥ ስራ በተያዘለት ጊዜ መሰረት ሊከናወንና በአፈፃፀም ወቅት ላጋጠሙ ችግሮች ወቅታዊ ምላሽ ሊሰጥ ይገባል፡፡ |
| | 6. ባለስልጣኑ የጉምሩክ ስነ-ስርዓትን በተመለከተ ከባለድርሻ አካላት ጋር መደበኛ እና ተከታታይነት ያለው የመወያያ መድረክ ሊኖረው እና በመድረኩ የሚነሱ ጉዳዮችን የሚፈታበት ስርአት ሊኖረው ይገባል፡፡ |

## አባሪ 3 የጉምሩክ ስነ -ሥርዓት የስራ ፍሰት ስዕላዊ መግለጫ


### ሀ.የመልቲ ሞዳል ገቢ ዕቃ ትራንዚት ሥነ-ሥርዓት አፈፃፀም የስራ ፍሰት ስዕላዊ መግለጫ




## ሲ.የዩኒ ሞዳል ገቢ ዕቃ ትራንዚት ሥነ-ሥርዓት አፈፃፀም ስዕላዊ መግለጫ




## ሐ.የወጪ ዕቃዎች ትራንዚት ሥርዓት ስዕላዊ መግለጫ



መ.ወደ መድረሻ ቦታቸው ደርሰው ትራንዚት ያጠናቀቁ እቃዎች ላይ የሚፈፀም የእቃ አወጣጥ ሥርአት ስእላዊ መግለጫ






ሰ.የዕቃዎች ወደ ጉምሩክ መጋዘን አገባብና አወጣጥ ስነ ሥርዓት የስራ ፍሰት መግለጫ